በማስተማሪያ ቋንቋነት፡ በኦሮሚያ ክልል ለአራተኛ ክፍል የተዘጋጀ የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ተገቢነት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት
የቀረበ ጥናት

ለአማርኛ ማስተማር /TEAM/ ኤም.ኤ.ዲግሪ
ማሟያ የተዘጋጀ

ወንድአጥር ደነቀ
ሰኔ፡ 1993

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በማስተማሪያ ቋንቋነት፡ በኦሮሚያ ክልል ለአራተኛ ክፍል የተዘጋጀ የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ተገቢነት

በ

ወንድአጥር ደነቀ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ	ፈርማ
ፈታኝ	ፈርማ
ፈታኝ	ፈርማ

ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ጊዜያቸውን ሰውተው ጽሑፌን በጥንቃቄ በማንበብ፣ የማሻሻያ ሀሣብ በመስጠትና በማረም የቅርብ ክትትልና እገዛቸው ላልተለየኝ አማካሪዬና መምህሬ ለዶ/ር መኮንን ዲሳሳ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

የግል መፅሐፎቹን በማዋስ፣ ጠቃሚ ምክሮችን በመለገስና ልምዱን በማካፈል ሙያዊ ድጋፉ ላልተለየኝ ለሰለሞን ተሰማ ያለኝን አክብሮትና ምስጋና የላቀ ነው:: እንዲሁም መጽሐፍ በማዋስ ለረዳኝ ለሙስባህ፣ በትምህርት ቤት ቆይታዬ እገዛውን ላላልተለየኝ፣ ስታስቲካዊ ስሌቶችን በኮምፒዩተር በመሥራት ለተባበሩኝ እንዳለ ሸዋንግዛው ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

ለጥናቱ መሳካት በቂ ክፍለ ጊዜና ተጠኝ ተማሪዎችን እንዳገኝ ለረዱኝ ለመንደራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሥራ ኃላፊና መምህራን ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፣ መጠይቆችንና ፈተናዎችን በማባዛት በኩል ትብብር ላደረጉልኝ የጅማ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንና አስተዳደር ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው::

በትምህርት ቤት ቆይታዬ ያለመታከት ድጋፋቸውና ምክራቸው ላልተለየኝ ለእናቴ ለወ/ሮ አስራት ብርሃኔ፣ ለባለቤቴ ፀሐይ ባወቀ፣ ለእህቶቼ ለፀዳለ፣ ፋንታዬና ሰብለ ደነቀ፣ ለሙሉብርሃን ገ/ሔር እና ለእንዳለልኝ አንበሴ ያለኝን ከፍ ያለ ልባዊ ምስጋና እና አክብሮት እገልፃለሁ::

በመጨረሻም ዋናውን ጥናት በኮምፒውተር በመፃፍ ቀና ትብብሯ ላልተለየኝ ለወ/ሮ ንግሥት ግደይ፣ የሞራል ማበረታቻ ያደረጉልኝ ለነበሩት ጓደኞቼ መኮንን ክብረት፣ ጠና ጨርቆስ፣ ተሾመ ሸዋረገድ፣ አግዛ ብዛና አስፋወሰን ብርሃኔ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

ማውጫ

ገፅ

ምስጋና i
አጎፅሮተ-ጥናት ii

ምዕራፍ አንድ - መግቢያ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ 1
1.2. የጥናቱ ዓላማ 3
1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት 4
1.4. የጥናቱ ገደብ 5

ምዕራፍ ሁለት - ክለሳ ድርሳን 6
2.1. የንባብ ግንዛቤዎች 6
2.1.1. ከታች ወደላይ የንባብ አቀራረብ 6
2.1.2. ከላይ ወደታች የንባብ አቀራረብ 7
2.1.3. መስተጋብራዊ የንባብ ሂደት አቀራረብ 8
2.2. የትምህርት ይዘቶችን አንብቦ ለመገንዘብ የሚያስፈልጉ የንባብ ክሂሎች 9
2.3. የውጤታማ አንባቢ ባህርያት 11
2.4. የንባብ ክሂልን ለማዳበር የሚቀርብ መልመጃዎች ባሕሪይ ... 16
2.5. ውጤታማ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ 18

ምዕራፍ ሶስት ያጠናን ዘዴ 23
3.1. የጥናቱ አካሄድ 23
3.2. የናሙና አመራረጥ 24
3.3. የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች 25

ምዕራፍ አራት የመረጃዎች ውጤትና ትንተና 27
4.1. ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰጥ የአማርኛ ንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ግምገማ 27
4.1.1. በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የንባብ ክሂል ትምህርቶች አቀራረብ ብቃት 27
4.1.2. የአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ የሚጠይቀው የንባብ ክንዋኔዎች 31
4.1.3. በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የንባብ ክሂል መልመጃዎች የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቃቸውን የንባብ ክንዋኔዎች ከማለማመድ አንፃር 33
4.1.4 ከመምህራን የተገኙ መረጃዎች ትንተና 37

4.2. የንባብ ክሂልን ለማዳበር የሚያግዝ አማራጭ የትምህርት አቀራረብ ናሙና 43
4.3. የቅድመና ድህረ-ልምምድ የንባብ ፈተናዎች ውጤት ስታት ስቲካዊ ትንተና 49

ምዕራፍ አምስት- ማጠቃለያና አስተያየት 52
5.1 ማጠቃለያ 52
5.2 አስተያየት... 57
ዋቢዎች 59
የአባሪዎች ዝርዝር
ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ... 62
ለክትትልና ለሙክራ ቡድን ተማሪዎች የተሰጡ ቅድመና ድህረ- ልምምድ
የንባብ ፈተናዎች... 69
በአማራጭነት የቀረበ የትምህርት አቀራረብ ዝግጅት ናሙናዎች 77
የቲ- ስሌት ውጤት መግለጫ... 82
የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ናሙና... ... 86

አጎፅሮተ-ጥናት (Abstract)

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል አማርኛ መማሪያ ቋንቋቸው ለሆኑ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰጥ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ፥ ለዚያው ደረጃ የቀረበው የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቀውን የንባብ ክሂል ለማዳበር ምን ያህል ብቃት አለው? ክሂሉን በተሻለ መልኩ ለማዳበር የንባብ ትምህርቱ እንዴት ቢቀርብ ይሻላል? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት፥ ገላጭ (Descriptive) እና ሙከራዊ (Experimental) የጥናት ዘዴን በመጠቀም የትምህርቱን አቀራረብ የገመገመና አማራጭ የትምህርት አቀራረብ በማዘጋጀት በሙከራ የፈተሸ ጥናት ነው::

ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበው የአማርኛ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ክሂሉን ለማዳበር ያለው ብቃት

- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የንባብ ክሂል ትምህርቶች አቀራረብ ተገቢነት ከመስኩ ምሁራን በተገኙ ወቅታዊና ውጤታማ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ትወራዎች አንፃር በመመዘን፥
- በአማርኛና በአካባቢ ሳይንስ መፃሕፍት ውስጥ የቀረቡ የንባብ ክንዋኔዎችን በንፅፅር በመመልከት፥
- መምህራንን መጠየቅ በማስሞላት የክፍል ውስጥ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረባቸውን በመቃኘት ተገምግሟል::

በዚህ መልክ የተገመገመው የትምህርት አቀራረብ የንባብ ክሂልን በደረጃው ለማዳበር፥ የአካባቢ ሳይንስ የሚጠይቀውን የንባብ ክሂል ለማለማመድ ያለው ብቃት ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል::

በአራተኛ ክፍል ደረጃ የንባብ ክሂልን በተሻለ መልኩ ሊያዳብር ይችላል ተብሎ በአማራጭነት የተዘጋጀው የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ፥ በአጋጣሚ ናሙና በተመረጡ የክትትልና የሙከራ ቡድን ቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና (Randomized Control and Experimental Group: Pre test-Posttest) ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ ውጤታማነቱ በሙከራ ተፈትሿል::

ሙከራውን ለማካሄድ በአጋጣሚ ናሙና (Random Sampling) ለተመረጡ የክትትልና የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የቅድመና ድህረ-ልምምድ ፈተና ተሰጥቶ፣ በፈተናዎቹ ውጤት መካከል የታየው ልዩነት በቲ-ስሌት(t-test)ታይቷል::

በተገኘው ስታቲስቲካዊ ውጤት የክትትል ቡድን ተማሪዎች የቅድመና ድኅረ-ልምምድ ፈተናወች ውጤት ከቲ-ስርጭት ዋጋ ያነሰ ሆኖ ሲገኝ፣ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የቅድመና ድህረ-ልምምድ ፈተናዎች ውጤት ከቲ-ስርጭት ዋጋ የበለጠ ሆኗል::

ይህ ውጤት የክትትል ቡድን ተማሪዎች የድህረ-ልምምድ ፈተና ውጤት ከቅድመ-ልምምድ ፈተና ውጤት የጎላ ልዩነት እንዳላሳየ ሲያመለክት፣ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በአማራጭነት በቀረበው የትምህርት አቀራረብ ከመለማመዳቸው በፊት በወሰዱት የቅደመ-ልምምድ ፈተና ውጤት፣ በአማራጭነት በቀረበው የትምህርት ዝግጅት ከተማሩ በኋላ የተፈተኑት የድህረ-ልምምድ ፈተና ውጤት የተሻለ ሆኖ መገኘቱን አመላክቷል::

ይህም ለሙከራ የቀረበው የትምህርት አቀራረብ፣ በአራተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡ የንባብ ክሂል ትምህርቶች አቀራረብ በተሻለ መልኩ ክሂሉን ለማዳበር ብቃት እንዳለው የሚያሳይ ሆኖ ተገኝቷል::

ከጥናቱ በተገኙ መረጃዎች መነሻነት የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ በየጊዜው መፈተሸና በሙከራ ስለማጠናከር፣ መምህራንንና መማሪያ መፃሕፍት አዘጋጆችን ከወቅታዊና ውጤታማ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ጋር ስለማስተዋወቅና በመማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ወቅት ሌሎች ትምህርቶች የሚጠይቁትን የንባብ ክሂል በጥናት ሰለመለየት አስፈላጊነት አስተያየት ቀርቧል::

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ

በመደበኛ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ የትምህርት አይነቶችን ለመከታተል የሚመጡ ተማሪዎች፥ የንባብ ክሂል (Reading Skills) የግድ ሊኖራቸው የሚገባ መሠረታዊ ክሂል ነው። መሠረታዊ መባሉም የሌሎች ትምህርቶች መቅረቢያና መማሪያ መሣሪያ በመሆኑ ነው (Jarolimek and Foster 1997)።

ህፃናትም ሆኑ አዋቂዎች በአብዛኛው የሚማሩት ከንባብ ሂደት በሚገኝ ግንዛቤ በመሆኑ፥ መሠረታዊ የንባብ ክሂል ትምህርት ለህፃናት መስጠት የማንኛውንም ትምህርት ይዘት አንብበው እንዲገነዘቡ ማስቻል እንደሆነ፥ የብዙ ወላጆችና መምህራን እምነት ነው (May 1990)። አንዳንድ ጥናቶችም፥ ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የሚሰጡ የትምህርት አይነቶች የሚጠይቁትን የንባብ ክሂሎች ማስተማር ለትምህርት ውጤት መሻሻል ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ይገልፃሉ (Jarolimek and Foster 1997)።

ለዚህም የመማሪያ ቋንቋው በትምህርትነት ሲቀርብ፥ የትምህርት ይዘቶቹ የሚጠይቁትን የንባብ ክሂሎች ሊያዳብር በሚችልበት መልክ በመቅረብ እገዛ ሊያደርግ እንደሚገባ ይታመናል፤ በየደረጃው የሚሰጥ የንባብ ክሂል ትምህርት አላማም፥ ተማሪዎችን ከተለያዩ የንባብ ስልቶች ጋር የሚያስተዋውቅ ሊሆን ይገባል (Silberstein 1994)።

በየደረጃው በቀረቡ የአማርኛ መርሀ ትምህርቶችና በነሱ መነሻነት (በመርሀ ደረጃ) በተዘጋጁት መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ከተጠቀሱት አላማዎች መካከል፥ የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ማዳበር አንዱ ነው። ይሁን እንጅ፥ ክሂሉን በተሻለ መንገድ ለማዳበር የሚረዱ ወቅታዊ የማስተማሪያ ዘዴዎች በተግባር ላይ ባለመዋላቸው፥ የተማሪዎች አንብቦ የመገንዘብ ችሎታ ዝቀተኛ እንደሆነ (ሰለሞን 1990 ዓ.ም) በአማርኛ ማስተማሪያ መሣሪያዎችና በክፍል ውስጥ ትምህርት አቀራረብ ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙ ይገልፃል።

ዛሬም ቢሆን ብዙ ወላጆችና የአንደኛ ደረጃ መምህራን፥ ተማሪዎች በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የቀረቡላቸውን የትምህርት ይዘቶች አንብበው የመገንዘብ ችሎታቸው ዝቅተኛ በመሆኑ፥ አጠቃላይ የትምህርት ውጤታቸው አጥጋቢ እንዳልሆነ ሲገልፁ ይደመጣሉ። ለዚህ በምክንያትነት ሊጠቀሱ ከሚችሉ ተላውጦዎች መካከል፥ የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ሌሎች ትምህርቶች የሚጠይቁትን የንባብ ክሂል ለማዳበር ተገቢ በሆነ መልኩ ባለመቅረቡ ሊሆን ይችላል።

ይህን አመለካከት፥ በዳራዊ ጥናት (Background Research) ለማጠናከር፥ የዚህ ጥናት አቅራቢ በጅማ ከተማ ከሚገኙ አንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው ሳይክል ትምህርት ቤቶች መካከል፥ በነሲብ ናሙና (Random Sampling) በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ ሃያ መምህራንን መጠይቅ በማስሞላት መረጃ ለማሰባሰብ ሞክሯል።

በተገኘው መረጃ 78% ያህሉ የተማሪዎቻቸው አንብቦ የመገንዘብ ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ ሲገልፁ፥ 22% የሚሆኑት መካከለኛ እንደሆነ አመልክተዋል። በተጨማሪም 72% ያህሉ የአማርኛ የንባብ መልመጃዎች ሌሎች ትምህርቶች የሚጠይቁትን የንባብ ክሂሎች ለማለማመድ ያላቸው አጋዥነት ዝቅተኛ እንደሆነ ሲገልፁ፥ አብዛኞቹ መልመጃዎች ከምንባብ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች መፈለግና ዐረፍተነገር መመስረት ላይ የሚያተኩሩ እንደሆኑ መጠይቁን ከሞሉት 76% ያህሉ ጠቁመዋል። አጠቃላይ የትምህርቱ አቀራረብ የንባብ ክሂልን ለማዳበር ተገቢነት አለው ብለው እንደማያምኑ ሁሉም መምህራን አረጋግጠዋል።

የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረባቸውን በተመለከተ፥ 75% ያህሉ ተማሪዎቻቸውን ተራ በተራ በማስነሳት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የማስነበብ ስልትን አዘውትረው እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ፥ 25% የሚሆኑት ብቻ የግል የፀጥታ ንባብ (Silent reading) ስልት እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል፤ መጠይቁን የሞሉት መምህራን በሙሉ የንባብ ክሂል መልመጃዎችን የሚያቀርቡት ምንባቡ ተነቦ ካለቀ በኋላ እንደሆነም አረጋግጠዋል።

በዚህ መልክ የሚቀርብ የንባብ ክሂል ትምህርት፥ የትምህርት ይዘቶችን አንብቦ ለመገንዘብ የሚያስችል የንባብ ክሂል ለማዳበር ያግዛል ብሎ መጠበቅ አስቸጋሪ ይሆናል። ስለዚህ ችግሩን በመጠኑም ቢሆን ለማቃለል፥ የትምህርቱን አቀራረብ በስፋት በመመርመር፥ አማራጭ የትምህርት አቀራረብ መንገድ መሞከርና ውጤታማነቱን ማረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል።

አማርኛ የማስተማሪያ ቋንቋ በሆነባቸው ደረጃዎች የተደረጉ ቀደምት ጥናቶች፡ የቋንቋው ትምህርት አቀራረብ ክሂሎችን ለማዳበር ብቃት እንደሌለው እና በደረጃው ለቀረቡ ትምህርቶችም መማሪያነት ያለው እገዛ ዝቀተኛ እንደሆነ ጠቅለል ባለ መልኩ የሚገልፁ ናቸው (ሰናይት 1974፡ የሻነው 1980፡ ነገሠ 1989)። ይሁን እንጂ፡ የትምህርቱ አቀራረብ የሚታይበትን ችግር ለማቃለል የሚያግዝ አማራጭ መንገድ ለማቅረብ የሚሞክሩ አይደሉም፡ ስለዚህ በንባብ ክሂል አቀራረብ ላይ የሚታየውን ችግር በመጠኑም ቢሆን ለማቃለል፡ የዚህ ጥናት መከናወን አስፈላጊ ይሆናል።

1.2 <u>የጥናቱ ዓላማ</u>

በኦሮሚያ ክልል (ኦሮምኛ የአፍ መፍቻቸው ላልሆኑ ተማሪዎች) አማርኛ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስተማሪያ ቋንቋነት ያገለግላል። በዚህ ደረጃ የሚሰጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አቀራረብ፡ እንደ ማስተማሪያ ቋንቋነቱ ሌሎች ትምህርቶችን በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የአጋዥነት ሚና ሊኖረው ይገባል። ከዚህ አንፃር ይህ ጥናት ለአራተኛ ክፍል ከሚሰጡ የትምህርት አይነቶች መካከል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርትን በናሙናነት በመውሰድ የሚከተለው አላማ ይኖረዋል።

የጥናቱ ዓላማ፡ ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰጥ የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ፡ ለዚያው ደረጃ የቀረበው የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቀውን የንባብ ክሂል ለማዳበር ያለውን ተገቢነት በመመርመር፡ በተሻለ ደረጃ ክሂሉን ለማዳበር የሚያግዝ አማራጭ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ መንገድ መሞከርና ውጤታማ መሆን አለመሆኑን መፈተሽ ነው።

ጥናቱ ከላይ የቀረበውን አጠቃላይ አላማ መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞክራል።

1. ለአራተኛ ክፍል በተዘጋጀ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የንባብ ክሂልን ለማዳበር የቀረቡ ትምህርቶች አቀራረብ፡ የንባብ ክሂልን ለማዳበር ያላቸው ተገቢነት ምን ያህል ነው?
2. በአራተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የንባብ ክሂል መልመጃዎች የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቃቸውን የንባብ ክሂሎች ከማለማመድ አንፃር ያላቸው አጋዥነት ምን ያህል ነው?

3. እንደ ማስተማሪያ ቋንቋነቱ ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚቀርብ የአማርኛ ንባብ ክሂል ትምህርት ክሂሉን ይበልጥ ለማዳበር እንዴት ቢቀርብ ይሻላል?
4. በአማራጭነት የቀረበው የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ምን ያህል ውጤታማ ነው?

ጥናቱ እነኝህን ጥያቄዎች በመመለስ፥ የትምህርቱ አቀራረብ ክሂሉን ለማዳበር ያለውን ብቃት ለማመልከትና በአማራጭነት የቀረበው የትምህርት አቀራረብ ውጤታማ መሆን አለመሆኑን ለማሳየት ይሞክራል::

1.3 <u>የጥናቱ አስፈላጊነት</u>

በአንደኛ ደረጃ ለመጀመሪያው ሳይክል ተማሪዎች የሚቀርብ የማስተማሪያ ቋንቋ የንባብ ክሂል ትምህርት፥ የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ችሎታ መሠረት ለማስያዝ ቀዳሚ ድርሻ እንዳለው እሙን ነው:: በመሆኑም፥ የትምህርቱ አቀራረብ ብቃት በየወቅቱ መፈተሽና በተሻለ ተገቢና ወቅታዊ አቀራረብ መጠናከር ይኖርበታል:: የትምህርቱን አቀራረብ ማጠናከር፥ የተማሪዎችን አንብቦ የመግንዘብ ችሎታ በማዳበር፥ አጥጋቢ የትምህርት ውጤት እንዲያስመዘግቡ ከማስቻሉ በላይ፥ ለገሀዱ አለም ንባብ (Real life reading) መሠረት ለመጣል ያግዛል::

ከዚህ አንፃር ይህ ጥናት ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰጥ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የሚጠናከርበትን መንገድ ለማመላከት የሚሞክር በመሆኑ የጥናቱ ውጤት

1. የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ለማዳበር የሚያግዝ ተገቢና ውጤታማ የንባብ ክሂል ትምህርት እንዴት መቅረብ እንዳለበት ለመጽሐፍ አዘጋጆችና ለመምህራን መነሻ ሃሣብ መጠቆም፤
2. አማርኛ የማስተማሪያ ቋንቋ በሆነባቸው ክፍሎች ለሚያስተምሩ መምህራንና መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች፥ የትምህርት ይዘቶችን አንብቦ ለመገንዘብ የሚያግዝ የንባብ ክሂል ትምህርት እንዴት መቅረብ እንዳለበት ግንዛቤ በመስጠት፤
3. የሌሎች ክሂሎችን አቀራረብ ተገቢነት ለሚመረምሩና የመማሪያ መጽሐፍትን የክሂሎች አቀራረብ ለማሻሻል ለሚነሱ ጥናቶች መነሻ በመሆን ያገለግላል ተብሎ ይታመናል::

1.4 የጥናቱ ገደብ

ጥናቱ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አዘጋጅነት፣ አማርኛ መማሪያ ቋንቋቸው ለሆኑ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰጥ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ተገቢነትን የሚመለከት ነው። ተገቢነቱ የታየው፣ ለአራተኛ ክፍል የቀረቡ የትምህርት አይነቶች የሚጠይቁትን የንባብ ክሂል ከማዳበር አንፃር ነው። ይሁን እንጅ ሁሉንም የትምህርት አይነቶች በዚህ ጥናት ለማካተት የጥናቱ ጊዜ ባለመፍቀዱ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት በናሙናነት ተወስዷል።

የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫም ለአራተኛ ክፍል የሚሰጥ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ፣ በዚያው ደረጃ የቀረበው የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቀውን የንባብ ክሂል ለማዳበር ያለውን ተገቢነት በመፈተሽ፣ አማራጭ የትምህርት አቀራረብ መንገድ በማቅረብ ውጤታማ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ነው።

በአማራጭነት የቀረበውን የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ውጤታማነት ለመሞከር፣ በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ትምህርት ቤቶችንና ተማሪዎችን በሙሉ ለማካተት የጊዜና የገንዘብ አቅም ስለማይፈቅድ፣ ለመከራው በቂ ክፍለ ጊዜና ተጠኝ ተማሪዎች ማግኘት ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው በጅማ ከተማ የሚገኙ የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው ሳይክል ትምህርት ቤቶች ብቻ የጥናቱ ተተኳሪዎች ሆነው ተመርጠዋል።

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳን

በዚህ ክፍል ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ሥራዎችና ወደ አንድ አጠቃላይ ድምዳሜ ሊያደርሱ የሚያስችሉ ትወራዎችን ለመቃኘት ተሞክሯል::

2.1 የንባብ ግንዛቤዎች

ለንባብ የሚሰጥ ትርጉምና ጽነሰ ሃሣባዊ ግንዛቤ (Conception of Reading) በንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ላይ ተፅእኖ ያሳድራል (May 1990):: የንባብ ግንዛቤ በየጊዜው እየተለወጠ መምጣት፥ ለትምህርት አቀራረብ መለዋወጥና መሻሻል ምክንያት እንደሆነም ይታመናል::

ቀደም ካሉት ጊዜያት ጀምሮ፥ ንባብ ከፍች (Meaning) ጋር በተያያዘ መልኩ ሲገለፅ ቆይቷል (Harrison and Gardner 1977)፤ ይሁን እንጅ ለንባብ ሂደት ያለ ግንዛቤ አንድ አይነት አይደለም::

የመምህራንን የንባብ ግንዛቤ ለመመልከት የተደረጉ ጥናቶችን በመጥቀስ (May 1990:395) "መምህራን ለንባብ ያላቸው ግንዛቤ በሁለት ይከፈላል፤ ከታች ወደላይ (Bottom-up) እና ከላይ ወደታች (Top-Down)::" በማለት ሲገልፁ፥ በተጨማሪም ንባብ መስተጋብራዊ ሂደት (Interactive Process) እንደሆነም ግንዛቤ ተወስዷል (Rlvers 1987)::

የነዚህን የንባብ ሂደት ግንዛቤዎች መሠረት ሃሣብና በንባብ ትምህርት አቀራረብ ላይ ያላቸውን ሥነ-ትምህርታዊ ፋይዳ (Pedagogical Implication) ለማየት እንሞክራለን::

2.1.1. ከታች ወደላይ የንባብ አቀራረብ

ቀደም ባሉት ጊዜያት ንባብ ከዝቅተኛ የጽሑፍ ክፍል (ፊደልና ቃል) ጥናት ጀምሮ፥ ደረጃ በደረጃ ወደ ከፍተኛው የጽሑፍ ክፍል (ሀረግና 0ረፍተ ነገር) ፍች በመሄድ ለንባብ የቀረበውን ጽሑፍ የመረዳት ሂደት ተደርጎ ይታሰብ ነበር (Carrell 1988)::

በዚህ የንባብ ሂደት ግንዛቤ መሠረት፥ አንብቦ ለመረዳት በጽሑፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት በሙሉ ማወቅ እና በትክክለኛ ንበት (Proununcation) ማንበብ አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል፥ አንብቦ የመገንዘብ ችግር የሚፈጠረውም፥ ከተማሪዎቹ የቃላትና የሰዋሰው ችሎታ ማነስ እንደሆነ ይታሰባል። ተማሪዎች ለንባብ በቀረበላቸው ጽሑፍ ውስጥ ላሉት ቃላት እንግዳ ከሆኑ አንብበው መገንዘብ ይቸገራሉ የሚል አመለካከት ይታያል (Carrell 1984)።

ይህን የንባብ ግንዛቤ መሠረት ያደረገ የንባብ ትምህርት አቀራረብ፥ ለንባብ የቀረበው ጽሑፍ የተዋቀረባቸውን ሥነ-ልሳናዊ ክፍሎች በማለማመድ ላይ ያተኩራል (Rivers 1986)። ሥነ-ልሳናዊ የቋንቋ ችሎታ ለውጤታማ ንባብ አስፈላጊ እንደሆነ ብዙ ጥናቶች ስለሚያሳዩ (Williams 1986)፥ ከታች ወደ ላይ የንባብ ሂደት አንብቦ ለመገንዘብ የራሱ የሆነ ቀጠሜታ እንዳለው ይታመናል (Eskey 1988)፥ ነገር ግን አጠቃላይ በሆነ መልኩ ክሂሉን ለማዳበር ያለው እገዛ ዝቀተኛ እንደሆነ በብዙ ምሁራን ዘንድ ይተቻል (Nuttal 1982)።

ከታች ወደ ላይ የንባብ አቀራረብ፥ በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አሰጣጥ ላይ ተዕእኖው ይታያል። ብዙ መምህራን አንብቦ ለመገንዘብ ትክክለኛ ንበት (Prounucation) አስፈላጊ እንደሆነ ግንዛቤ በመውሰዳቸው፥ የንባብ ትምህርቱን ለንበት ማለማመጃ ሲያውሉት ይታያል፥ ምንባቦቹም በመምህሩ ወይም በተማሪዎች ከፍ ባለ ድምፅ አብዛኛውን ጊዜ ይነበባሉ፥ በአቀራረቡ ለንባብ ችግር መፈጠር ምክንያት በተማሪዎች የቃላት እውቀት ማነስ እንደሆነ በመታሰቡ፥ አብዛኛው የንባብ ክፍለ ትምህርት ከምንባብ የወጡ ቃላትን ፍች ለማስተማር ሲያገለግል መታየቱ፥ የንባብ ግንዛቤው ያሳደረው ተዕእኖ ውጤት ሊሆን ይችላል (Nuttal 1982)።

በዚህ መልክ የሚቀርብ የንባብ ትምህርት በቃላት ተናጥላዊ ፍችና የቃል በቃል ትርጉም ላይ ተማሪው እንዲያተኩር ስለሚያደርግ፥ ለአጠቃላይ ግንዛቤ የሚደረግ ንባብን ይገድባል፥ ይህ ደግሞ ለአጠቃላይ ንባብ ችሎታ ዝቀተኛ መሆን ዋነኛ ምክንያት ሊሆን ይችላል (Nuttal 1982)።

2.1.2 ከላይ ወደታች የንባብ አቀራረብ

ከላይ ወደታች የንባብ ሂደት ከአጠቃላይ ግንዛቤ በመነሳት የአንድን ጽሑፍ ሃሳብ የመገንዘብ ሂደትን ይመለከታል፥ በዚህ የንባብ ግንዛቤ፡ ንባብ ከአንባቢው ቀደምት እውቀት በመነሳት ለንባብ የቀረበውን ጽሑፍ የመገንዘብ ሂደት ነው፥ ማንበብ የሚጀምረውም፥ አንባቢው ካካበተው እውቀት ነው (May 1990)።

በዚህ የንባብ ግንዛቤ፥ የአንባቢ ቀደምት እውቀት (Backgraound knowledge) አንብቦ ለመገንዘብ ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል (Carrell 1984)። የንባብ ሂደት አንባቢው ስለሚያነበው ጽሑፍ ያለውን ቀደምት እውቀት ለንባብ ከቀረበው ጽሑፍ ጋር በማስማማት አጠቃላይ ሃሣብን መረዳት መቻል ነው (Wallace 1991)።

ጥሩ አንባቢ ቀደምት እውቀቱን በመጠቀም ለንባብ የቀረበለትን ጽሑፍ ይዘት ቀድሞ ይገምታል፥ በንባብ ሂደት ከጽሑፍ የሚያገኘውን አዲስ ሃሣብ ቀድሞ ከገመተው ጋር ያወዳድራል፤ ይመዝናል በመጨረሻ ያስማማና ይገነዘባል (Grellet 1981, Mei-yun 1997)። ከታች ወደ ላይ የንባብ አቀራረብ በአነኝህ ውጤታማ አንባቢ በሚጠቀምባቸው ስልቶች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ፥ በአቀራረቡ ማስተማር የንባብ ችሎታን ለማዳበር እንደሚያግዝ ይታመናል።

አቀራረቡ ውጤታማ አንባቢ በሚጠቀምባቸው ከፍተኛ የንባብ ስልቶች ላይ ማተኮሩ ለውጤታማ የንባብ ትምህርት ሂደት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ቢታመንም፥ ለጀማሪ ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ የሚያስፈልጉ የንባብ ክሂሎች ላይ ትኩረት ባለመስጠቱ ድክመት እንዳለበት ይተቻል (Eskey 1988)።

2.1.3. <u>መስተጋብራዊ የንባብ ሂደት አቀራረብ</u>

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተቀባይነት እያገኘ የመጣው የንባብ ግንዛቤ፥ ንባብ ከታች ወደ ላይና ከላይ ወደታች የንባብ ስልትን መጠቀም የሚጠይቅ፥ በአንባቢና ለንባብ በቀረበው ጽሑፍ መካከል የሚደረግ መስተጋብራዊ ሂደት (Interactive Process) ነው የሚል ግንዛቤ ነው (Rivers 1987)።

በዚህ የንባብ ግንዛቤ፥ የማንበብ ሂደት ይበልጥ ውጤታማ የሚሆነው አንባቢው ሁለቱንም፥ የቃላት ፍች መለየት /ከታች ወደ ላይ/ (decoding Skills) እና ጽሑፍን የመተርጎም ስልት /ከላይ ወደታች/ (Interpretive Strategies) በማዋሀድ መጠቀም ሲቻል ነው (Eskey 1988, Celce-Murica 1991)።

ውጤታማ አንባቢ ለንባብ በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት ፍች የመለየት (decoding skill) እና ለግንዛቤ የሚያስፈልጉ፡ የመተንበይ የመመዘንና የመተርጎም ስልቶችን (Interpretive Skills) አንብቦ ለመረዳት ይጠቀማል (Grellet 1981, Eskey 1988)። ስለዚህ ተማሪዎችን ውጤታማ አንባቢ እንዲሆኑ ለማገዝ፡ የትምህርት አቀራረባችን በመስተጋብራዊ የንባብ ግንዛቤ ላይ መመስረት የተሻለ ሊሆን ይችላል።

በመስተጋብራዊ የንባብ ሂደት ግንዛቤ፡ ማንበብ የቃላትን ፍችና ሰዋሰዋዊ ሥርዓትን ማወቅ ብቻ የሚጠይቅ ሳይሆን፡ ለንባብ ከቀረበው ጽሑፍ ጋር መስተጋብር መፍጠርንም የሚጠይቅ ነው (Papalia 1987) ተማሪው ለንባብ ከቀረበለት ጽሑፍ ጋር መስተጋብር በመፍጠር አንብቦ የመገንዘብ ችሎታውን እንዲያጎለብት፡ ቀደምት እውቀቱን የመጠቀም ችሎታውና የመተንበይ ክሂሉን (Predictive Skill) እንዲያዳብር ማገዝ ያስፈልጋል። ለዚህ ተገቢ የሆነ የቅድመ ንባብ ክንዋኔዎች በማዘጋጀት ተማሪውን ማሳተፍ ይገባል (Johonson 1982)።

ይህን የንባብ ግንዛቤ መሠረት በማድረግ የሚቀርብ የንባብ ክሂል ትምህርት የሚያተኩረው፡ ግንዛቤን ለማዳበር በሚደረግ የንባብ ሂደት ላይ እንጅ፡ ምን ያህል እነደተገነዘቡ በማወቅ ውጤት ላይ አይደለም (Greenwood 1981)። ለግንዛቤ የማንበብ ሂደት የሚጠይቀውን የንባብ ስልትና ክሂል ለማዳበር የሚያግዝ ወቅታዊና ተቀባይነት ያገኘ የትምህርት አቀራረብ ቅድመ ንባብ፡ በንባብ ወቅትና ድህረ ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተ የትምህርት አቀራረብ እንደሆነ የመስኩ ምሁራን ሲገልፁ፡ በዚህ አቀራረብ ማስተማር የተሻለ ውጤታማ እንደሆነም ይመክራሉ። (Nuttal 1982, Nunan 1989, Grellet 1981)።

2.2 <u>የትምህርት ይዘቶችን አንብቦ ለመገንዘብ የሚያስፈልጉ የንባብ ክሂሎች</u>

ተማሪዎች በደረጃቸው የቀረቡላቸውን የትምህርት ይዘቶች አንብበው መገንዘብ የሚችሉት፡ የትምህርት ይዘቶችን አንብበው ለመገንዘብ የሚያስችል የንባብ ክሂል ችሎታ ሲኖራቸው ነው። የተማሪዎች የትምህርት ውጤት መሳካትና አለመሳካትም የመማሪያ መጽሐፎቻቸውንና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ጽሑፎችን አንብበው ከመገንዘብ ችሎታቸው ጋር የተያያዘ ነው (cushenbery 1985)።

የትምህርት ይዘቶችን አንብበው የመገንዘብ ችሎታቸውን በማሳደግ፡ አጥጋቢ የትምህርት ውጤት እንዲያስመዘግቡ፡ የትምህርት አይነቶቹ የሚጠይቁትን የንባብ ክሂሎች ማስተማር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው (Carin 1997)። ስለዚህ የትምህርት አይነቶች የሚጠይቁትን የንባብ

ክሂሎች መለየትና ለየትምህርቱ አስፈላጊ የሆኑ ክሂሎች ላይ ማተኮር ያስፈልጋል (Harrison and Gardner 1977)::

የትምህርት ይዘቶችን መሠረት ያደረጉ (Content areas) ጽሑፎችን አንብቦ ለመገንዘብ፡ አጠቃላይ ሃሣብን ከዝርዝር ሃሣብ መለየት፡ መመሪያዎችን መረዳት፡ በምክንያትና በውጤት መካከል ያለ ግንኙነትን መገንዘብ፡ ሀቅን ከግል አመለካከት መለየት፡ ካርታዎችን ግራፎችንና ሠንጠረገሮችን ማንበብና መተርጎም የሚያስችሉ የንባብ ክሂሎችን ይጠይቃሉ (May 1990)::

እነኝህ ክሂሎች ለተለያዩ የትምህርት አይነቶች አስፈላጊ ቢሆኑም፡ የተወሰኑት ለአንዳንድ የትምህርት መስኮች ብቻ ይበልጥ የሚያስፈልጉ አሉ:: ለምሳሌ ካርታዎችንና ቻርቶችን ማንበብና መተርጎም ለመልካ ምድር ሳይንስ ትምህርት ይበልጥ አስፈላጊ ሲሆን፡ መመሪያዎችን አንብቦ መከተልና ሙከራዎችን ማካሄድ በሳይንስ ትምህርት አስፈላጊ ነው (Cushenbery 1985)::

እያንዳንዱ የትምህርት መስክ የራሱ የሆኑ ቃላት፡ የአረፍተነገር አወቃቀር፡ ተጠይቃዊ የሃሣብ አደረጃጀትና የሚፈልገው የንባብ ፍጥነት ስላለው፡ ተማሪውን የተለያየ የንባብ ክሂል ይጠይቀዋል (Jarolimek and Foster 1997):: የህብረተሰብ ሳይንስ ትምህርት ዝርዝርና የተወሰኑ መረጃዎችን እንዲገነዘብ፡ የእይታና የአሰሳ (Skimming and Scanning) የንባብ ስልትን፡ ካርታዎችን የማንበብ ክሂልን፡ በጊዜ ቅደም ተከተል የተከናወኑ ታሪካዊ መረጃዎችን የመለየትና የማስታወስ ችሎታን፡ በአብዛኛው ሲጠይቁት፡ የሳይንስ ትምህርት ደግሞ ችግሮችን መለየት፡ ሙከራ ለማካሄድ ጥቃቅን መረጃዎችንና መመሪያዎችን መገንዘብ፡ ሀቅን ከእውነታ መለየት፡ ማጠቃለያ ሃሣብን መፈለግ እና እይታዊ መረጃዎችን የማንበብ ክሂል ይጠይቁታል (Cushenbery 1985):: እንዲህ ማለት ግን የተለያዩ የትምህርት አይነቶች በጋራ የሚጠይቁዋቸው የንባብ ክሂሎች የሉም ማለት አይደለም::

በሁሉም የትምህርት መስኮች አስፈላጊ ከሆኑ የንባብ ክሂሎች መካከል የሚከተሉት ዋንኞቹ እንደሆኑ (Jarolimek and Foster 1997:296, Cushenbery 1985:5) ይገልፃሉ፡ እነሱም

- መረጃዎችን የመፈለግ ስልት
- ግራፎችን፡ ቻርቶችንና ሌሎች ስዕላዊ መረጃዎችን (Pictorial Matrials) ማንበብ፡
- መረጃዎችን አጠቃሎ ለጠቀሜታ በሚውል መልኩ መገንዘብ፡
- ተግባራትን ለመፈፀም መመሪያዎችን መረዳት፡

- አጠቃላይ ሃሣብን መለየትና ዝርዝር መረጃዎችን ማስታወስ፡
- በቅደም ተከተል የተከናወኑ ድርጊቶችን አጠቃሉ መገንዘብ ናቸው::

እነዚህ ክሂሎች በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የተካተቱ የትምህርት አይነቶችን ለመገንዘብ ብቻ ሳይሆን፥ ከትምህርት ቤት ውጭም ማንኛውንም መረጃ ለማግኘት አስፈላጊ ናቸው::

ተማሪዎችን የእነኝህ ክሂሎች ባለቤት ለማድረግ፥ የንባብ ትምህርቱ መለማመጃዎች በትምህርት ይዘቶች ላይ ቢመሠረቱ ጠቀሜታቸው ከፍተኛ እንደሚሆን (Cross 1995) ይገልፃሉ፥ ይሁን እንጅ የትምህርቱ አቀራረብ ለውጤታማ ንባብ የሚያበቁ የንባብ ስልቶችንና ንዑሳን ክሂሎችን ለማዳበር በሚያስችል መልኩ ካልቀረበ ውጤቱ አጥጋቢ ሊሆን አይችልም (Vale and Ann 1995)::

ውጤታማ ንባብ አንድ ጥሩ አንባቢ የሚጠቀማቸውን የንባብ ስልቶችና ንዑሳን ክሂሎች መጠቀም መቻል ነው:: (Mei-yun 1997):: ይህ ማለት የውጤታማ ንባብ ትምህርት አላማ ጥሩ አንባቢ የሚጠቀምባቸውን የንባብ ስልቶች የሚጠቀም ውጤታማ አንባቢ ማፍራት ማለት ነው:: እዚህ ላይ የሚነሳ ጥያቄ፥ ጥሩ አንባቢ እንዴት ነው የሚያነበው፥ የሚል ይሆናል፤ ይህን ጥያቄ መመለስ የትምህርቱን አቀራረብ ለማደራጀት ስለሚያመች፥ በቅድሚያ የውጤታማ አንባቢ ባህርያትን መለየት ያስፈልጋል፤ እኛም ቀጥለን የውጤታማ አንባቢ ባህርያትን ከትምህርት አቀራረብ አንፃር ለመመልከት እንሞክራለን::

2.3 የውጤታማ አንባቢ ባህርያት

ሀ. በአላማ ማንበብ

ጥሩ አንባቢ ለተወሰነ ጉዳይ በአላማ የማንበብ ልምድ አለው፤ አንድን ጽሑፍ የሚያነብበትን ምክንያት (purpose) በቅድሚያ ለይቶ በማወቅ፥ ከሚያነብበት ምክንያት አንፃር የንባብ ስልቱንና ፍጥነቱን በማስማማት ያነባል (Nuttal 1982 Grellet 1981, Ur 1996)::

ውጤታማ ንባብ በአላማ ማንበብን የሚጠይቅ በመሆኑ፥ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ለማነሳሳት የሚያነቡበት ምክንያት በቅድሚያ ማዘጋጀት ይገባል፤ ለዚህም ከንባብ በፊት ተማሪዎቹ የሚሰሯቸው ክንዋኔዎች ማቅረብ አስፈላጊ ይሆናል (Cross 1995, Nuttal 1982)::

ለ. የመገመት ችሎታ

ጥሩ አንባቢ ለንባብ የቀረበውን ጽሑፍ ይዘት ቀድሞ የመገመት ስልት ለግንዛቤ ይጠቀማል። ውጤታማ አንባቢ ስለሚያነበው ጽሑፍ ያለውን እውቀት በመጠቀም ከጽሑፉ በመነሳት ምን ሊያገኝ እንደሚቻል፥ ቀጣዩ ክፍል ምን ሊሆን እንደሚችል ቀድሞ ይገምትና በንባብ ሂደት ከጽሑፉ የሚያገኘውን ሃሣብ ቀድሞ ከገመተው ሃሣብ ጋር በማዋሃድ አጠቃላይ ግንዛቤ ይወስዳል (Grllet 1981)።

ውጤታማ ንባብ አንባቢው ቀድሞ በገመተውና ለንባብ ባቀረበው ጽሑፉ ሃሣብ መካከል ያለ ተዛምዶን የመመልከት ሂደት ነው (Harmer 1991)፤ ስለዚህ የተማሪዎችን አንብቦ የመገንዘብ ችሎታ ለማዳበር የመገመት ክሂላቸውን (Predictive Skill) ማሳደግ ያስፈልጋል። ለዚህም ከንባብ በፊት ተማሪዎች ቀድመው መገመት የሚያስችላቸው ክንዋኔዎች ማቅረብ ያስፈልጋል (Ur 1996)።

ሐ. ቀደምት እውቀትን ለግንዛቤ መጠቀም

ውጤታማ አንባቢ ስለሚያነበው ጽሑፍ ያለውን ቀደምት እውቀት (Backgraund Knowledge) ወደ ጽሑፉ በማምጣት ከጽሑፉ ውስጥ ከሚገኘው አዲስ እውቀትና መረጃ ጋር በማዋሃድ የጽሑፉን መልዕክት ይገነዘባል (Mei yue 1997)።

ውጤታማ የንባብ ሂደት ቀደምት እውቀትን ለንባብ ካቀረበ ጽሑፍ ጋር ማዛመድን የሚሻ ክንውን በመሆኑ (Grellet 1981) ተማሪዎች ያለፈ ልምድና እውቀታቸውን አንብበው ለመገንዘብ የሚያውሉበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት ማለማመድ ያስፈልጋል፤ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ፥ ለንባብ ከቀረበላቸው ጽሑፍ ውስጥ ሊያገኙ የሚችሉትን ሃሣብ ከጽሑፍ ተነስተው እንዲገምቱ የሚያስችል ተግባራት ማቅረብ ከመምህሩ ይጠበቃል (Johnsten 1988)።

መ. የቃላትን ፍች ከአውዳቸው መገንዘብ

ጥሩ አንባቢ ለንባብ በቀረበለት ጽሑፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት ፍች በሙሉ ለማወቅ ሳይጨነቅ ከአውዳዊ አገባባቸው ፍቻቸውን በመገመት አጠቃላይ የጽሑፉን ሃሣብ የመገንዘብ ልምድ አለው። ውጤታማ አንባቢ በንባብ ወቅት የሚያጋጥሙትን እንግዳ ቃላት በሙሉ ለማወቅ በየጊዜው መዝገበ ቃላት በማገላበጥ የንባብ ጊዜውን አያጠፋም። መዝገበ ቃላት

የሚጠቀመው አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ብቻ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ከአገባባቸው ፍቻቸውን በመገመት በትስስር የሚሰጡትን ፍች ለአጠቃላይ ግንዛቤ ያውላል (Ur 1996)።

ለውጤታማ ንባብ ተማሪዎችን ማነቃቃት ያለብን፥ እንግዳ ቃላትን ከአገባባቸው ፍቻቸውን የመገመት ልምድ እንዲያዳብሩ ነው። የትምህርት አቀራረቡም፥ ተማሪውን የቃል በቃል ትርጉም ከመጠየቅ ወይም ከምንባብ የወጡ ቃላትን በተናጠል ፍቻቸውን ከማስጠናት ተቆጥቦ፥ የተለያዩ ፍንጮችን በመስጠት አገባባዊ ፍችን የመስጠት ስልት የሚያለማምድ መሆን አለበት (Grillet 1981)። ይህን ስልት ለማዳበር፥ የቃላትን ፍች ሊገምቱ የሚያስችል ተግባር ከንባብ በፊት ማቅረብ ያግዛል (Nuttal 1982, Ur 1996)።

ሠ. ለግል ንባብ ትኩረት መስጠት

ጥሩ አንባቢ ንባብ በግል የሚከናወን ተግባር መሆኑን ተገንዝቦ ለግሉ የፀጥታ ንባብ (Silent Reading) የማንበብ ልምድና ችሎታ አለው። በግል የፀጥታ ንባብ ማንበብ የንባብ ፍጥነትን ለማሻሻልና ለግንዛቤ ድምፅን ከፍ አድርጎ ከማንበብ (Reading aloud) የበለጠ ውጤታማ እንደሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ (May 1990)። ስለዚህ የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ተማሪውን የፀጥታ ንባብ ማለማመድ ላይ ማተኮር ይገባዋል።

የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ለምን አላማ፥ ምንና እንዴት ማንበብ የተገነዘቡ ውጤታማ አንባቢ ተማሪዎችን ለማፍራት የሚያግዝ በመሆኑ፥ የትምህርቱ አቀራረብ ተማሪዎቹ በመምህሩ ወይም በተማሪዎች ከፍ ባለ ድምፅ የሚነበቡ ምንባቦችን እንዲያዳምጡ ወይም ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ከማድረግ ተቆጥቦ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎቹ ራሳቸው በፀጥታ የሚያነቡበትን ሁኔታ የሚያመቻች መሆን ይገባዋል (Silbersten 1994, Nuttal 1982)።

ረ. ንባብን ከተገቢ የማንበብ ስልትና ፍጥነት ጋር ማስማማት

ውጤታማ አንባቢ ማንኛውንም ጽሑፍ በአንድ አይነት ስልትና ፍጥነት አያነብም፥ ከሚያነብበት አላማ፥ ከጽሑፉ ይዘት፥ ጽሑፉ ከያዘው መረጃ ስፋትና ጥልቀት አንፃር የንባብ ስልቱንና ፍጥነቱን በማጣጣም ያነባል (Cushenbery 1985)።

ማንኛውንም ጽሑፍ በአንድ አይነት ስልትና የንባብ ፍጥነት ማንበብ፡ ጽሑፍን ለመገንዘብና ውጤታማ አንባቢ ለመሆን እንደማያስችል ይታመናል (Harrison and Gardner 1977)። ተማሪዎች ይህን ተገንዝበው ከሚያነቡበት አላማና ከሚያነቡት ጽሑፍ አይነት አንፃር የንባብ ስልትና ፍጥነታቸውን በመለዋወጥ የማንበብ ልምድ እንዲያዳብሩ ማገዝ ያስፈልጋል፡ ለዚህም ከተለያዩ የንባብ ስልትና ፍጥነት ጋር በማስተዋወቅ ማለማመድ ተገቢ ይሆናል (Nuttal 1982, Johnsten 1988)።

ንባብ በአላማ የሚከናወን ተግባር ነው (Cross 1995)፡ ዝርዝር መረጃዎችን ለማግኘት፡ የተወሰኑ መረጃዎችን ብቻ ለማግኘት፡ መመሪያን ተከትሎ አንድ ተግባር ለመፈፀም የግል አመለካከትን ለማስማማት፡ ለአጠቃላይ ግንዛቤ ሊነበብ ይችላል። ለነኝህ የንባብ ምክንያቶች የአነባብ ስልቱ ይለያያል፡ የስልቱ መለያየት ደግሞ የንባብ ፍጥነቱ እንዲለያይ ያስገድዳል (Cushenbery 1985)።

የንባብ ትምህርት አላማ ተማሪውን ጥሩ የማንበብ ስልት እንዲኖረው ከተለያዩ የንባብ ስልት ጋር በማስተዋወቅ ማገዝ ነው (Badrawi 1992)።ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ ተማሪውን ከሚከተሉት የንባብ ስልቶችና ፍጥነቶች ጋር ማስተዋወቅ እንደሚገባ የመስኩ ምሁራን ይገልፃሉ (Nuttal 1982, Cushenbery 1985, Harrson and Gardner 1977, Mei-yun 1997)።

ሀ. <u>የትኩረት ንባብ (Detailed Reading)</u> - እያንዳንዱን ዝርዝርና ጥቃቅን መረጃዎችን በጥንቃቄ በመመልከት ውስብስብ መረጃዎችን ለመገንዘብ የሚደረግ የንባብ ስልት ነው። ይህ ስልት በዝግታ የማንበብ ፍጥነትን የሚጠይቅ ሲሆን በደቂቃ ከ125 ቃላት ባልበለጠ ፍጥነት የሚነበብ ነው (Cushenbery 1985)።

የትኩረት ንባብ፡ የሳይንስ ሙከራዎችን ለማካሄድ፡ እውነታን ከግል አስተያየት ለመለየት፡ በቻርትና በስዕላዊ መግለጫዎች የቀረቡ መረጃዎችን አጠቃሎ ለመገንዘብ፡ የግል አመለካከትን ለንባብ ከቀረበ ጽሑፍ ጋር ለማነፃፀር እና ለመገምገም፡ ለሚደረጉ የንባብ ተግባራት የሚውል ነው።

ተማሪዎች በየዕለቱ በሳይንስ የትምህርት መስክ የሚቀርቡ ጽሑፎችንና የማስተማሪያ መሣሪያዎች የሚይዙትን እጅግ የታመቁ መረጃዎችን ለመረዳትና ሙከራዎችን ለማካሄድ በጥንቃቄና በዝግታ ፍጥነት የማንበብ ተግባር ስለሚያጋጥማቸው፡ የትኩረት ንባብ የሚጠይቁ መልመጃዎች በማቅረብ ማለማመድ ይገባል። መልመጃዎቹም እውነታን የመለየት፡ ለተወሰኑ

የጽንሰ ሃሣብ ጥያቄዎች መልስ የመስጠት፥ በዋናና በዝርዝር ሃሣብ መካከል ያለ እንድነትን ማመልከት፥ መመሪያን ተከትሎ ተግባር የመፈፀም ሊሆኑ ይችላሉ። (Cushenbery 1985)።

ለ. <u>የአሰሳ ንባብ (Scanning)</u> - የተወሰኑ መረጃዎችን ብቻ ለማግኘት የሚደረግ ፈጣን የንባብ ስልት ነው። እንደ ዓመተ ምህረት፥ የቦታና የሰው ስሞች፥ አሃዛዊ መግለጫዎች በፍጥነት በመቃኘት የተፈለገውን መረጃ ለማግኘት የሚደረግ ንባብ ነው።

በዚህ የንባብ ስልት ትኩረት የሚሰጠው በተፈለገው መረጃ ላይ ብቻ በመሆኑ አስፈላጊ ያልሆኑ ዝርዝር ጉዳዮችን በፍጥነት ማለፍን ይጠይቃል። ስለዚህ ተማሪዎችን የአሰሳ ንባብ ለማለማመድ ብዙ መረጃዎችን ለማስታወስ ሳይጨነቁ የተፈለጉ መረጃዎችን ብቻ እንዲፈልጉ ከንባብ በፊት ቀድሞ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፥ ለምሳሌ ብያኔን፥ የቦታ ወይም የሰው ስምን፥ የኬሚካል ስሞች የአየር ንብረት መጠን ለይተው እንዲያሳዩ የሚጠይቁ ክንዋኔዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ሐ. <u>የእይታ ንባብ (Skimming)</u> - ለንባብ የቀረበውን ጽሑፍ አጠቃላይ ሃሣብ ለማግኘት በፍጥነት የሚደረግ ንባብ ነው። የዚህ ንባብ ፍጥነት ከአሰሳ ንባብ ፍጥነት ባነሰ የሚከወን ሲሆን፥ ለንባብ የቀረበውን ጽሑፍ ፈጠን ባለ መልኩ መመልከትን ይሻል።

ተማሪውን የእይታ ንባብ ስልት ለማለማመድ የሚቀርቡ ክንዋኔዎች በተወሰነ የጊዜ ገደብ የሚፈፅምበት ጊዜ ለተማሪው ወስኖ መግለፅ እንደሚገባና በግልና በፀጥታ ንባብ የሚከወን መሆኑን መምህራን መገንዘብ እንዳለባቸው (Cushenbery 1985) ያሳስባሉ።

መ. <u>አውዳዊ ንባብ (Inferring)</u> - ይህ የንባብ ስልት በሚነበበው ጽሑፍ ውስጥ የተካተቱትን ጽንሰ ሃሣቦች ያዘሉ ቃላትና ሀረጎች ከተቀናጁበት አንፃር አገባባዊ ሙያዊ፥ ባህላዊና ተጠይቃዊ ፍንጮችን በመጠቀም በትስስር የሚያስገኙትን መልዕክት ለመገንዘብ የሚያስችል ስልት ነው። ይህን ስልት ተማሪውን ለማስጨበጥ ከአውዳዊ አገባባቸው የቃላትን ፍች መገመት የሚያችሉ መልመጃዎች ማቅረብ የተሻለ ይሆናል።

የንባብ ፍጥነትን በልምምድ ማሻሻል በመቻሉ ሁኔታ ላይ በምሁራን ዘንድ ስምምነት ባይኖርም ተማሪዎችን ከተለያዩ የንባብ ፍጥነቶች ጋር ማስተዋወቅና ማለማመድ ተገቢ ይሆናል (Ur 1996)። ከዚህ አንፃር ተማሪዎችን ከሚከተሉት የንባብ ፍጥነቶች ጋር ማስተዋወቅ እንደሚገባ (Cushenbery 1985, Mei-yun 1997) ይገልፃሉ።

<u>የዝግታ ንባብ</u> - ከ200 - 300 ቃላት (Mei-yun 1997) በደቂቃ የሚነበብ ዝቅተኛው የንባብ ፍጥነት ሲሆን የመማሪያ መፃህፍትንና ውስብስብ መላግብትን አንብቦ ከፍተኛ ግንዛቤ ለማግኘት የሚያስፈልግ ፍጥነት ነው:: (Mei-yun 1997)

<u>መካከለኛ ንባብ ፍጥነት</u> - ከ250 - 500 ቃላት (Mei-yun 1997) በደቂቃ ማንበብን ሲመለከት አንባቢው ለመሠረታዊ ሙያዊ ቃላት፥ ጽነሰ ሃሣቦችና ንዑሳን ርዕሰ ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት ለሚደረግ ንባብ የሚያገለግል የንባብ ፍጥነት ነው:: ይህ የንባብ ፍጥነት አብዛኛው የትምህርት ይዘቶች የሚጠይቁትን የንባብ ክንዋኔ ለመተግበር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ (Cushenbery 1985) ይገልፃሉ::

<u>የፍጥነት ንባብ</u> - የአንድን ጽሑፍ አጠቃላይ ሃሣብ ለማግኘትና የተወሰኑ መረጃዎችን ለመፈለግ የሚደረግ እጅግ ፈጠን ባለ መልኩ የሚነበብ ንባብ ነው::

ከነኝህ የንባብ ፍጥነቶች ጋር ተማሪውን ለማስተዋወቅ የሚከተሉትን ዘዴዎች በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ወቅት መጠቀም እንደሚያግዝ (Nuttal 1982:40) ይጠቅሳሉ::

- አሃዞችን፥ ምህፃረ ቃላትን፥ ስሞችን ፈጠን ባለመልኩ እንዲለዩ ማድረግ፥
- አንድን ጽሑፍ በፍጥነት ቃኝተው የሚመልሱዋቸው የግንዛቤ ጥያቄዎች መስጠት፥
- ስዕላዊ መግለጫዎችን በማቅረብ ከጽሑፍ ይዘት ጋር እንዲያስማሙና እንዲተረጉሙ ማድረግ፥

ከላይ ለመግለፅ የተሞከሩትን የጥሩ ንባብ ሂደት ባህርያት ተማሪውን ለማላበስ የንባብ ትምህርቱ የሚያለማምዳቸው መልመጃዎች ምን መምሰል አለባቸው? ይህን ጥያቄ ቀጥለን ለመመለስ እንሞክራለን::

2.4 <u>የንባብ ክሂልን ለማዳበር የሚቀርቡ መልመጃዎች ባህርይ</u>

አንብቦ የመገንዘብ ችሎታን ለማዳበር ታስበው የሚቀርቡ መልመጃዎች ከቋንቋ ችሎታ መሣኝነት ይልቅ፥ የንባብ ግንዛቤን የማጠናከር ባህርይ ሊታይባቸው ይገባል፥ አላማቸውም፥ ለንባብ የቀረበው ጽሑፍ የተዋቀረበትን የቋንቋ ክፍሎች ማሳወቅ መሆን የለብትም (Nuttal 1982)::

የመልመጃዎቹ አቀራረብ ትኩረት የቋንቋ ችሎታን ለመመዘን ከሆነ፡ የንባብ ችሎታን ለማዳበር የሚኖራቸው እገዛ አነስተኛ ስለሚሆን ትኩረታቸው ለማንዛቤ የማንበብ ሂደት ላይ ሊሆን ይገባል (Greenwood 1981)::

አንብቦ የመገንዘብ ሂደትን ለማጠናከር የሚቀርቡ መልመጃዎችና እንዋኔዎች (ከድህረ ንባብ እንዋኔዎች በስተቀር) ከንባብ በፊት መቅረብ ይገባቸዋል፤ የዚህ ጠቀሜታ፡ ተማሪው የሚያነብበትን ምክንያት ቀድሞ በማስተዋወቅ የማንበብ ፍላጎቱን ለማነሳሳትና የማንበብ ስልቱን ከአላማው አንፃር በማስማማት እንዲያነብ ማስቻል ነው (Grellet 1981, Ur 1996)::

አንብቦ የመገንዘብ ችሎታን ለማዳበር ከሚያግዙ የመልመጃ ጥያቄዎች መካከል የሚከተሉት አይነት ጥያቄዎች ዋንኞቹ እንደሆኑ (Nuttal 1982, Silberstein 1994) ይጠቀማሉ::

ሀ. <u>ቀጥተኛ ምላሽ የሚሹ ጥያቄዎች</u> - ተማሪው ብዙም ሳይጨነቅ፡ ከሚያነበው ጽሑፍ ውስጥ በቀላሉ መልስ ለማግኘት የሚያስችለው ጥያቄዎች ሲሆኑ፡ አመላለሱም በጽሑፍ ውስጥ በቀረበበት መልኩ ይሆናል::

ለ. <u>በራስ አገላለፅ የሚመለሱ ጥያቄዎች</u> - ተማሪው ቃል በቃል ከሚመልስ ይልቅ ለንባብ የቀረበውን ጽሑፍ መልዕክት ሳያዛባ በራሱ ግንዛቤ እንዲገልፅ እድል የሚሰጡ ጥያቄዎች ናቸው::

ሐ. <u>አውዳዊ መልስን የሚጋብዙ ጥያቄዎች</u> - ለንባብ በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ ያሉ እያንዳንዱ ቃል፡ ሀረግና ዐረፍተ ነገር እርስ በርሳቸው ካላቸው ግንኙነት እና ትስስር በመነሳት መልስ መስጠትን የሚጠይቁ ጥያቄዎች ሲሆኑ፡ በያንዳንዱ ትርጉም አዘል አሀድ መካከል ያለን የሃሳብ ቅንጅትና ትስስርን የሚጠይቁ ጥያቄዎችን ይጨምራል::

መ. <u>ግምገማ የሚሹ ጥያቄዎች</u> - የፀሐፊውን ሃሳብ ከራሳቸው አመለካከት አኳያ በመተንተን የሚመለሱ ጥያቄዎችን ይመለከታል:: እነኝህ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ብቻ የሚጋብዙ ሳይሆኑ፡ በመልስነት ያቀረቡትን ሃሳብ በማስረጃ እንዲያጠናክሩ የሚጠይቁም ናቸው::

ሠ. <u>የማስታወስና የማገናዘብ ጥያቄዎች</u> - ለንባብ በቀረበው ጽሑፍ ላይ ብቻ ሳይሆኑ ቀደም ሲል ያነበቡዋቸውን ተዛማጅ ጽሑፎች በማስታወስ፡ በመካከላቸው ያለውን ተዛምዶ አገናዝበው መልስ እንዲሰጡ የሚደራጁ የጥያቄ አይነቶች ናቸው::

በቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት ውስጥ የሚቀርቡ የንባብ መልመጃዎች አንብቦ የመገንዘብ ችሎታን ለማዳበር፥ ብዙ ጊዜ የአማራማሪነት ባህርይ ቢታይባቸው ይመረጣል (Ur 1996)። መልመጃዎቹ ክፍል ውስጥ ሲቀርቡ በሚከተለው መንገድ ቢተገበሩ ጠቀሜታቸው የጎላ እንደሚሆን (Grellet 1981, Nuttal 1982) ይጠቁማሉ።

- ተማሪዎቹ የሚሰሩዋቸው ጥያቄዎችና ክንውኖች መጀመሪያ ከቀረቡ በኋላ፥ ጽሑፉን ደረጃ በደረጃ በፀጥታ እንዲያነቡ ማድረግ፥
- ለቀረቡት ጥያቄዎች በቡድንና በጥንድ ሆነው መልስ እንዲሰጡ ማበረታታት፥
- የየቡድኑን መልስ ከነምክንያታቸው ለክፍሉ እንዲቀርቡ ማድረግ፥
- በመጨረሻም የክፍሉን ተማሪዎች በሙሉ የሚያሳትፍ ውይይት ማካሄድና አጠቃላይ እርማት ለክፍሉ መስጠት።

ተማሪዎቹ መልመጃዎቹን በሚሰሩበት ወቅት በተገቢው መንገድ መሰራታቸውን መምህሩ መከታተልና እያንዳንዱ ተማሪ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና መርዳት ይጠበቅበታል። 18

2.5 ውጤታማ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ

ውጤታማ ንባብ Goodman ባቀረቡት የሥነ-ልቦናዊ ሥነ-ልሳን የንባብ ጽነሰ ሃሣብን መሠረት ያደረገ መሆን እንዳለበት (Mei-yun 1997) ይገልፃሉ። እንደ (Goodman 1967) ንባብ የሥነ-ልቦናዊ ሥነ-ልሳን የመተንበይ ሂደት (A Psycholinguistic guessing game) ነው። የንባብ ሂደትም በቋንቋና በእሳቤ መካከል ያለ የመገመት፥ የመምረጥ፥ የመመዘን፥ የማዋሃድ እና የመተርጎም ዑደታዊ ሂደት እንደሆነ (Mei-yun 1997:180, Goodman 1982) ን በመጥቀስ ይገልፃሉ።

ይህን የሥነ-ልቦናዊ ሥነ-ልሳን የንባብ ግንዛቤ መሠረት በማድረግ የትምህርት አቀራረብን ማደራጀት ውጤታማ ሊያደርግ እንደሚችል ይታመናል። ምክንያቱም በምዕራፍ 2.3 ላይ ለማመልከት እንደሞከርነው፥ ጥሩ አንባቢ ለንባብ ከቀረበለት ጽሑፍ በመነሳት የጽሑፉን ይዘት የመገመት፥ በንባብ ሂደት ያገኘውን ሃሣብ የመመዘንና ከግምቱ ጋር በማዋሃድ የጽሑፉን አጠቃላይ ፍሬ ሃሣብ የመገንዘብ ባህርይ ስላለው፥ ግንዛቤውን መሠረት ማድረግ የጥሩ አንባቢ ባህርይን ለማላበስ ስለሚያስችል ነው።

የውጤታማ ንባብ ትምህርት አላማ ጥሩ አንባቢ የሚጠቀምባቸውን የማንበብ ስልቶችና ንዑሳን ክሂሎችን መጠቀም የሚችል ውጤታማ አንባቢ ተማሪ ማፍራት በመሆኑ (Mei-yun 1997) የተማሪዎችን አንብቦ የመገንዘብ ችሎታ ለማዳበር የሚያግዝ የትምህርት አቀራረብ የጥሩ አንባቢ ባህርያትን መርህ ሊያደርግ ይገባዋል::

በምዕራፍ 2.3 ላይ የተጠቀሱት የጥሩ አንባቢ ባህርያት (በምክንያት ማንበብ፣ የመገመት ስልትን መጠቀም፣ ያለፈ እውቀትን ለማንዛቢ ማዋል እና ንዑሳን ክሂሎችን የመጠቀም ችሎታ)፣ ለንባብ ትምህርት አቀራረብ ሥነ-ትምህርታዊ ፋይዳ እንዳላቸው (Harmer 1991) ያመለክታሉ::

ውጤታማ አንባቢ የሚጠቀምባቸውን የንባብ ስልቶችና ንዑሳን ክሂሎች መጠቀም የሚችል ውጤታማ አንባቢ ለማፍራት፣ ወቅታዊና ተቀባይነት ያገኘ የትምህርት አቀራረብ ቅድመ-ንባብ (Pre-reading)፣ በንባብ ወቅት (While-reading) እና ድህረ-ንባብ (Post-reading) ክንውኖችን ያካተተ ሦስት የክንዋኔ ደረጃዎች ያሉት የትምህርት አቀራረብ እንደሆነ (Grellet 1981, Nuttal 1982, Grant 1987, Ur 1996) እና ሌሎችም የመስኩ ምሁራን ያመለክታሉ::

የቅድመ-ንባብ ደረጃ ክንዋኔዎች (Pre-reading Activites) አላማ፣ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ለማነሳሳት፣ ቀደምት እውቀታቸውን ከጽሑፉ ይዘት ጋር ለማስተሳሰርና የምንባቡን ፍሬ ሃሣብ እንዲገምቱ ለማስቻል ነው (Grellet 1981, Ur 1996)::

በንባብ ወቅት ደረጃ የሚቀርቡ ክንዋኔዎች አላማ የፀሐፊውን ሃሣብ፣ የጽሑፉን አደረጃጀትና ይዘት ተማሪዎች መገንዘብ እንዲችሉ ማገዝ ሲሆን፣ የድህረ ንባብ ክንዋኔዎች አላማ ደግሞ አጠቃላይ የምንባቡን ሃሣብ የመረዳት ሁኔታን ለማረጋገጥ፣ የጽሑፉን ሃሣብ ተማሪዎቹ ከግል ህይወታቸውና እውቀታቸው ጋር በማዋሃድ ለሌላ ተግባር መጠቀም ለማስቻል ነው (Grellet 1981, Nuttal 1982)::

በነኝህ ደረጃዎች የንባብ ክሂልን ለማዳበር የሚቀርቡ ክንውኖች ምንነት (Grellet 1981, Nuttal 1982, Williams 1984, Harmer 1991, Ur 1996) ካቀረባቸው ሃሣቦች በመነሳት በክፍል ውስጥ የሚቀርቡበትን የአቀራረብ ሂደት እንመልከት፣

I. ቅድመ-ንባብ ደረጃ ክንውኖች (Pre-reading activities)

ሀ. መግቢያ

በዚህ ክፍል መምህሩ በቅድሚያ የምንባቡን ርዕስ ለተማሪዎች ያስተዋውቃል፤ በትውውቅ ጊዜ አራት ተግባራትን እንዲያከናውን ይጠበቃል፤

1. ተማሪዎቹ ምንባቡን የሚያነቡበትን ምክንያት በማቅረብ የማንበብ ፍላጎታቸውን ያነሳሳል።
2. ለንባብ በቀረበው ምንባብ ርዕስ ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ የሚጠይቁ መነሻ ጥያቄዎች በማቅረብ ቀደምት እውቀታቸውን ከምንባቡ ይዘት ጋር እንዲያስተሳስሩ ያነቃቃል፤
3. የምንባቡ ይዘት ስለምን ጉዳይ ሊሆን እንደሚችል እንዲገምቱ ያደርጋል፤ ይህን ለማድረግ ተማሪዎችን በቡድንና በጥንድ በማድረግ ምንባቡ ሊመልሳቸው የሚችሉ ጥያቄዎችን ያቀርባል፤ ወይም በምንባቡ ውስጥ ሊነሱ የሚችሉ ሃሣቦችን እንዲሰነዝሩ ያደርጋል፤ የተማሪዎቹን መልስ ለውይይት በማቅረብ ክፍሉን ያወያያል፤
4. የተማሪዎቹን የንባብ ሂደት ሊያደናቅፉ የሚችሉ ቁልፍ ቃላትን ለትምህርት ያቀርባል፤

ለ. የምንባቡን አጠቃላይ ሃሣብ ለማግኘት የመጀመሪያ የንባብ ክንዋኔ ያቀርባል፤

- ተማሪዎቹ በምንባብ ውስጥ የቀረቡት ሃሣቦች ስለምን ጉዳይ እንደሚገልፁ እንዲገነዘቡ፥ አጠቃላይ ሃሣብን የሚጠይቁ ጥያቄዎች ያቀርባል፤ ጥያቄዎቹ ዝርዝር ጉዳዮችን መረዳት ሳያስፈልጋቸው ሊመልሱዋቸው የሚችሉዋቸው ይሆናሉ።

ከነዚህ ክንዋኔዎች በኋላ ወደ ንባብ ወቅት የክንዋኔ ደረጃ ያሸጋግራቸዋል።

II. የንባብ ወቅት ደረጃ ክንዋኔዎች (While reading activities)

ሀ. የምንባቡን አጠቃላይ ሃሣብ ለማግኘት የመጀመሪያ ደረጃ የዝምታ ንባብ ያስነብባል፡

- በቅድመ ንባብ ደረጃ የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ የእይታ (Skimming) ፍጥነት ንባብ ተማሪዎቹ ያነባሉ፡
- መምህሩ ደቂቃዎችን ወስኖ በመስጠት በዚያ ደቂቃ ውስጥ አጠቃላይ ሃሣቡን ለማግኘት የፍጥነት ንባብ እንዲያካሂዱ ያበረታታል

ለ. ምጋቤ ምላሽ (Feed-back)

- ተማሪዎቹ የመለሷቸው መልሶች ትክክለኛ መሆናቸውን እንዲያረጋግጡ በመልሶቻቸው ላይ ያወያያል፡
- ከውይይቱ በኋላ መምህሩ አጠቃላይ እርማት ለክፍሉ ተማሪዎች ይሰጣል::

ሐ. ዝርዝር ጉዳዮችን ለመግንዘብ ሁለተኛ ደረጃ የፀጥታ ንባብ ያስነብባል፡

- ተማሪዎቹ ዝርዝር ጉዳዮችን ለመረዳት በዝግታ የፀጥታ ንባብ ያካሂዳሉ፡ ለጥያቄዎቹ መልስ ይሰጣሉ፡ የቀረቡላቸውን ክንውኖች ይተገብራሉ::
- መምህሩ ክንውኖቹ በአግባቡ መፈፀማቸውን ይከታተላል::

መ. ምጋቤ ምላሽ

- ተማሪዎቹ መልሶቻቸውን በቡድንና በጥንድ በመሆን ያስተያያሉ፡
- ወደ ምንባቡ በመመለስ መልሳቸውን ያረጋግጣሉ፡
- በክፍል ደረጃ በመልሶቻቸው ላይ እንዲወያዩ መምህሩ ያደርግና አጠቃላይ እርማት ለክፍሉ በመምህሩ ይሰጣል::

III. ድህረ-ንባብ ደረጃ ክንዋኔ (Post-reading activities)

ሀ. ከንባብ በኋላ መምህሩ

- አጠቃላይ ምንባቡን የመገንዘብ ሁኔታዎችን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን፡
- ምንባቡን እንዲገመግሙ የሚያበረታቱ ተግባራትን፡
- ከራሳቸው ልምድ ጋር የምንባቡን ሃሣብ እንዲያዛምዱና እንዲያገናኙ የሚያግዙ ክንዋኔዎችን ያቀርባል::

ለ. ተጨማሪ ክንውኖች ያቀርባል

- ሌሎች የክሂል ዘርፎችን በቅንጅት መጠቀም የሚያስችላቸው ተግባራትን ያዘጋጃል፤
- በምንባቡ መነሻነት ድርሰት እንዲፅፉ፥ ለመምህራኖቻቸው ቃለመጠይቅ በማድረግ ወይም መጽሐፍት በማንበብ ንግግር እንዲያዘጋጅ፥ ሪፖርት እንዲፅፉ የሚጋብዙ ተግባራት ይሰጣል።

ምዕራፍ ሦስት

የጥናቱ ዘዴዎች

ጥናቱ ገላጭ (Descriptive) እና ሙከራዊ (Experimental) የምርምር ስልቶችን መሠረት በማድረግ፥ የሚከተሉትን የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችንና የአጠናን ስልቶችን በመጠቀም የተከናወነ ነው።

3.1 የጥናቱ አካሄድ (Procedure)

ጥናቱ አላማውን ከግብ ለማድረስ የተከተለው አካሄድ፥ ለአራተኛ ክፍል የቀረበ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ፥ በደረጃው የቀረበው የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቀውን የንባብ ክሂል ለማዳበር ያለውን ብቃትና አጋዥነት በመገምገም፥ አማራጭ የትምህርት አቀራረብ መሞከርና ውጤታማነቱን ማረጋገጥ ነው።

በመጀመሪያ ለአራተኛ ክፍል የቀረበው የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት አቀራረብ የንባብ ክሂል ለማዳበር ያለውን ተገቢነት ለመፈተሽ፥ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የንባብ ትምህርቶች አቀራረብ ከተዘረዘሩ በኋላ በመስኩ የተሰማሩ ምሁራን ባቀረቧቸው ውጤታማ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ትወራዎች አንፃር ለመገምገም ተሞክሯል።

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የንባብ መልመጃዎች በደረጃው የቀረበው የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቀውን የንባብ ክሂል በማለማመድ በኩል ያላቸውን አጋዥነት ለመመልከት፥ በየመጽሐፍቱ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች የሚጠይቋቸው የንባብ ክንዋኔዎች ከተተነተኑ በኋላ ንፅፅራዊ ምልከታ ተካሂዷል።

በተጨማሪም የመምህራኑን የክፍል ውስጥ የትምህርት አቀራረብ ለመቃኘት፥ ከአራተኛ ክፍል መምህራን በጽሑፋዊ መጠይቅ የማስተማር ልምዳቸውን በተመለከተ መረጃ ተሰብስቧል።

በዚህ መልክ የትምህርቱ አቀራረብ የብቃት ደረጃ ከታየ በኋላ፥ ቅድመ-ንባብ፥ በንባብ ወቅትና ድህረ-ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተ፥ ወቅታዊና በውጤታማነቱ ተቀባይነትን ያገኘ አማራጭ የትምህርት አቀራረብ በማዘጋጀት ውጤታማነቱን ለመፈተሽ ተሞክሯል።

በአማራጭነት የቀረበውን የትምህርት አቀራረብ ውጤታማነቱን ለመፈተሽ፥ በአጋጣሚ ናሙና የሚመረጡ የክትትል ቡድንና የመከራ ቡድን ቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና (Randomized Control and Experimental Group Pre test-Posttest) ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል።

ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት፥ በተማሪዎች ዳራዊ እውቀት፥ በጊዜ፥ በትምህርት አሰጣጥ፥ በመማር ሁኔታዎች አንፃር የሚፈጠሩ ተሳውጠዎችን መቆጣጠር የሚያስችል በመሆኑ ነው።

መከራውን ለማካሄድ፥ በናሙናነት በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚገኙ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል የሁለት ክፍል ተማሪዎች በእጣ ተመርጠው አንደኛው ለመከራ ሌላው ለክትትል ቡድን በእጣ ተመድበዋል።

ለክትትልና ለመከራ ቡድን ተማሪዎች፥ የንባብ ችሎታቸው በተመሳሳይ ደረጃ ላይ መገኘቱን ለመመልከትና ለመከራው መነሻ እንዲሆን ከልምምዱ በፊት የቅድመ-ልምምድ ፈተና ተዘጋጅቶ ተሰጥቷል።

የፈተናው ውጤት በሦስት መምህራን ታርሞ ከተመዘገበ በኋላ፥ ለመከራ ቡድኑ ተማሪዎች በአማራጭነት በተዘጋጀው የትምህርት አቀራረብ፥ ለክትትል ቡድኑ ደግሞ በመማሪያ መጽሐፋቸው ውስጥ በቀረበው መልክ ለስድስት ሳምንት (ለ30 ክፍለ ጊዜያት) በአጥኚው ትምህርት ከተሰጠ በኋላ፥ ለሁለቱም ቡድኖች የድህረ-ልምምድ ፈተና ተዘጋጅቶ ተሰጥቷል።

ፈተናው በሦስት መምህራን ታርሞ ውጤቱ ከተመዘገበ በኋላ በሁለቱ ፈተናዎች መካከል የታየው ልዩነት በ "ቲ" ስሌት (T-test) ተፈትሾ በተገቢው ስታትስቲካዊ መንገድ ለመተንተን ተሞክሯል።

3.2 <u>የናሙና አመራረጥ</u>

ጥናቱ በኦሮሚያ ክልል አማርኛ መማሪያ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች የሚሰጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ተገቢነትን ለመመልከት የታሰበ ቢሆንም፥ ከጊዜ፥ ከገንዘብና ከቁሳቁስ ማነስ የተነሳ፥ ሁሉንም የኦሮሚያ አካባቢዎች በጥናቱ ማካተት አልተቻለም፤ ስለዚህ በጅማ ከተማ የሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ የጥናቱ ተተኳሪዎች እንዲሆኑ ተመርጠዋል።

በጅማ ከተማ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች የተመረጡበት ምክንያት፡ ጥናቱን ለማካሄድ በቂ ተጠኝ ተማሪዎችንና የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለማግኘት አመቺ እንደሆኑ በመታመኑ የምቾት ናሙና (Convenience Sampling) ዘዴን በመጠቀም ነው።

በጅማ ከተማ ከሚገኙ 12 የመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል ስድስት ትምህርት ቤቶች በተራ እጣ ናሙና (Random Sampling) ዘዴ ተመርጠው፡ በነኝህ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአራተኛ ክፍል መምህራን መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል።

ከስድስቱ ትምህርት ቤቶች መካከል፡ አንድ ትምህርት ቤት (የመንደራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ሙከራውን ለማካሄድ በእጣ ተመርጧል። ሙከራው በአንድ ትምህርት ቤት ብቻ እንዲደረግ የተፈለገው የትምህርት ቤቶች አደረጃጀት፡ የመምህራንና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ልዩነት በተማሪዎች የንባብ ችሎታ ላይ ልዩነት ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ስለታሰበ ነው።

ሙከራውን ለማካሄድ በተመረጠው የመንደራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚገኙ ስድስት የአራተኛ ክፍሎች መካከል፡ የ4ኛ "ሀ" ክፍል ተማሪዎች ለሙከራ ቡድን፡ የ4ኛ "መ" ተማሪዎች ደግሞ ለክትትል ቡድን በእጣ ተመድበዋል።

ጥናቱ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርትን በናሙናነት የወሰደው፡ በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት ቀድሞ በሳይንስ፡ በታሪክ፡ በጅኦግራፊ፡ በእርሻና በባልትና ሳይንስ የትምህርት ዘርፎች ይቀርቡ የነበሩ ይዘቶች ተጠቃለው በአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ሥር መቅረባቸው፡ የንባብ ክሂል ትምህርቱን አቀራረብ ተገቢነት ከዚህ ትምህርት አንባር ማየቱ አጠቃላይ ገፅታውን ማሳየት ያስችላል ከሚል ግምት ነው።

3.3 <u>የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች</u>

ጥናቱ ለመረጃ መሰብሰቢያ የተጠቀመባቸው መሣሪያዎች የጽሑፍ መጠይቅ ግምገማና ፈተናዎችን ነው።

<u>የጽሑፍ መጠይቅ</u> - ከተዛማጅ ጽሑፎች የተገኙ ጭብጦችን መሠረት በማድረግ የንባብ ትምህርት አቀራረብን፥ የመምህራንን የማስተማር ልምድና የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ የሚመለከቱ ዝግና ክፍት ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ለናሙና በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚያስተምሩ የአራተኛ ክፍል መምህራን ተሞልተዋል::

መጠይቆቹ ለመምህራኑ ከመቅረባቸው በፊት፥ በሁለት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን፥ በሦስት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ታይተው ማሻሻያ ከተደረገባቸው በኋላ በአሰሳ ጥናት (Pilot Study) ለ10 መምህራን ቀርበው ተሞክረዋል::

<u>ፈተና</u> - በአማራጭነት የቀረበውን የትምህርት አቀራረብ ለመሞከርና ውጤታማነቱን ለመፈተሽ የቅድመ እና የድህረ ልምምድ ፈተናዎች ተዘጋጅተው ለሙከራና ለክትትል ቡድን ተማሪዎች ተሰጥተዋል::

ፈተናዎቹ ለተማሪዎች ከመሰጠታቸው በፊት በአንድ የብሔራዊ ፈተና ድርጅት የአማርኛ ፈተና ባለሙያ፥ በሁለት የኮሌጅ መምህራንና በሁለት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ተገምግመው ማሻሻያ ከተደረገባቸው በኋላ በአሰሳ ጥናት (Pilot Study) ለአስር የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ተሰጥተው የተማሪዎቹን ደረጃ የሚመጥኑና ለጥናቱ አላማ ተገቢ መሆናቸው ተፈትሿል::

<u>ግምገማ</u> - በአሮሚያ ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ መማሪያ እንዲሆን የቀረበው መጽሐፍ የንባብ ትምህርት አቀራረብ የንባብ ክሂልን ለማዳበር ያለው ተገቢነት ተገምግሟል:: ተገቢነቱ የተገመገመው ከውጤታማና ወቅታዊ የትምህርት አቀራረብ ትወራ አንፃር ነው::

ምዕራፍ አራት

የመረጃዎች ውጤትና ትንተና

ለጥናቱ የተመረጡትን የአሰራርና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም የተሰበሰቡ መረጃዎች ለጥናቱ በሚያመች መልኩ ተተንትነውና ተተርጉመው በዚህ ክፍል ቀርበዋል::

4.1. ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰጥ የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ግምገማ

4.1.1 በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የንባብ ክሂል ትምህርቶች አቀራረብ፥ ክሂሉን ለማዳበር ያላቸው ብቃት

በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፥ አማርኛ መማሪያ ቋንቋቸው ለሆኑ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ 24 ምንባቦች ቀርበዋል:: ምንባቦቹ ግብርና፥ ጤና፥ የአካባቢ ጥበቃ፥ የቤትና የዱር እንስሳት እክብካቤ፥ የምግብ ክፍሎች፥ የደብዳቤ አፃፃፍና ማህበራዊ ጉዳዮችን ያካተቱ ናቸው::

መማሪያ መጽሐፉ ከያንዳንዱ ምንባብ ቀጥሎ መልመጃ አንድ፥ ሁለትና ሦስት በሚል መልኩ የተደራጁ የመለማመጃ ጥያቄዎችን ያቀርባል:: የተለያዩ መመሪያዎችና ማስታዎሻዎችንም አካቷል::

በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች በሙሉ የንባብ ክሂልን ብቻ ለማዳበር የቀረቡ ናቸው ብሎ መገመት አስቸጋሪ ቢሆንም፥ መልመጃ አንድና ሁለት ይበልጥ የንባብ ክሂልን ለማዳበር የቀረቡ ናቸው ማለት የሚቻል ይመስላል:: ምክንያቱም፥ የመልመጃዎቹ ትዕዛዞች በአብዛኛው፥ በምንባቡ መሠረት መልሱ፥ ቀጥለው ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች ቀርበዋል፥ በምንባቡ መሠረት እውነት ሀሰት በማለት መልሱ፥ ቀጥለው ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች በምንባቡ መሰረት ስጡ የሚሉ በመሆናቸው ነው::

በአራተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የንባብ ትምህርቶች የቀረቡበት መንገድ፥ ከምንባብ በኋላ ከምንባብ የወጡ የቃላትና የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ነው:: የዚህ አይነት አቀራረብ አሰልቺና ዘልማዳዊ በመሆኑ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ከመግታቱም

በላይ የቃላትና የግንዛቤ ፈተና እንጅ፥ ማስተማር እንዳልሆነ በብዙ የመስኩ ምሁራን ሲተች ቆይቷል (Nuttal 1982, Grellet 1981)።

በምዕራፍ ሁለት ለማመልከት እንደተሞከረው፥ ጥሩ የንባብ ትምህርት ማተኮር ያለበት ግንዛቤን ለማዳበር በሚደረግ የንባብ ሂደት ላይ እንጅ፥ ተማሪው ምን ያህል እንደተገነዘበ በመመዘን ላይ መሆን የለበትም (Greenwood 1981)፤ አንብቦ የመገንዘብ ችሎታን ለማዳበር የትምህርቱ አቀራረብ ተማሪው የሚፈፅማቸው ተግባራትን (ከድህረ-ንባብ እንዋኔ በስተቀር) ከንባብ በፊት በማቅረብ ተማሪውን የሚያሳትፍ ሊሆን ይገባል። ይህ ተማሪው የሚያነብበትን ምክንያት ቀድሞ እንዲያውቅ እና የንባብ ስልቱንና ፍጥነቱን እንዲያስተካክል ያግዘዋል።

የአራተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የትምህርት አቀራረብ ትኩረት ግን የተማሪውን የቃላትና የግንዛቤ ችሎታ መመዘን በመሆኑ፥ ተማሪው የሚያነብበትን ምክንያት አውቆ የንባብ ስልቱን አስማምቶ እንዲያነብ የሚያዘጋጁት እንዋኔዎች የሉትም። ይህ ደግሞ ለግንዛቤ የማንበብ ችሎታው ዝቅተኛ እንዲሆን ምክንያት ሊሆን ይችላል።

ቀደምት ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፥ የተማሪዎች አንብቦ የመገንዘብ ችሎታ ዝቅተኛ እንዲሆን ምክንያት ከሆኑ ጉዳዮች መካከል፥ የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ በአላማ የማያስነብብ መሆኑ አንዱ ነው። በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ ትምህርቶችም፥ ተማሪው ለምንና እንዴት ማንበብ እንዳለበት የሚያሳውቁ እንዋኔዎችን ስላልያዙ የተማሪውን የማንበብ ፍላጎት በማነሳሳት ለንባብ የሚያዘጋጁ አይደሉም፤ የዚህ ድምር ውጤት በተማሪው የንባብ ችሎታ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚያሳድር ይታመናል።

ለምንና እንዴት ማንበብ የሚችሉ ውጤታማ አንባቢ ተማሪዎችን ለማፍራት የሚያግዝ የንባብ ትምህርት አቀራረብ፥ ተማሪውን ከቀረበለት ምንባብ ጋር መስተጋብር ሊፈጥር የሚያስችሉት ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ የቅድመ-ንባብ፥ የንባብ-ወቅትና የድህረ ንባብ እንዋኔዎችን ያካተተ ሊሆን እንደሚገባ በምዕራፍ ሁለት ለማሳየት ሞክረናል። ተማሪው ከቀረበለት ምንባብ ጋር መስተጋብር በመፍጠር አንብቦ የመገንዘብ ችሎታቸውን እንዲያዳብር በቅድሚያ ቀደምት እውቀቱን ወደ ምንባቡ በማምጣት የቀረበለትን ዕሑፍ ይዘት የመተንበይ ችሎታውን ማዳበር የሚያስችሉ እንዋኔዎች ሊቀርቡለት ይገባል። በንባብ ወቅት የሚያከናውናቸው ተግባራትም ቀድመው ቀርበውለት የሚያነብበትን ስልትና ፍጥነት ሊለዩለት ይገባል።

ከዚህ አንባር የመማሪያ መጽሐፉን አቀራረብ ስንመለከት፥ የቅድመ-ንባብ እና የንባብ-ወቅት ክንዋኔዎች ጨርሶ የሌሉት ሲሆን፥ በመልመጃ ሦስት ስር የቀረቡ ጥያቄዎች በመጠኑ የድህረ ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተቱ ይመስላሉ። ይሁን እንጅ በዚህ መልመጃ ሥር የቀረቡት ጥያቄዎች አብዛኛዎቹ በቅድመ-ንባብ ክንዋኔ ሥር መቅረብ የሚገባቸው እንደሆኑ ይታያል። ለአብነት ያህል ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች እንመልከት፥

- የግል ንፅህና ለምን ያስፈልጋል ተነጋገሩበት? (ገፅ 24)
- ከቋቁቻ ጋር የሚመሳሰሉ የምታውቃቸውን የቆዳ በሽታዎች ስም ግለፁ? (ገፅ 78)
- በዱር እንስሳትና በቤት እንስሳት መካከል ያለው ልዩነት ምን ይመስላችኋል ተነጋገሩበት? (ገፅ 60)

እነኝህ ጥያቄዎች በምንባቡ ውስጥ የሚነሱ ወይምን ምንባቡ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ስለሆኑ፥ ተማሪው ምንባቡን ከማንበቡ በፊት ቢቀርብለት፥ ቀደምት እውቀቱን ከምንባቡ ሃሣብ ጋር እንዲያዛምድና ይዘቱን እንዲገምት የሚያስችሉት ይሆኑ ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የንባብ ክሂል ትምህርቶች በአብዛኛው የቃላትና የሰዋሰው ማስተማሪያ በመሆን እያገለገሉ ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡ መልመጃዎች መካከል ስልሳ ሁለቱ ለዚሁ ተግባር ውለዋል። አርባ ሁለት መልመጃዎች የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች እና ዐረፍተ ነገር መመስረትን ሲጠይቁ፥ ሃያዎቹ፤ ደግሞ የቃላት ርባታ፥ ምስረታና የአረፍተ ነገር ስርዓት ያለማምዳሉ። ከዚህ ቁጥር መገንዘብ የሚቻለው ትምህርቱ ቃላትንና ሰዋሰውን ለማስተማር በአብዛኛው ያገለገለ መሆኑን ነው።

የተማሪው የቋንቋ ችሎታ ካልዳበረ፥ አንብቦ የመገንዘብ ችሎታው ሊዳብር እንደማይችል አያጠያይቅም፤ ይሁን እንጅ፥ የንባብ ክፍለ ትምህርቱ ዋነኛ ትኩረት ለዚህ ተግባር ከሆነ፥ ዋናው ጉዳይ ተዘንግቶ ለተጓዳኝ ጉዳዮች ትኩረት እንደመስጠት ሊቆጠር ይችላል። ምክንያቱም የንባብ ትምህርት ዋና ትኩረት ቃላትና ሰዋሰውን ማስተማር ሳይሆን የንባብ ስልቶችን ማለማመድ በመሆኑና አንብቦ ለመገንዘብ የቃላት ፍች በሙሉ ማወቅ የግድ አስፈላጊ ስላልሆነ ነው (Ur 1996, Silberstein 1994)።

በምዕራፍ ሁለት ለማየት እንደሞከርነው፥ ተገቢ የንባብ ትምህርት አቀራረብ የተማሪውን የማንበብ ሂደት ሊያደናቅፉ የሚችሉ ቁልፍ ቃላትና ሰዋሰዋዊ ክፍሎች ሲኖሩ፥ ምንባቡን ለመገንዘብ እንዲያግዙ ከንባብ በፊት በማቅረብ ያስተዋውቃል፤ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ግን

የቃላትና የሰዋሰው ትምህርት ከምንባቡ በኋላ የቀረቡ በመሆናቸው ተማሪው የቀረበለትን ምንባብ በሚያነብበት ወቅት ለማንዛቢ የሚያግዙት አይሆኑም::

ውጤታማ ንባብ ለንባብ በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት ከአገባባቸው ፍቻቸውን በመገመት በትስስር የሚያስገኙትን መልዕክት መገንዘብን የሚጠይቅ በመሆኑ፥ ተማሪዎቻችንን ማነቃቃት ያለብን ቃላትን ከአውዳዊ አገባባቸው የመገመት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ መሆን አለበት እንጅ በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በቀረበው መልክ የቃል በቃል ትርጉም በመጠየቅ መሆን የለበትም:: የትምህርት አቀራረባችን አንብቦ የመገንዘብ ችሎታን ለማዳበር እንዲያግዝ፥ የተለያዩ ፍንጮችን በመስጠት አገባባዊ ፍቺ የመገመት ስልትን የሚያለማምድ መሆን አለበት (Grellet 1981)::

ከዚህ አንፃር በአራተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች የቀረቡበት መንገድ በአብዛኛው የቃላትን ትርጉም ከአገባባቸው መገመት የሚያስችል ባለመሆኑ፥ ተማሪውን ለውጤታማ አንባቢነት ለማብቃት የሚኖረው እገዛ ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል::

በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የጥያቄ አይነቶችን ስንመለከት፥ አብዛኛዎቹ ተማሪውን እውነት ሀሰት እንዲል፥ እንዲመርጥና እንዲያዛምድ የሚጠይቁ ናቸው:: እነዚህ የጥያቄ አይነቶች ደግሞ የተማሪውን የማንበብ ጥረት የሚያጎለብቱና ለንባብ የሚያነቃቁ አይደሉም::

በመስኩ የተሰማሩ ምሁራን (Nuttal 1982, Silberstein 1994) የጠቆሙዋቸው የውጤታማ ንባብ ትምህርት መልመጃዎች (በራስ አገላለፅ የሚመለሱ፥ አውዳዊ መልስ የሚሹ፥ ግምገማን የሚጠይቁ፥ ግላዊ አስተያየትን የሚመለከቱ፥ የማስታወስና የማገናዘብ ችሎታን የሚጠይቁ) ጥያቄዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ባለመታየታቸው በተጠቀሱት የጥያቄ አይነቶች ብቻ የንባብ ክሂሎችን ለማለማመድ ይቻላል ማለት ያስቸግራል::

በአራተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተለያዩ ማስታወሻዎችና መመሪያዎች ቀርበዋል:: ከቀረቡት መካከልም የንባብ ክሂልን የሚመለከቱ ይገኛሉ:: ለምሳሌ (በገፅ 70) ላይ የንባብ ፍጥነትና አይነቶችን፥ (በገፅ 77) ላይ ደግሞ የመረጃ ምንጮችን የሚመለከት መመሪያዎች ቀርበዋል:: እነዚህ መመሪያዎች በትወራ መልክ የቀረቡ የአሰራር መርሆዎች ናቸው::

መርሆዎቹን ተማሪው እንዲገለገልባቸው ከምንባቦችና ከመልመጃዎች ጋር በመጣመር መቅረብ ይገባቸዋል። ምክንያቱም ተማሪው ሊያውቃቸውና ሊገለገልባቸው የሚችለው በምንባቦች ምሳሌነት ሲቀርቡለትና በመልመጃዎች ሲለማመድባቸው ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ግን ከምንባብና ከመልመጃዎች ተለይተው የቀረቡ በመሆናቸው ተማሪው ምናልባት በቃል ጥናት ደረጃ ያውቃቸው እንደሆን እንጅ ሊጠቀምባቸው አያስችሉትም።

አጠቃላይ በሆነ መልኩ የአራተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ፥ በምዕራፍ ሁለት ከተጠቀሱት በመስኩ የተሰማሩ ምሁራን ካቀረቧቸው የውጤታማ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ትወራዎች አንፃር ሲገመገም፥ ክሂሉን ለማዳበር ያለው ተገቢነትና ብቃት ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል።

4.1.2 <u>የአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ የሚጠይቀው የንባብ ክንዋኔዎች</u>

ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች በቀረበ የአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ማስተዋልና ማጥናት፥ ሰውና ኑሮው፥ የተፈጥሮ አካባቢያችን፥ ኢትዮጵያ አገራችንና የኢትዮጵያ ህዝቦች፥ ባህሎች፥ ስልጣኔና ቅርሶች የሚሉ ክፍለ ትምህርቶች ቀርበዋል። በነኝህ አበይት ክፍለ ትምህርቶች ስር የሚገለፁ ሃያ አንድ ንዑሳን ርዕሶችም ተካተዋል።

መጽሐፉ ይዘቶችን በስዕላዊ መግለጫዎች፥ በሠንጠረዦችና በሙከራ ሂደቶች በማስደገፍ በአንቀፅና በምንባብ መልክ ያቀርባል። የትምህርት ይዘቶቹ 182 በሚያህሉ ስዕላዊ መግለጫዎች ተደግፈው፥ 36 በሚሆኑ የሙከራ ተግባራትና በ36 ሠንጠረዦች ተጠናክረው የቀረቡ ናቸው።

ተማሪው የቀረቡትን ይዘቶች አንብቦ ለመገንዘብ፥ በአንቀፅና በምንባብ መልክ የተገለፁት ይዘቶች ከሚጠይቁት የንባብ ክሂሎች ባሻገር ስዕላዊ መግለጫዎችንና ሠንጠረዦችን የማንበብና የመተርጎም፥ መመሪያዎችን አንብቦ ሙከራዎችን ለማካሄድ የሚያስችሉት ክሂሎች ሊኖሩት ይገባል።

መማሪያ መጽሐፉ ይዘቶቹን ካቀረበ በኋላ፥ የቀረቡትን ይዘቶች በሚመለከት የግንዛቤ ጥያቄዎችና የሙከራ ተግባራዊ ሂደቶችን የሚጠይቁ መልመጃዎች ያቀርባል። መልመጃዎቹ የቀረቡበት የጥያቄ አይነቶች የምርጫና የማዛመድ፥ እውነት ወይም ሀሰት፥ ክፍት ቦታዎች የመሙላት፥ አጭር መልስ የመስጠትና ተግባራዊ ክንዋኔዎችን የሚጠይቁ ናቸው።

መልመጃዎቹ የሚጠይቁትን የንባብ ክንዋኔዎች አጠቃላይ ገፅታ ስንመለከት ተማሪው የቀረበለትን የይዘት ገለፃ አንብቦ፥ ዝርዝር መረጃዎችንና እውነታዎችን በማስታወስ ለቀረቡለት የግንዛቤ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥ፥ በቅደም ተከተል የተገለፁ የአሰራርና የድርጊት ዝርዝር መግለጫዎችን ተረድቶ ሙከራዎች እንዲያካሂድ፥ በሠንጠረገሮች የቀረቡ መረጃዎችን በማንበብ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥ፥ ዝርዝር መረጃዎችን አጠቃሎ እንዲገልፅ፥ ለሙያዊ ቃላት ፍች እንዲሰጥ፥ እውነታን ከግል አመለካከት እንዲለይ እና በምክንያትና በውጤት መካከል ያለ ግንኙነትን እንዲገልፅ የሚመለከቱ ናቸው::

ሠንረጠዥ አንድ፥ በአካባቢ ሳይንስ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የንባብ ክንዋኔዎች፥ መጠንና ተማሪውን የሚጠይቁ ክሂሎችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

ተራ ቁጥር	በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የክንዋኔ አይነቶች	የቀረቡበት የድግግሞሽ መጠን	ክንዋኔውን ለመፈፀም ከተማሪው የሚጠበቅ የንባብ ክሂል
1	መንስኤና ውጤትን መለየት	10	በምክንያትና በውጤት መካከል ያለ ግንኙነትን መገንዘብ
2	ዝርዝር መረጃዎችን ማስታወስ	12	ዝርዝር ሃሣቦችን ከአጠቃላይ ሃሣብ ለይቶ መረዳት
3	ዝርዝር መረጃዎችን አጠቃሎ ማቅረብ	15	በዋና እና በዝርዝር ሃሣቦች መካከል ያለ ዝምድናን መገንዘብ፥ ዋና ሃሣብን መለየት
4	እውነታን ከግል አስተያየት መለየት	12	የግል አስተያየትና እውነታዎች የሚቀርቡበትን የጽሑፍ አቀራረብ መንገድ መለየት
5	በሠንጠረዥ የቀረቡ መረጃዎችን አጠቃሎ መገንዘብ	36	- ሠንረገሮችን ማንበብና መተርጎም - መረጃዎችን በሠንጠረዥ መግለፅ
6	መመሪያዎችን በማንበብ ሙከራዎች ማካሄድ	36	በቅደም ተከተል የቀረቡ ዝርዝር መረጃዎችን አንብቦ የመገንዘብ፥ ተግባራትን የመፈፀምና ውጤቱን የመግለፅ
7	ለሙያዊ ቃላት ፍች መፈለግ	8	የቃላት ፍች ከአውዳቸው በመገመት የመገንዘብ
8	በስዕላዊ መግለጫዎች ተደግፈው የቀረቡ ገለፃዎችን መረዳት	182	- ስዕላዊ መግለጫዎችን የማንበብና የመተርጎም - ስዕላዊ መግልጫዎችን ከይዘት ገለፃ ጋር አገናዝቦ የመረዳት
9	በካርታዎችና በቻርቶች የቀረቡ መረጃዎችን አጠቃሎ መገንዘብ	13	ካርታዎችንና ቻርቶችን ማንበብና መተርጎም
10	በጊዜ ቅደም ተከተል የተፈፀሙ ሁኔታዎችን አጠቃሎ መገንዘብ	10	ዋና ዋና ሁኔታዎች የተፈፀሙበትን ጊዜ ለይቶ የመረዳትና የማስታወስ
11	በይዘቶች መካከል ያለ ግንኙነት አገናዝቦ መረዳት	8	ቀደምት እውቀትን ለግንዛቤ የማዋልና ይዘቶችን የማዛመድ
12	እውነታዎችን ማወዳደር	8	የማወዳደሪያ የጽሑፉ አቀራረብ ስልቶችን የመለየት

ከሠንጠረዥ አንድ መረዳት እንደሚቻለው፥ በአካባቢ ሳይንስ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች በከፍተኛ ደረጃ ስዕላዊ መግለጫዎችን የማንበብና የመተርጎም፥ ከይዘቶች ጋር አገናዝቦ የመረዳት የንባብ ክሂልን ሲጠይቁ፥ ሠንጠረዦችን ማንበብና በቅደም ተከተል የተገለፀው ዝርዝር የአሰራር መረጃዎችን አንብቦ ተግባራትን የመፈፀም ክሂሎችን በሁለተኛ ደረጃ እንደሚጠይቁ ነው።

ዝርዝር መረጃዎችን አጠቃሎ የመገንዘብ፥ ቻርቶችንና ካርታዎችን ማንበብና መተርጎም፥ እውነታን ከግል አስተያየት መለየት፥ በምክንያትና በውጤት መካከል ያለ ግንኙነት መለየትና የቃላትን ፍች ከአገባባቸው የመገመት ችሎታ ከቀረቡበት የመለማመጃና የይዘት መቅረቢያ መንገድ ድግግሞሽ መጠን አንፃር በደረጃ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ተማሪውን የሚጠይቁት የንባብ ክሂሎች ናቸው።

በአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች አንብቦ ለመገንዘብና መልመጃዎቹን ለመሥራት፥ ተማሪው ክንዋኔዎቹን ለመተግበር የሚያስችሉት የንባብ ክሂሎች ሊኖሩት ግድ ይለዋል። ለዚህ ደግሞ፥ የመማሪያ ቋንቋው የንባብ ክፍለ ትምህርት መልመጃዎች ክሂሎቹን በማለማመድ በኩል እገዛ ሊያደርጉለት ይገባል።

ለአራተኛ ክፍል በተዘጋጀ የአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶችና መልመጃዎች የሚጠይቁትን የንባብ ክንዋኔዎች አጠቃላይ ገፅታ ይህን ያህል ካየን፥ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች ተማሪውን ምን ያህል ክሂሎቹን በማለማመድ በኩል እገዛ እንደሚያደርጉ ቀጥለን ለመመልከት እንሞክራለን።

4.1.3 በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች፥ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቃቸውን የንባብ ክንዋኔዎች ከማለማመድ አንፃር

ለአራተኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከያንዳንዱ ምንባብ ቀጥሎ የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል። መልመጃዎቹ መልመጃ አንድ፥ ሁለትና ሦስት በሚል መልክ የተከፈሉ ናቸው።

በመልመጃ አንድ፥ የምንባቡ ፍሬ ነገር ተማሪው መጨበጡን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የግንዛቤ ጥያቄዎች ቀርበዋል። መልመጃ ሁለት ከምንባብ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች መፈለግና ሰዋሰዋዊ ጥያቄዎችን አካቷል። መልመጃ ሦስት ደግሞ የምንባቡን ሃሣብ ተማሪው ከግል ህይወቱና ከአካባቢው ጋር የሚያዛምድባቸው ተግባራዊ ጥያቄዎች ይዟል።

መልመጃዎቹ የቀረቡት በምርጫ፥ በማዛመድ፥ በእውነት ሀሰት፥ ክፍት ቦታዎችን በመሙላት፥ አጭር መልስ በሚሹና ተግባራትን መፈፀም በሚጠይቁ የጥያቄ አይነቶች ነው። መልመጃዎቹ በአብዛኛው ተማሪውን ከምንባብ የወጡ የግንዛቤ ጥያቄዎችን እንዲመልስ፥ ከምንባብ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች እንዲሰጥ፥ ቃላትን ክፍች አንፃር እንዲያዛምድ፥ ዐረፍተ ነገር እንዲመሰርት፥ የቃላት ርባታና ምስረታ ሥርዓትን እንዲለይ፥ የአያያዥ ቃላትን አገባብ ለይቶ መጠቀም እና የምንባቡን ሃሣብ ከግል ህይወቱና ከአካባቢው ጋር እንዲያዛምድ የሚጠይቁ ናቸው።

ከአንተ ክንዋኔዎች በተጨማሪ እጅግ አነስተኛ በሆነ መጠን መንስኤና ውጤትን መለየት፥ የድርጊት ቅደም ተከተላዊ አካሄድን መግለፅ፥ በስዕላዊ መግለጫና በሠንጠረዥ የቀረበ መረጃን መሠረት በማድረግ ጥያቄዎችን መመለስ፥ ዋና ሃሣብንና ዝርዝር ሃሣብን መለየትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች በመጽሐፍ ውስጥ ቀርበዋል።

ከአንተ መካከል ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንመልከት፥

- የደን መጨፍጨፍ የአየር መዛባትን የሚያስከትል ሲሆን፥ ይህ ለምርት መቀነስ ምክንያት ይሆናል

ሀ. መንስኤ_____
ለ. ውጤት_____

ሀ. መንስኤ_____
ለ. ውጤት_____
/ገፅ 59/

- የድርጊት ቅደም ተከተሎችን አስተካክላችሁ ፃፉ

ጉድጓድ ማዘጋጀት
የዘር ፍሬ ማዘጋጀት
ችግኞችን መትከል
መደብ ማዘጋጀት /ገፅ 71/
ችግኞችን ማፍላት

- የውሃ ብክለት የሚለውን ምንባብ እንደገና አንብቡና የተረዳችሁትን ዋና ዋና ሃሣቦች ማስታወሻ ይዛችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ /ገፅ 106/

እነዚህ የመልመጃ ጥያቄዎች በአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች ለመገንዘብ የሚያስፈልጉ የንባብ ክሂሎችን በማለማመድ በኩል እገዛ እንደሚያደርጉ ይታመናል፤ ነገር ግን በሁለቱ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የቀረቡትን መጠን ስንመለከት፥ በአማርኛው መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት እጅግ አነስተኛ በመሆናቸው የጎላ እገዛ ያደርጋሉ ለማለት አያስደፍርም::

ሠንጠረዥ ሁለት፡ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች የሚጠይቁት የንባብ ክንዋኔና የሚያለማምዱት ክሂሎችን የሚያሳይ፡

ተራ ቁጥር	መልመጃዎቹ የሚጠይቁት ክንዋኔዎች	የቀረቡት መልመጃ ብዛት	የሚያለማምዱት ክሂሎች
1	ከምንባብ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች መፈለግና በቃላቱ አረፍተነገር መስራት	40	የቃላትን ፍች ማጥናት መለየት
2	ከምንባብ ለወጡ የግንዛቤ ጥያቄዎች መልስ መስጠት	36	አጠቃላይና ዝርዝር ሃሣቦችን ማስታወስ
3	የቃላት ምሰረታና ርባታን በተመለከተ የቀረቡ ሰዋሰዋዊ ጥያቄዎችን መስራት	8	የቃላት ሰዋሰዋዊ ሥርዓት መለየት
4	አያያዥ ቃላትን አረፍተነገር ውስጥ መጠቀምና የአረፍተነገር መዋቅር መለየት	12	የአያያዥ ቃላትን አገባብ መለየት በአረፍተነገር ውስጥ መገልገል
5	እውነትን ከግል አስተያየት ለይቶ ማመልከት	2	የግል አስተያየትና እውነታ የሚገለፅበትን የፅሑፍ አቀራረብ መለየት እና እውነታን ከአስተያየት መለየት
6	መንስኤና ውጤትን መግለፅ	3	በምክንያትና በውጤት መካከል ያለ ግንኙነትን ለይቶ መገንዘብ
7	መረጃዎችን ማወዳደር፥ ማገናዘብና አጠቃሎ መገንዘብ	2	ሃሣብን የማወዳደሪያ መንገድ እና በጽሑፍ ማቅረቢያ ዘዴን መለየት
8	ሠንጠረዦችና ካርታዎችን መሠረት በማድረግ የቀረቡ ጥያቄዎችን መመለስ	1	ካርታና ሠንጠረዥን ማንበብና መተርጎም
9	ዋና እና ዝርዝር ሃሣቦችን ለይቶ ማመልከት	3	አጠቃላይና ዝርዝር ሃሣብን ለይቶ ማንበብና መገንዘብ
10	የምንባብን ሃሣብ ከግል ህይወትና ከአካባቢ ጋር ማገናኘትና ተግባራትን መፈፀም	15	የምንባብን ሃሣብ ከቀደምት እውቀት ጋር ማዛመድ፥ ሌሎች ክሂሎችን በማዋሃድ መጠቀም
11	በቅደም ተከተል የሚከናወኑ ተግባራትን ማስተካከል	2	በቅደም ተከተል የቀረቡ ዝርዝር መረጃዎች መለየት፥ አካሄዳቸውን አንብቦ በመረዳት ተግባራት መፈፀም

* (ቁጥሮቹ በመልመጃዎቹ ሥር የቀረቡትን የጥያቄዎች መጠን የሚያመለክቱ አይደሉም የመልመጃዎችን ብዛት እንጅ፤)

በሠንጠረዥ ሁለት ውስጥ የተገለፁትን ክንዋኔዎችና የቀረቡበትን የመልመጃ መጠን አጠቃላይ ገፅታ ስንመለከት፥ በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ተማሪውን በአብዛኛው የሚያለማምዱት የምንባቡን ፍሬ ሃሣብ በማስታወስ ጥያቄዎችን መመለስ፥ ከምንባብ ለወጡ ቃላት ፍች መፈለግና ሰዋሰዋዊ ሥርዓትን ማለማመድ ነው ማለት ይቻላል።

እነዚህ ደግሞ በአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶችና መልመጃዎች የሚፈልጉትን የንባብ ክንዋኔዎች በማለማመድ በኩል እገዛ ያደርጋሉ ለማለት ያስቸግራል፤ ምክንያቱም በአካባቢ ሳይንስ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶችና መልመጃዎች በከፍተኛ ደረጃ የሚጠይቁት የቃላትን ፍችና ሰዋሰዋዊ ሥርዓትን የሚመለከቱ ባለመሆናቸው ነው።

በሁለቱ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የቀረቡትን የንባብ ክንዋኔዎች በንፅፅር ስንመለከት፥ በአካባቢ ሳይንስ መጽሐፍ ውስጥ ለቀረቡ ይዘቶችና መልመጃዎች የሚያስፈልጉ ስዕላዊ መግለጫዎችን ከይዘት ገለፃ ጋር አዋህዶ የመገንዘብ፥ ቻርቶችን አንብቦ የመረዳትና በቅደም ተከተል የተገለፁ የድርጊት መመሪያዎችን አንብቦ ሙከራዎችን የማካሄድ ክንዋኔዎች በአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ ትኩረት አልተሰጣቸውም። ሙከራዎችን የማካሄድና ስዕላዊ መግለጫዎችን አንብቦ የመረዳት ክንዋኔዎች በአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ ጨርሶ ያልቀረቡ ሲሆን፥ ሠንጠረዥ የማንበብና የመተርጎም ክንዋኔ በአንድ መልመጃ ብቻ ቀርቧል።

በአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በምክንያትና በውጤት መካከል ያለ ግንኙነት መለየት 10 ጊዜ፥ መረጃዎችን አጠቃሎ መገንዘብና ካርታዎችን ማንበብ 15 ጊዜ፥ እውነታን ከግል አስተያየት መለየት 12 ጊዜ፥ በቅደም ተከተል የተፈፀሙ ሁኔታዎችን መግለፅ 10 ጊዜ፥ እውነታዎችን ማወዳደር 8 ጊዜ ያህል በተደጋጋሚ ሲቀርቡ፥ በማስተማሪያ ቋንቋው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ግን ከ 3 ባልበለጡ መልመጃዎች ብቻ ቀርበዋል። ይህ ደግሞ የአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች ለመገንዘብና መልመጃዎቹን ለመስራት አስፈላጊ ለሆኑ የንባብ ክሂሎች ትኩረት ሰጥተው በብዙ መልመጃዎች ተማሪውን እንደማያለማምዱት ያመለክታል።

ከዚህ ግንባቤ በመነሳትም በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች የአካባቢ ሳይንስ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶችን ለመገንዘብ የሚያስፈልጉ የንባብ ክሂሎችን በማለማመድ በኩል ያላቸው አገዛ ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል::

4.1.4 በጽሑፍ መጠይቅ ከመምህራን የተገኙ መረጃዎች ትንተና

መጠይቁን የሞሉት ለናሙና በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ አርባ የአራተኛ ክፍል መምህራን ናቸው:: ከነኝህ መካከል 22ቱ ወንዶች ሲሆኑ፥ 18ቱ ሴት መምህራን ናቸው:: ሁሉም በመምህራን ማሰልጠኛ የሚሰጠውን መደበኛ የመምህርነት ስልጠና የወሰዱና ከስልጠና በኋላ ተጨማሪ የስልጠና ዕድል ያላገኙ ናቸው::

መምህራኑ ከ15 - 28 ዓመት የማስተማር ልምድ ያላቸው ሲሆኑ በነኝህ የአገልግሎት ዘመናት ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል አማርኛና ሌሎች ትምህርቶችን ያስተማሩ መሆናቸውን ገልፀዋል::

ሠንጠረዥ ሦስት፥ የተማሪዎቻቸውን የንባብ ችሎታ በተመለከተ የመምህራኑ ምላሽ

ተራ ቁጥር	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
ሀ	ያነበቡትን ምንባብ የማስታወስ ችሎታቸው ምን ያህል ነው?	15%	37.5%	40%	7.5%	-
ለ	ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን የመስራት ችሎታቸውስ	10%	30%	50%	10%	-
ሐ	መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን አንብበው በተግባር የመተርጎም ችሎታቸው ምን ያህል ነው?	-	-	35%	42.5%	22.5%
መ	ስዕላዊ መግለጫዎችን፥ ቻርቶችንና ካርታዎችን የማንበብና የመተርጎም ችሎታቸው	-	-	27.5%	62.5%	10%
ሠ	አጠቃላይ ሃሣብን ከዝርዝር ሃሣብ የመለየት ችሎታቸው	-	-	42.5%	57.5%	-
ረ	የአንድን ጽሑፍ ቁልፍ ሃሣብ የመገመት ችሎታቸው ምን ያህል ነው?	-	-	35%	42.5%	22.5%

ከሠንጠረዥ ሦስት መገንዘብ እንደሚቻለው መጠይቁን ከሞሉ መምህራን መካከል 40%ቱ ተማሪዎቻቸው ያነበቡትን ምንባብ ይዘት የማስታወስ ችሎታቸው መካከለኛ መሆኑን ሲገልፁ፥ 37.5ቱ ደግሞ ከፍተኛ እንደሆነ አመልክተዋል:: 15%ቱ በጣም ከፍተኛ ነው ሲሉ 7.5%ቱ ብቻ ዝቅተኛ እንደሆነ ጠቁመዋል::

ከምንባብ የወጡ የግንዛቤ ጥያቄዎችን የመስራት ችሎታቸው መካከለኛ እንደሆነ መጠይቁን ከሞሉት መምህራን መካከል 50%ቱ ሲያረጋግጡ፥ 30%ቱ ከፍተኛ፥ 10%ቱ ደግሞ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ አመልክተዋል።

መመሪያዎችን አንብበው በተግባር የመተርጎም ችሎታቸውን በተመለከተ 42.5%ቱ ዝቀተኛ፥ 22.5%ቱ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ሲገልፁ፥ በተመሳሳይ መልኩ የጽሑፍን ቀጣይ ይዘት የመተንበይ ችሎታቸውም ዝቅተኛ እንደሆነ በ42.5% መምህራን ሲገለፅ፥ በ22.5% መምህራን ደግሞ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ተገልፅዋል።

አጠቃላይ ሃሣብን ከዝርዝር ሃሣብ የመለየት ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑ በ57.5% መምህራን ሲረጋገጥ፥ በ42.5% መምህራን ደግሞ መካከለኛ እንደሆነ ተጠቁሟል። ግራፎችን፥ ሠንጠረዦችን፥ ካርታዎችንና ስዕላዊ መግለጫዎችን አንብቦ የመገንዘብ ችሎታቸውም ቢሆን ዝቅተኛ እንደሆነ መጠይቁን ከሞሉት 62.5% መምህራን አረጋግጠዋል። 27.5%ቱ ብቻ መካከለኛ መሆኑን ጠቁመዋል።

መምህራኑ ስለተማሪዎቻቸው የንባብ ችሎታ የሰጡትን ምላሽ ስንመለከት፥ ተማሪዎቹ ያነበቡትን ምንባብ ማስታወስና ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን የመስራት ችሎታቸው ከሌሎቹ በተሻለ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይጠቁማል። ለዚህ ውጤት በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች በአብዛኛው የሚያለማምዱት ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን መሰረት መሆኑ እገዛ እንዳደረጉ መገመት ይቻላል።

በአማርኛና በአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐ�ት መካከል ግንኙነት መኖር አለመኖሩን እንዲገልፁ ለቀረበላቸው ጥያቄ መጠይቁን ከሞሉት 40 መምህራን መካከል 27ቱ (67.5%) ግንኙነት እንደሌላቸው ሲገልፁ፥ የተቀሩት ግንኙነት እንዳላቸው አመልክተዋል።

በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች፥ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቃቸውን የንባብ ክሂሎች በማለማመድ በኩል እገዛ እንደማያደርጉ በ29 (72.5%) መምህራን ሲረጋገጥ፥ መምህራኑ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የሚያለማምዱዋቸው መልመጃዎችም ተማሪዎቻቸው በአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን መልመጃዎች እንዲሰሩ ያግዛሉ የሚል እምነት እንደሌላቸው መጠይቁን ከሞሉት መካከል 28ቱ (70%) መምህራን ገልፀዋል፡

ሠንጠረዥ አራት ለንባብና ንባብን ስለማስተማር ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ የሰጡት ምላሽ

ተራ ቁጥር	ጥያቄ	በጣም አስማማለሁ	አስማማለሁ	ለመወሰን ያስቸግረኛል	አቃወማለሁ	በጣም አቃወማለሁ
1	ንባብን ማስተማር የአማርኛ መምህራን ተግባርና ሃላፊነት ብቻ ነው።	-	-	5%	85%	10%
2	ማንበብ አንድን ጽሑፍ ከዳር እስከ ዳር መወጣት ማለት ነው።	22.5%	40%	10%	12.5%	15%
3	የትምህርት ይዘቶችን አንብቦ የመገንዘብ ችሎታን ለማዳበር የተለያዩ የንባብ ስልቶችን ማስተማር ያስፈልጋል።	40%	50%	-	10%	-
4	የንባብ ክሂልን በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡ ምንባቦች የወጡ ጥያቄዎችን ብቻ በማሰራት ማዳበር ይቻላል።	-	37.5%	17-5%	45%	-
5	ተማሪዎች ለንባብ የቀረበላቸውን ጽሑፍ አንብበው ለመረዳት በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን ቃላት በሙሉ ማወቅ አለባቸው	37.5%	62.5%	-	-	-
6	ለንባብ የቀረበውን ጽሑፍ ቃላት፥ ሐረግና ዐ.ነገር ደረጃ በደረጃ እያሳወቁ አጠቃላይ የጽሑፉን ሃሣብ እንዲገነዘቡ ማድረግ የንባብ ክሂልን ለማዳበር የሚመረጥ መንገድ ነው።	-	67.5%	12.5%	20%	-

ከሠንጠረዥ አራት ማንበብ እንደሚቻለው፥ ንባብን ማስተማር የአማርኛ መምህራን ተግባርና ሃላፊነት ብቻ እንዳልሆነ በመምህራኑ ዘንድ ግንዛቤ መኖሩን 34 መምህራን (85%) ሃሣቡን እንደሚቃወሙት በመግለፅ አመልክተዋል።

ማንበብ ማለት አንድን ጽሑፍ ከዳር እስከ ዳር መውጣት ማለት እንደሆነ የአብዛኛዎቹ መምህራን ግንዛቤ መሆኑን 40%ቱ መስማማታቸውን፥ 22.5%ቱ ደግሞ በጣም መስማማታቸውን በመግለፅ ጠቁመዋል።

በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን መልመጃዎች ብቻ በማሰራት የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ማዳበር እንደሚቻል 37.5% መምህራን መስማማታቸውን ሲገልፁ፥ 45% የሚያህሉት ሃሣቡን በመቃወም በቂ እንዳልሆነ አመልክተዋል። የተለያዩ የንባብ ስልቶችን ማስተማር የንባብ ችሎታን ለማዳበር አስፈላጊ እንደሆነም በ50% መምህራን ታምኖበታል።

መጠይቁን የሞሉት መምህራን በሙሉ ተማሪዎቻቸው ለንባብ የቀረበላቸውን ጽሑፍ አንብበው ለመገንዘብ በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን ቃላት በሙሉ ማወቅ የግድ እንደሚያስፈልጋቸው የሚያምኑ መሆናቸውን 62.5%ቱ እስማማለሁ፥ 37.5% ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ በማለት አረጋግጠዋል።

መጠይቁን ከሞሉት መምህራን መካከል 27ቱ ወይም 67.5%ቱ የንባብ ክሂልን ለማዳበር፥ ለንባብ በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት፥ ሀረጋትና አረፍተነገሮች ደረጃ በደረጃ በማስጠናት አጠቃላይ የጽሑፉን ሃሳብ እንዲገነዘቡ ማድረግ የተሻለና የሚመረጥ መንገድ እንደሆነ ሲቀበሉ፥ 8 መምህራን ወይም 20%ቱ ብቻ መንገዱ የሚመረጥ እንዳልሆነ ሀሳቡን በመቃወም አመልክተዋል። የተቀሩት ለመወሰን እንደተቸገሩ ጠቁመዋል።

መምህራኑ ለንባብ ማስተማሪያ አዘውትረው የሚጠቀሙባቸውን የማስተማሪያ ዕሑፎች እንዲገልፁ ለቀረበላቸው ጥያቄ፥ 35 መምህራን (87.5) በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦች አዘውትረው እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ፥ 5 መምህራን (12.5%) ብቻ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን በተጨማሪ እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል።

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦችና መልመጃዎች ለትምህርት ሲያቀርቡ ምንም አይነት ለውጥና ማሻሻያ ሳያደርጉ በመጽሐፉ ውስጥ በቀረቡበት መልክ እንደሆነ በ 37 መምህራን (92.5%) ተገልጸዋል። 3 መምህራን (7.5%) ብቻ መጠነኛ ማሻሻያ አድርገው እንደሚያቀርቡ ጠቁመዋል።

ሠንጠረዥ - አምስት - የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ልምዳቸውን በተመለከተ የሰጡት ምላሽ

ተራ ቁጥር	አቀራረብ	አዘውትራ እጠቀማለሁ	አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ	አልፎ አልፎ	አንዳንዴ የምጠቀምበት ጊዜ አለ	ፈፅሞ አልጠቀም
1	በመጀመሪያ ምንባቡን ራስዎ ካነበቡ በኋላ ተማሪዎቹን ተራ በተራ በማስነሳት ማስነበብ፤	77.5%	22.5%	-	-	-
2	ተማሪዎቹ ተራ በተራ እየተነሱ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ማድረግ፤	82.5%	17.5%	-	-	-
3	ተማሪዎቹ በየግላቸው ድምፃቸውን ሳያሰሙ እንዲያነቡ ማድረግ፤	-	10%	55%	35%	-
4	በጥንድና በቡድን ተማሪዎቹን በማድረግ ማስነበብ፥	-	-	10%	5%	85%
5	ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ለመነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎችን በማቅረብ ማወያየት፤	-	12.5%	-	65%	22.5%
6	የተማሪዎቹን የንባብ ሂደት ሊያደናቅፉ የሚችሉ አዳዲስ ቃላትን ከንባብ በፊት ለትምህርት ማቅረብ፤	-	-	20%	12.5%	67.5%
7	ምንባቡ ከተነበበ በኋላ ከምንባብ የወጡ የቃላትና የግንዛቤ ጥያቄዎችን ማሰራት	80%	20%	-	-	-
8	ተማሪዎቹ የሠሩዋቸውን መልመጃዎች በቡድንና በጥንድ ሆነው እንዲያርሙ ማድረግ፤	-	-	-	30%	70%
9	ከምንባቡ መበነሳት ከአካባቢያቸው ወይም ከሌላ ትምህርት ጋር የተያያዙ የንባብ መልመጃዎች ማቅረብ፤	7.5%	57.5%	25%	10	-
10	ከተለያዩ የትምህርት ይዘቶች የተወሰዱ ጽሑፎችን ለንባብ ማቅረብ፤	-	5%	-	20%	75%

በሠንጠረዥ አምስት መጠይቁን የሞሉት መምህራን የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ልምዳቸውን አዘውትረው ከሚጠቀሙበት አንፃር የገለፁት መረጃ ተጠቃሎ ቀርቧል::

በገለፃቸው መሠረት ምንባቦችን ለንባብ ሲያቀርቡ አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው መንገዶች፥ መጀመሪያ መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው ካነበቡ በኋላ ተማሪዎቻቸውን ተራ በተራ በማስነሳት ማስነበብና ተማሪዎችን ብቻ ተራ በተራ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ማድረግ እንደሆነ ጠቁመዋል::

ለዚህም መጠይቁን ከሞሉት 40 መምህራን መካከል 31 መምህራን (77.5%) መጀመሪያ ራሳቸው አንብበው ቀጥሎ ተማሪዎችን ተራ በተራ የማስነበብ አቀራረብን አዘውትረው እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ፥ 22.5%ቱ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል::

ራሳቸው ሳያነቡ ተማሪዎችን ብቻ ተራ በተራ በማስነሳት ማስነበብን ደግሞ 82.5% ወይም 33 መምህራን አዘውትረው እንደሚጠቀሙ፥ 17.5%ቱ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚጠቀሙ አረጋግጠዋል።

ተማሪዎቻቸው በየግላቸው ድምፃቸውን ሳያሰሙ እንዲያነቡ የሚያደርጉት አልፎ አልፎ ብቻ እንደሆነ በ55% መምህራን ተደግፏል። 10% የሚሆኑት ብቻ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚያስነብቡ ጠቁመዋል። ተማሪዎችን በቡድንና በጥንድ በማድረግ የማስነበብ ልምድም እንደሌላቸው፥ 34 ወይም 85%ቱ መምህራን ፈፅሞ እንደማይጠቀሙ አረጋግጠዋል።

ምንባቡን ከማስነበባቸው በፊት የሚያከናውኑዋቸው ተግባራትን በተመለከተ የተገኘው መረጃ ለመነሻ የሚሆኑ ሃሣቦችን ከንባብ በፊት በማቅረብ ተማሪዎችን የሚያወያዩት 12.5% ብቻ ሲሆኑ፥ 65%ቱ አንዳንድ ጊዜ፥ የተቀሩት ደግሞ ፈፅሞ እንደማያወያዩ ያመለክታል። በተመሳሳይ መልኩ፥ የተማሪዎችን የንባብ ሂደት ሊያደናቅፉ የሚችሉ ቁልፍ ቃላትንም ከንባብ በፊት የማቅረብ ልምድ እንደሌላቸው 67.5% የሚሆኑት ፈፅሞ እንደማይጠቀሙ በመግለፅ አመልክተዋል።

መጠይቁን ከሞሉት መምህራን መካከል 32 (80%) መምህራን ምንባብ ካስነበቡ በኋላ ከምንባብ የወጡ የቃላትና የግንዛቤ ጥያቄዎችን አዘውትረው እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ፥ 20%ቱ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ይህንኑ አሠራር እንደሚጠቀሙ ጠቁመዋል።

ተማሪዎቻቸው የሠሩዋቸውን መልመጃዎች በጥንድና በቡድን ሆነው እርስ በርሳቸው እንዲተራረሙ አብዛኛው መምህር እንደማያደርግ መጠይቁን ከሞሉት 70%ቱ ፈፅሞ እንደማይጠቀሙ፥ 30%ቱ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ብቻ እንደሚጠቀሙ በመግለፅ አረጋግጠዋል።

ካቀረቡላቸው የምንባብ ሃሣብ በመነሳት ከአካባቢያቸው ወይም ከሌላ ትምህርት ጋር የተያያዙ መልመጃዎችን አዘውትረው እንደሚጠቀሙ 7.5% የሚሆኑት መምህራን ብቻ ሲገልፁ 57.5% ያህሉ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚያቀርቡ ገልፀዋል። 25%ቱ አልፎ አልፎ፥ 10%ቱ ደግሞ አንዳንድ ብቻ እንደሚያቀርቡ ጠቁመዋል። የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን ግን ለንባብ በማቅረብ ከተማሪው ጋር እንደማያስተዋውቁ፥ መጠይቁን ከሞሉት 40 መምህራን መካከል በ30ዎቹ ወይም በ75% ፈፅሞ እንደማያቀርቡ ተገልጿል።

በተጨማሪም መምህራኑ በአማራጭነት የቀረበው የትምህርት አቀራረብ ተግባራዊ ለማድረግ የስልጠናና የትውውቅ መድረክ ቢዘጋጅላቸው በአቀራረቡ ለመጠቀምና ውጤታማ ለመሆን ፈቃደኞች እንደሆኑ በ100% አረጋግጠዋል።

4.2 የንባብ ክሂል ለማዳበር የሚያግዝ አማራጭ የትምህርት አቀራረብ

እንደማስተማሪያ ቋንቋነቱ ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰጥ የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት በደረጃው የሚሰጠው የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቀውን የንባብ ክሂል ለማዳበር እንዴት ቢቀርብ ይሻላል? የሚለውን የጥናቱን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ ለሙከራ የቀረበውን የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ናሙና ለማሳየት ይሞክራል።

ለሙከራ የቀረበው የትምህርት ዝግጅት፥ አንብቦ የመገንዘብ ችሎታን ለማዳበር ወቅታዊና ውጤታማ እንደሆነ በመስኩ በተሰማሩ ምሁራን ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ቅድመ-ንባብ በንባብ-ወቅት እና ድህረ-ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተ በሦስት ደረጃ የተከፈለ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ነው።

በናሙናነት የቀረቡትን የንባብ ትምህርቶች፥ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቃቸውን የንባብ ክሂሎች ለማለማመድ ይሆናሉ ተብለው የተመረጡ ጽሑፎችንና በአራተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦችንና መልመጃዎችን መሠረት አድርገው የተዘጋጁ ናቸው። ለዚህም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦች መመልከት ያስፈልጋል።

በዚህ ንዑስ ክፍል በሙከራ ቡድን ተማሪዎች ልምምድ ከተደረገባቸው መካከል አብነት ሊሆኑ የሚችሉ ክፍለ ትምህርቶች ብቻ ሲቀርቡ፥ ሌሎቹ በአባሪ ተያይዘዋል። (ሌሎቹን ከአባሪ ሦስት ይመልከቱ)

ክፍለ ትምህርት - አንድ

ርዕስ - የዱር እንስሳት (የአራተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ገፅ 56)

የትምህርቱ ዓላማዎች - ያለፈ ልምድና እውቀታቸውን ለንባብ ከቀረበው ምንባብ ጋር በማዋሃድ የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት ይገነዘባሉ።

- አጠቃላይና ዝርዝር መረጃዎችን ለማግኘት ያነባሉ።
- በምክንያትና በውጤት መካከል ያለ ግንኙነትን ይለያሉ።
- ከምንባቡ ያገኙትን ግንዛቤ በንግግርና በጽሑፍ ይገልፃሉ።

ቅድመ-ንባብ ክንዋኔዎች

<u>መልመጃ አንድ</u> - ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት፥ በቡድንና በጥንድ በመሆን በሚከተሉት መነሻ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፤ በውይይታችሁ የደረሳችሁባቸውን መልሶች መዝግቡና በአንድ የቡድናችሁ አባል አማካይነት ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ፥

ሀ. ስለዱር እንስሳት የምታውቁትንና ማወቅ የምትፈልጉትን ዘርዝሩ

የምታውቋቸው	ማወቅ የምትፈልጉዋቸው

ለ. በዱር እንስሳትና በቤት እንስሳት መካከል ምን ልዩነት አለ?

ሐ. የዱር እንስሳት ለሰው ልጅ ምን ይጠቅማሉ ትላላችሁ?

መ. ለዱር እንስሳት ቁጥር ማነስና መጥፋት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ የምትሉዋቸውን ዘርዝሩ?

- ለነኝህ ጥያቄዎች የሰጣችኋቸው መልሶች ትክክል መሆን ስለመሆናቸውን፥ ምንባቡን ስታነቡ ለማረጋገጥ ሞክሩ፤

የንባብ-ወቅት ክንዋኔዎች

<u>መልመጃ ሁለት</u> - ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች ልብ ብላችሁ አንብቡ፤ ክፍት ቦታዎቹን ብቻ ለመሙላት የሚያስችሉዋችሁ መረጃዎችን ብቻ ለማግኘት ምንባቡን አንድ ጊዜ በፍጥነት አንብቡና ክፍት ቦታዎችን ሙሉ::

1. የዱር እንስሳት በ_____፥ በ_____ ና በ_____ ሊኖሩ የሚችሉ ናቸው::
2. የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ድርጅት የተቋቋመው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ_____ነው::
3. ለዱር እንስሳት መመናመን እንደ ምክንያት የሚጠቀሱትን _____ ና _____ ብሎ በሁለት መክፈል ይቻላል::
4. በዘልማድ የዱር እንስሳት ሲባሉ_____ ብቻ የሚያካትት ይመስላል::
5. ባለፉት 200 ዓመታት ወደ_____ የሚጠጉ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ጠፍተዋል::

ምጋቤ ምላሽ - ለጥያቄዎቹ የሰጠሀቸውን መልሶች ከጓደኞቻችሁ ጋር አስተያዩና በመልሶቻችሁ መካከል ልዩነት ካለ ምንባቡን እንደገና በጋራ አንብባችሁ አስተካክሉ፡

- የጋራ መልሳችሁን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ (አሳዩ)
- መምህራችሁ ለክፍሉ በሙሉ የሚሰጡትን እርማት በደብተራችሁ ፃፉ

መልመጃ ሦስት - ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን ዝግ ብላችሁ እንደገና አንብቡና አጭር መልስ ስጡ::

1. የዱር እንስሳት ስንል የትኞቹን ማለታችን ነው?
2. ለዱር እንስሳት መጥፋት ሰው የሚፈጥራቸውን ምክንያቶች ግለፁ?
3. የዱር እንስሳት ቁጥር እንዳይቀንስና ጨርሶም እንዳይጠፉ መንግስታት እየወሰዱ ያሉት ርምጃዎች ምንድናቸው?
4. የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት የጥበቃ ታሪክም ገና ልጅ ነው ሲል ምን ለማለት የተፈለገ ይመስላችኋል?
5. በሦስተኛው አንቀፅ መጀመሪያ እዚህም ሆነ እዚያ ሀረግ ምንና ምንን ይገልፃል?
6. የዱር እንስሳት እየታደኑ የሚገደሉት ለምንድን ነው?
7. መንግስታት ለዱር እንስሳት ጥበቃ የሚያደርጉት ለምን ብለው ነው

ድህረ-ንባብ ክንዋኔዎች

መልመጃ አራት - ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች በምሳሌው መሠረት መልሱ

ምሳሌ - የደኖች መመንጠር ለዱር እንስሳት መሰደድ ምክንያት ይሆናል::

መንስኤ - የደኖች መመንጠር፡

ውጤት - የዱር እንስሳት መሰደድ፡

ሀ. አደን ለዱር እንስሳት መጥፋት እንደ ሳቢያ ይወሰዳል::

መንስኤ -

ውጤት -

ሰ. ሰደድ እሳት ለደን ቃጠሎ ምክንያት ሲሆን ይህ ደግሞ የዱር እንስሳት መሰደድን ያስከትላል::

1. መንስኤ -

   ውጤት -

2. መንስኤ -

   ውጤት -

ሐ. የደን መጨፍጨፍ የአየር መዛባትን ያስከትላል፤ ይህ ደግሞ ለምርት መቀነስ አይነተኛ ምክንያት ይሆናል::

1. መንስኤ-

   ውጤት-

2. መንስኤ-

   ውጤት-

መ. የእርከን ሥራ የአፈር መሸርሸርን ይቀንሳል

መንስኤ-

ውጤት-

<u>መልመጃ አምስት</u>

1. በዱር እንስሳትና በደን መካከል ያለ ግንኙነት ምን እንደሆነ የአካባቢ ሳይንስ መጽሐፋችሁን አንብባችሁ ወይም መምህራችሁን ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በየተራ እየተነሳችሁ በንግግር ግለፁ?

2. የዱር እንስሳትን ለመንከባከብና ለመጠበቅ በአገራችን የተከለሉ ፓርኮችን፣ የሚገኙበትን ክልል እና የዱር እንስሳቱን አይነት የሚገልፅ ጽሑፍ አንብቡና ያገኛችሁትን ሀሳብ በሠንጠረዥ አቅርቡ::

የፓርኩ ስም	የሚገኝበት ክልል	በውስጡ ያሉ እንስሳት

ክፍለ ትምህርት ሁለት

ርዕስ - የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ክልሎች

ቅድመ ንባብ እንዋኔዎች

<u>መልመጃ አንድ</u> - ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት፣ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመሆን ተወያዩ፣ በውይይታችሁ የምትስማሙባቸውን የመልስ ሃሣቦች መዝግቡና ለመምህራችሁ አሳዩ።

ሀ. የአየር ንብረት ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. አካባቢያችሁ ሞቃታማ ነው ወይስ ቀዝቃዛ? ለምን ሞቃታማ ወይም ቀዝቃዛ የሆነ ይመስላችኋል።

ሐ. የኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎችና ዝቀተኛ ቦታዎች የሚባሉትን አካባቢዎች ታውቃላችሁ? ዘርዝሩዋቸው? የአየር ንብረት ሁኔታቸውስ ምን ይመስላል?

<u>መልመጃ ሁለት</u>

ከዚህ በታች የኢትዮጵያን የአየር ንብረት ክልሎች የሚያሳይ ሠንጠረዥ ቀርቧል፣ ሠንጠረዡ ሙሉ መረጃዎችን አልያዘም፣ የጎደሉትን ክፍት ቦታዎች ምንባቡን በፍጥነት አንብቡና አሟሉ።

ስታነቡ ክፍት ቦታዎችን ለመሙላት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ብቻ ለማግኘት ይሁን።

የአየር ንብረት ክልል	የክልሉ ከፍታ በሜትር	የአየሩ ሁኔታ	አካባቢዎች
ደጋማ	ከ2300 በላይ		
ወይና ደጋማ		መካከለኛ	
ቆላማ			ድሬዳዋ፣ አዋሽ ጋምቤላ
በረሀማ	ከ0-500		

<u>መልመጃ ሦስት</u> - ምንባቡን እንደገና በዝግታ አንብቡና ቀጥለው ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ

1. የኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች የአየር ሁኔታ _____ ነው።

ሀ. ቀዝቃዛና መካከለኛ የዝናብ መጠን ሐ. ከፍተኛ የዝናብ መጠንና ቀዝቃዛ

ለ. ሞቃታማና ከፍተኛ የዝናብ መጠን መ. ዝቅተኛ የዝናብ መጠንና ሞቃታማ

2. አማካይ የሙቀት፥ የትዝታዜ፥ የአየር ርጥበትና የዝናብ መጠን የአንድን አካባቢ _____ ያመለክታል።

ሀ. የአየር ንብረት ለ. የአየር ሁኔታ ሐ. መልክአ ምድረመ. አኗኗር

3. ደረቅና ሞቃታማ አካባቢዎች

ሀ. አነስተኛ የዝናብ መጠን አላቸው ሐ. እጅግ አነስተኛ የዝናብ መጠን አላቸው

ለ. በረሀማ የአየር ክልል ውስጥ ይካተታሉ መ. ለ ና ሐ መልስ ናቸው።

4. በምንባቡ መሠረት ትክክለኛው ሃሣብ የትኛው ነው?

ሀ. ከፍተኛ ቦታዎች፥ ከዝቅተኛ ቦታዎች የትኛው ነው?

ለ. ዝቀተኛ ቦታዎች ሞቃታማ ሲሆኑ፥ ከፍተኛ ቦታዎች ቀዝቃዛ ናቸው።

ሐ. የኢትዮጵያ ዝቅተኛ ቦታዎች ቆላማና በረሀማ የአየር ንብረት አላቸው።

መ. ሁሉም ትክክል ናቸው።

ድህረ-ንባብ ክንዋኔዎች

<u>መልመጃ አራት</u>

ሀ. ከላይ የሞላችሁትን ሠንጠረዥ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ በቀረበው አንቀፅ ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ሙሉ።

ደጋማ የኢትዮጵያ አየር ንብረት ክልል ከፍተኛው ከ _____ ሜትር በላይ የሆኑ ከፍተኛ አካባቢዎችን ያጠቃልላል። የአካባቢው አየር ሁኔታ _____ ሲሆን፥ _____ የዝናብ መጠን አለው። _____ ና _____ ለደጋማ የአየር ንብረት ክልል ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ።

ለ. እስኪ እናንተ ደግሞ ከላይ የቀረበውን አንቀፅ ምሳሌ በማድረግ ወይና ደጋ፥ ቆላማና በረሀማ አካባቢዎችን በተመለከተ ሠንጠረዡን መሠረት አድርጋችሁ ሦስት አንቀፆች ፃፉ።

4.3 የቅድመና ድህረ-ልምምድ የንባብ ክሂል ፈተናዎች ስታስቲካዊ ውጤት ትንተና

በጥናቱ የአጠናን ዘዴ እንደተገለፀው፥ ቅድመ-ንባብ ፣ የንባብ ወቅትና ድህረ-ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተ የትምህርት አቀራረብ በመጠቀም የተማሪዎች አንብቦ የመገንዘብ ክሂል መሻሻሉን ለመመዘን ያገለገለው ስልት ለክትትልና ለሙከራ ቡድን ተማሪዎች በተሰጡት ቅድመና ድህረ-ልምምድ ፈተና ውጤቶች መካከል የታየውን ልዩነት ማመልከት ነው።

ለዚህ እንዲረዳ በሁለቱ ፈተናዎች የተገኙ አማካይ ውጤቶች (Mean) እና ካሬ ልይይት (Variance) በማስላት ውጤቱን በቲ-ስሌት (T-test) ለማረጋገጥ ተሞክሯል። በአሰራሩ የተገኘው ውጤትም እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ስድስት - የሙከራና የክትትል ቡድን ተማሪዎች የቅድመ-ልምምድ የንባብ ክሂል ፈተና ውጤት ስታስቲካዊ ስሌት

ምድብ	አማካይ	ካሬ ልይይት	ነፃነት ደረጃ	ቲ-ስሌት	ቲ-ሠንጠረዥ	የጉልህነት ደረጃ	ጉልህ ልዩነት
የክትትል ቡድን	48.63	83.72	38	0.696	1.70	0.05	አልታየም
የሙከራ ቡድን	47.25	73.62					

P < 0.05

ሠንጠረዡ እንደሚያሳየው፥ የክትትል ቡድን ተማሪዎች የቅድመ-ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት (Mean) 48.63 ሲሆን፥ ካሬ ልይይት (Variance) ደግሞ 83.72 ነው። የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት 47.25 ሲሆን፥ ካሬ ልይይቱ ደግሞ 73.62 ሆኗል።

ይህ ውጤት በቲ-ስሌት ሲሰላ 0.696 ይሆናል። በ38 የነፃነት ደረጃ (degree of freedom) በ0.05 የጉልህነት ደረጃ (Significance Level) የ ቲ-ስርጭት ሠንጠረዥ (T-distribution table) የሚያሳየው 1.70 ነው። በዚህም በቲ-ስሌት የተገኘው ውጤት (0.696)፥ በቲ-ሠንጠረዥ ከተጠቀሰው (1.70) ያነሰ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ ውጤት ከልምምዱ በፊት በክትትልና በሙከራ ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆኑ የንባብ ክሂል ችሎታ ልዩነት እንደሌለ ያመለክታል።

በመሆኑም ሙከራውን ማካሄድ እንደሚቻል የቲ-ስሌቱ ውጤት ይጠቁማል። (የስሌቱን ዝርዝር አሰራር ከአባሪ አራት ይመልከቱ)

ሠንጠረዥ ሰባት - የክትትል ቡድን ተማሪዎች የቅድመና ድህረ-ልምምድ ፈተና ውጤት ስታስቲካዊ ስሌት፡

ፈተና	አማካይ Mean	ካሬ ልይይት S^2	ነፃነት ደረጃ deg. free.	ቲ-ስሌት T-Cal	ሠንጠረዥ ቲ-table	የጉልህነት ደረጃ Signi. level	ጉልህነት Signi. - diff
ድህረ ልምምድ	49.5	65.93	38	0.4498	1.70	0.05	አልታየም
ቅደመ ልምምድ	48.63	83.72					

P<0.05

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው፡ የክትትል ቡድን ተማሪዎች የድህረ-ልምምድ ፈተና ውጤት አማካይ (Mean) 49.5 ሲሆን፡ ካሬ ልይይቱ (Variance) ደግሞ 65.93 ነው። የቅድመ-ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤታቸው 48.63፡ ካሬ ልይይቱ 83.72 ሆኗል።

ይህ ውጤት በ38 የነፃነት ደረጃ (degree of freedom) በ0.05 ጉልህነት ደረጃ (Significance level) በቲ-ስሌት ሲሰላ ውጤቱ 0.4498 ይሆናል። በቲ-ሠንጠረዥ በተጠቀሰው የነፃነትና የጉልህነት ደረጃ የተገለፀው ዋጋ 1.70 ነው። በውጤቱም በቲ-ስሌት የተገኘው (0.4498) በቲ-ሠንጠረዥ ከተጠቀሰው (1.70) ያነሰ ሆኖ ተገኝቷል። ስለዚህ የአራተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ጉልህ ልዩነት ያላመጣ መሆኑን የቲ-ስሌቱ ውጤት ያሳያል።

ሠንጠረዥ ስምንት የክትትል ቡድን ተማሪዎች የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ስታስቲካዊ ስሌት

ፈተና	አማካይ	ካሬ ልይይት	ነፃነት ደረጃ	ቲ-ስሌት	ሠንጠረዥ	የጉልህነት ደረጃ	ጉልህነት
ድህረ ልምምድ	60.75	135.72	38	5.90	1.70	0.05	ታይቷል
ቅድመ ልምምድ	47.25	73.62					

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው፥ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የቅድመ-ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤታቸው 47.25፥ ካሬ ልይይት ደግሞ 73.62 ነው። የድህረ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤታቸው 60.75 ሲሆን፥ ካሬ ልይይቱ ደግሞ 135.72 ነው።

በዚህ መሰረት በቲ ስሌት በ0.05 የጉልህነት ደረጃና በ38 የነፃነት ደረጃ የተገኘው ውጤት 5.90 ነው። ይህ ውጤት በቲ ሠንጠረዥ ከተጠቀሰው (1.70) ውጤት የበለጠ ሆኖ ታይቷል። ይህም በአማራጭነት የቀረበው የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የንባብ ክሂልን በተሻለ መልኩ ሊያዳብር እንደሚችል ያመለክታል። ይህ ውጤት በአማራጭነት ለሙከራ የቀረበው የትምህርት አቀራረብ ውጤታማና የተሻለ መሆኑን ያሳያል። (የስሌቱን ዝርዝር ከአባሪ አራት ይመልከቱ)

በአጠቃላይ የሁለቱን ቡድኖች የቲ-ስሌት ውጤት ስንመለከት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ውጤት የተሻለ እንደሆነ እንገነዘባለን። ለውጤታቸው መሻሻል አስተዋፅኦ ያበረከተው የንባብን ክሂል በተሻለ መንገድ ለማዳበር በአማራጭነት የተዘጋጀው ቅድመ-ንባብ፥ የንባብ ወቅትና ድህረ-ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተው የትምህርት አቀራረብ መሆኑን የቲ-ስሌት ውጤት ያመለክታል። በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የንባብ ክሂል ትምህርቶች አቀራረብ ክሂሉን በተገቢው መንገድ በማዳበር፥ በደረጃው የቀረበውን የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት አንብቦ ለመገንዘብ የሚያስችል የንባብ ክሂል ባለቤት ተማሪውን ለማድረግ የሚኖረው እገዛ ዝቅተኛ እንደሆነ የጥናቱ ስታስቲካዊ ስሌት ያሳያል።

ምዕራፍ አምስት

5.1 ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ ለመግለፅ እንደተሞከረው ለጥናቱ መነሻ የሆነው መሠረታዊ ጉዳይ፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ህፃናት በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የቀረቡላቸውን የትምህርት ይዘቶች አንብበው የመገንዘብ ችሎታቸው ዝቅተኛ በመሆኑ፡ የትምህርት ውጤታቸው አጥጋቢ እንዳልሆነ በተደጋጋሚ በመምህራን ሲገለፅ መደመጡ ነው።

ጥናቱ ለዚህ ችግር በምክንያትነት ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል አንዱ፡ የመማሪያ ቋንቋው የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ በደረጃው የቀረቡ የትምህርት አይነቶች የሚጠይቁትን የንባብ ክሂል ለማዳበር ተገቢ በሆነ መልኩ በመቅረብ እገዛ ሊያደርግ አለመቻሉ ሊሆን ይችላል የሚል መላምት ይዞ ተነስቷል። ጥናቱ ከመጀመሩ በፊትም የችግሩን ስፋት ለመመልከትና መላምቱን ለማጠናከር ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተሞክሯል።

የተገኙት መረጃዎች፡ ተማሪዎቹ በደረጃቸው የቀረቡላቸውን የትምህርት ይዘቶች አንብበው የመገንዘብ ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነና የመማሪያ ቋንቋው የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብም የሚፈለገውን የንባብ ክሂል ለማዳበር ብቃት እንደሌለው በመጠቆማቸው፡ የትምህርቱን አቀራረብ በስፋት በመገምገም፡ በተሻለ መልኩ ክሂሉን ለማዳበር የሚያስችል አማራጭ የትምህርት አቀራረብ ማዘጋጀትና ውጤታማነቱን መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ከዚህ አንፃር ጥናቱ በኦሮሚያ ክልል አማርኛ መማሪያ ቋንቋቸው ለሆኑ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ከሚሰጡ የትምህርት አይነቶች መካከል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርትን በናሙናነት በመውሰድ የመማሪያ ቋንቋ የሆነው የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ፡ ትምህርቱ የሚጠይቀውን የንባብ ክሂል ለማዳበር ያለውን ብቃትና እገዛ በመገምገም በተሻለ መንገድ ሊቀርብ የሚችልበትን አማራጭ አቀራረብ ማዘጋጀትና ውጤታማነቱን መፈተሽ አላማው በማድረግ ተከናውኗል።

አላማውን ከግብ ለማድረስ፡ ጥናቱ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሞክሯል።

1. ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰጥ የአማርኛ ንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ በደረጃው የቀረበው የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቀውን የንባብ ክሂል ለማዳበር ያለው ብቃት ምን ያህል ነው?

   1.1 በአራተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የንባብ ክሂልን ለማዳበር የቀረቡ ትምህርቶች አቀራረብ ክሂሉን ለማዳበር ያላቸው ተገቢነት ምን ያህል ነው?

   1.2 በአራተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የንባብ መልመጃዎች፡ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቃቸውን የንባብ ክሂሎች ከማለማመድ አንፃር ያላቸው አጋዥነት ምን ያህል ነው?

   1.3 የአራተኛ ክፍል መምህራን የክፍል ውስጥ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ልምዳቸው ምን ይመስላል?

2. እንደ ማስተማሪያ ቋንቋነቱ ለአራተኛ ክፍል የሚሰጥ የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት ክሂሉን ይበልጥ ለማዳበር እንዴት ይቅረብ?
3. በአማራጭነት የቀረበው የትምህርት አቀራረብ ምን ያህል ውጤታማ ነው?

እነዚህን የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ፡ የአራተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ተገቢነት በመስኩ የተሰማሩ ምሁራን ካቀረቧቸው ውጤታማ የትምህርት አቀራረብ ትወራዎች አንፃር ተገምግሟል፡ በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ መልመጃዎች የሚያለማምዱዋቸው ክንዋኔዎችና በአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ ይዘቶችና መልመጃዎች የሚጠይቁት የንባብ ክንዋኔዎች ተዘርዝረው በንፅፅር ታይተዋል፡ የአራተኛ ክፍል መምህራን መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል።

የመስኩ ምሁራን ያቀረቧቸውን ሃሣቦች መሠረት በማድረግ የቅድመ-ንባብ፡ የንባብ-ወቅትና የድህረ-ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተ አማራጭ የትምህርት አቀራረብ በማዘጋጀት ውጤታማነቱ ተፈትሿል። ውጤቱም በተገቢው ስታስቲካዊ ስሌት ተተንትኖ ቀርቧል። በተገኘው ውጤትም የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ተመልሰዋል፡

1.1 በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የንባብ ክሂል ትምህርቶች አቀራረብ የንባብ ክሂልን ለማዳበር ያላቸው ብቃት

- በአራተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የንባብ ክሂል ትምህርቶች አቀራረብ፣ ተማሪውን ከቀረቡለት ምንባቦች ጋር መስተጋብር በመፍጠር ለምንና እንዴት ማንበብ እንዳለበት ሁኔታዎችን የሚያመቻችለት የቅድመ-ንባብ፣ የንባብ ወቅትና የድህረ-ንባብ እንዋኔዎች በወጉ ያላከተተ፣ ግንዛቤን ለማዳበር በሚደረግ የንባብ ሂደት ላይ ሳይሆን በተማሪው የግንዛቤ ውጤት ላይ ያተኮረ እንደሆነ የግምገማው ውጤት አመልክቷል።

የመጽሐፉ አቀራረብ ከምንባቡ በኋላ የወጡ ጥያቄዎችን በመጠየቅ በአንድ አይነት መልክ የቀረበ በመሆኑ፣ የንባብ ትምህርቱ አቀራረብ ዘልማዳዊ ከሆነው አንብቦ የማስነበብ ዘዴ ያልተላቀቀ ሆኖ ተገኝቷል። የዚህ አይነቱ አቀራረብ ደግሞ፣ ተማሪውን ከምንባብ የወጡ ቃላትና ጥያቄዎችን መፈተን እንጅ፣ የንባብ ክሂሎችን ማስተማር ባለመሆኑ (Nuttal 1982) ለተማሪዎቹ በደረጃቸው የሚያስፈልጋቸውን የንባብ ክሂል ለማዳበር የሚኖረው እገዛ ዝቅተኛ ነው ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ ይችላል።

- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የንባብ ክሂል ትምህርቶች በአብዛኛው የቃላት ፍችና ሰዋሰዋዊ ሥርዓትን ለማስተማር እንዳገለገሉ ግምገማው ያመለክታል፣ የቃላት መልመጃዎች የቃል በቃል ትርጉም የሚጠይቁ በመሆናቸው የቃላትን ፍች ከአውዳዊ አገባባቸው የመፈለግ ክሂልን የሚያለማምዱ ሆነው አልተገኙም።
- የንባብ መልመጃዎች የቀረቡበት የጥያቄ አይነት በአብዛኛው ተማሪው እውነት ሀሰት እንዲል፣ እንዲመርጥና እንዲያዛምድ የሚጠይቁ ስለሆኑ ለንባብ የማያነቃቁና የተለያዩ የንባብ ክሂሎችን ለማለማመድ የሚያስችሉ አይደሉም።
- በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ መመሪያዎችና ማስታወሻዎች ከምንባብና ከመልመጃ ተለይተው ለብቻቸው የቀረቡ በመሆናቸው ተማሪው ሊጠቀምባቸው የሚችልባቸው ሆነው አልተገኙም።

1.2 በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የንባብ መልመጃዎች የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቃቸውን የንባብ ክሂሎች ከማለማመድ አንፃር ያላቸው አጋዥነት፣

- በአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ፣ የትምህርት ይዘቶችና መልመጃዎች ተማሪውን ስዕላዊ መግለጫዎችን የማንበብ፣ የመተርጎምና ከይዘት ገለፃ ጋር አዋህዶ የመገንዘብ፣ መመሪያዎችን አንብቦ በመረዳት ሙከራዎችን የማካሄድ፣

ቻርቶችንና ካርታዎችን አንብቦ የመገንዘብ፥ በምክንያትና በውጤት መካከል ያለ ግንኙነትን የመለየት፥ በቅደም ተከተል የተከናወኑ ድርጊቶችን የማስታወስ፥ እውነታን ከግል አመለካከት የመለየት፥ ለሙያዊ ቃላት ፍች መስጠትና አጠቃላይ ሀሳብን ከዝርዝር ሃሣብ ለይቶ የመረዳት የንባብ ክሂል የሚጠይቁ ሆነው ሲታዩ፥ በአንዳሩ በቋንቋው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ መልመጃዎች ለነኝህ ክሂሎች ትኩረት ሰጥተው ከማለማመድ አኳያ የቀረቡ ሆነው አልተገኙም::

1.3 የመምህራን የክፍል ውስጥ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ

- አብዛኛዎቹ የአራተኛ ክፍል መምህራን ወቅታዊና ውጤታማ ከሆነ የንባብ ክሂል የትምህርት አቀራረብ ጋር ትውውቅ የሌላቸው እንደሆኑ ለንባብና ንባብን ስለማስተማር ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ አመልክቷል::

- መምህራኑ የንባብ ክሂል ትምህርትን ክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ፥ ተማሪዎቻቸውን ተራ በተራ በማስነሳት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ካደረጉ በኋላ ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን የማሰራት ልማዳዊ (Traditional) አቀራረብ አዘውትረው የሚጠቀሙ ሆነው ተገኝተዋል::

- ለንባብ ማስተማሪያ የሚጠቀሙባቸው ጽሑፎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ምንባቦችና መልመጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ በቀረቡበት መልክ ለውጥና ማሻሻያ ሳያደርጉ እነደሆነ በአብዛኛው መምህራን መረጋገጡን ከመጠይቁ የተገኘ ምላሽ አሳይቷል::

- በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቻቸውን የሚያለማምዱዋቸው መልመጃዎች የእካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቃቸውን የንባብ ክንዋኔዎች ለመፈፀም ድጋፍ ይሆናሉ ብለው እንደማያምኑ የሰጡት ምላሽ አመልክቷል::

በማጠቃለያው የተጠቃለሉት መረጃዎች ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበው የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ በደረጃው የቀረበው የእካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቀውን የንባብ ክሂል ለማዳበር ያለው ብቃት ዝቅተኛ ነው ማለት ያስችላሉ:: ይህንንም የጥናቱ ስታስቲካዊ ውጤት በተጨማሪ አመልክቷል::

ስታስቲካዊ ስሌቱ እንደሚያሳየው በአማርኛ መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ባለው የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተማሩት የክትትል ቡድን ተማሪዎች የድህረ-ልምምድ ፈተና ውጤት በቅድመ-ልምምድ ፈተና ካስመዘገቡት ውጤት የጎላ ልዩነት አላሳየም። ይህ ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች በመሰጠት ላይ ያለው የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት የንባብ ክሂልን በደረጃው ለማዳበር ብቁ ሆኖ አልተገኘም ወደሚል ማጠቃለያ ያደርሳል።

2. በአማራጭነት የቀረበው የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብና ውጤታማነቱ

ከመስኩ ምሁራን የተገኙ ውጤታማ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ትወራዎችን መሠረት በማድረግ በአራተኛ ክፍል ደረጃ የንባብ ክሂልን በተቻለ መልኩ ያዳብራል ተብሎ የተዘጋጀው የትምህርት አቀራረብ ውጤታማ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ለሙከራና ለክትትል ቡድን ተማሪዎች የቅድመና ድህረ-ልምምድ ፈተና ተሰጧል።

በውጤቱም የመከራ ቡድን ተማሪዎች የድህረ-ልምምድ ፈተና ውጤት ከቅድመ-ልምምድ ፈተና ውጤት የተሻለ ሆኖ ሲገኝ፥ የክትትል ቡድን ተማሪዎች የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ከቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት የጎላ ለውጥ አላሳየም።

- የክትትል ቡድን ተማሪዎች የድህረና ቅደመ ልምምድ ፈተናዎች ውጤት በቲ-ስሌት ተሰልቶ እንደታየው የፈተናዎቹ ውጤት 0.4498 ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ በቲ-ስርጭት ሠንጠረዥ ከተጠቀሰው ዋጋ (1.70) ያነሰ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ በክትትል ቡድን ተማሪዎች ቅድመና ድህረ ልምምድ የንባብ ክሂል ፈተናዎች ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል።

- የመከራ ቡድን ተማሪዎች የቅድመና ድህረ-ልምምድ ንባብ ፈተናዎች ውጤት በቲ-ስሌት ሲሰላ የፈተናዎቹ ውጤት 5.90 ሲሆን፥ በ0.05 የጉልህነት ደረጃ በቲ-ስርጭት ሠንጠረዥ ላይ ከተገለፀው ዋጋ (1.70) የበለጠ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ በቅድመና ድህረ ልምምድ የመከራ ቡድን ተማሪዎች የንባብ ክሂል ፈተናዎች ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል።

የመከራ ቡድን ተማሪዎች የድህረ-ልምምድ ፈተና ውጤት ከቅድመ-ልምምድ ፈተና ውጤት የተሻለ ሆኖ መገኘቱ፥ በአማራጭነት የቀረበው የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ በአራተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት የንባብ ክሂል ትምህርቶች

አቀራረብ በተሻለ መልኩ ክሂሉን ለማዳበር ብቃት እንዳለው የጥናቱ ስታስቲካዊ ስሌት ያሳያል።

ስለዚህ በአማራጭነት የቀረበው የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ፥ በአራተኛ ክፍል ደረጃ የቀረበው የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቀውን የንባብ ክሂል በተሻለ መልኩ ለማዳበር ያስችላል ወደሚል ማጠቃለያ ያደርሰናል።

5.2 አስተያየት

የንባብ ክሂል የሌሎች ትምህርቶች መማሪያ መሣሪያ በመሆኑ፥ ህፃናት በመደበኛ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡትን የትምህርት አይነቶች ለመከታተል በመማሪያ ቋንቋው የትምህርት ይዘቶችና አንብበው ለመገንዘብ የሚያስችል የንባብ ክሂል ችሎታ ሊኖራቸው ግድ ይላል። ለዚህ የመማሪያ ቋንቋው በትምህርትነት ሲሰጥ፥ አስፈላጊውን የንባብ ክሂል በማስጨበጥ በኩል እገዛ ሊያደርግ በሚችልበት መልኩ መቅረብ ይኖርበታል።

ህፃናቱ በደረጃቸው የቀረቡላቸውን የትምህርት ይዘቶች አንብበው ለመገንዘብ የሚያስችላቸው የንባብ ችሎታ ከሌላቸው፥ በደረጃቸው ሊያውቋቸው የሚገቡ አዳዲስ እውቀቶችንና ፅንሰ ሃሣቦችን ሳያገኙ ይቀራሉ፤ ይህ ደግሞ በአጠቃላይ የትምህርት ውጤታቸው ላይ ጫና እንደሚያደርግ ይታመናል።

ስለዚህ ይህን ችግር ገና ከስሩ ለማቃለል፥ የንባብ ክሂል ችሎታ መሠረት የሚጣልበትን የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል የማስተማሪያ ቋንቋ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብን በየጊዜው በመፈተሽ፥ ክሂሉን በተሻለ መልኩ ሊያዳብሩ የሚችሉ አማራጭ አቀራረቦችን መሞከርና በውጤቱ መሠረት ትምህርቱን ማጠናከር አስፈላጊ ይሆናል። ይህ ጥናትም በዚሁ መንፈስ የተከናወነ ነው። በዚህ መሠረት ከጥናቱ በመነሳት የሚከተሉት አስተያየቶች ተሰንዝረዋል።

1. በትምህርት ቤት ደረጃ መምህራን የቋንቋውን ትምህርት ለማስተማር ከሚጠቀሙባቸው የትምህርት መሣሪያዎች መካከል መማሪያ መፃሕፍት ዋነኞቹ ናቸው። በዚህ ጥናትም፥ አብዛኛዎቹ መምህራን ንባብን ለማስተማር የሚጠቀሙት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉ ምንባቦችንና መልመጃዎችን በመጽሐፉ ውስጥ በቀረቡበት መልክ እንደሆነ መመልከት ተችሏል። መምህራኑ ዘወትር መማሪያ መጽሐፉን ብቻ ለመጠቀም ከተገደዱባቸው ምክንያቶች መካከል አንዱ ከወቅታዊ የንባብ ጽንሰ ሃሣባዊ ግንዛቤዎችና ውጤታማ የንባብ ትምህርት

አቀራረብ ጋር ትውውቅ ስለሌላቸው እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡ ስለዚህ መምህራን ከመማሪያ መጽሐፍ ጥገኝነት ተላቀው በራሳቸው ዝግጅት ክሂሉን በተሻለ መልኩ ማስተማር እንዲችሉና በዚህ ጥናት ውጤታማነቱ የተረጋገጠውን የትምህርት አቀራረብ ወደፊት ለመጠቀም፡ መምህራንን ከወቅታዊ የንባብ ግንዛቤና የትምህርት አቀራረብ ጋር ማስተዋወቅ ያስፈልጋል።

ለዚህም በሥራ ላይ ላሉ መምህራን በኮርስ፡ በወርክሾፕና በትምህርታዊ መጽሔቶች፡ ለዕጩ መምህራን ደግሞ በስልጠናቸው ወቅት የመስኩ ምሁራን ካስተዋወቋቸው ወቅታዊና ውጤታማ የንባብ ግንዛቤዎችና የትምህርት አቀራረብ ጋር የሚተዋወቁበትን መንገድ የትምህርት ቢሮው ሊያመቻችና ሊያስተዋውቅ ይገባል።

2. በዚህ ጥናት ናሙናነት እንደታየው፡ አማርኛ የማስተማሪያ ቋንቋ በሆነባቸው የክፍል ደረጃዎች የቀረቡ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍት የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ በደረጃቸው የቀረቡ ሌሎች ትምህርቶችን የሚጠይቁትን የንባብ ክሂሎች ለማዳበር ብቃት እንደሌላቸው ይገመታል፤

ስለዚህ መማሪያ መጽሐፍቱን የሚያዘጋጅ ባለሙያዎች በዝግጅት ወቅት በየደረጃው የሚሰጡ ሌሎች የትምህርት አይነቶች የሚጠይቁትን የንባብ ክሂሎች ቀድመው በመለየትና ክሂሎችን ለማለማመድ የሚያስችል ውጤታማ የንባብ ክሂል ትምህርት እንዴት እንደሚቀርብ በማጥናት እንደገና መጽሐፍቱን በአዲስ መልክ ቢያዘጋጅ፡ ለዚህም የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ትኩረት ቢሰጥ፡ ተማሪዎች በደረጃቸው የቀረቡላቸውን የትምህርት ይዘቶች አንብበው ለመገንዘብ የሚያስችላቸውን የንባብ ችሎታ በማዳበር፡ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ መርዳት ይቻላል።

3. ይህ ጥናት ከማስተማሪያ ቋንቋነት አንፃር ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰጥ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ተለምዷዊ ከሆነው አንብቦ የማስነበብ አቀራረብ ተላቆ ተገቢ በሆነ አቀራረብ የሚጠናከርበትን መንገድ ማመላከት ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ፡ በዚህ ጥናት መነሻነት አማርኛ የማስተማሪ ቋንቋ በሆኑባቸው ለሌሎች የክፍል ደረጃዎች የሚሰጡ የንባብ ትምህርት አቀራረቦች ላይ ግምገማ በማካሄድ፡ ክሂሉን በተሻለ መልኩ ሊያዳብሩ የሚችሉ አማራጭ አቀራረቦች ተዘጋጅተው ቢሞክሩ የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ማዳበር ወደሚያስችል አስተማማኝ የትምህርት አቀራረብ ተጠቃሚ ወደመሆን ደረጃ ለማምራት ያስችላል።

ማጣቀሻ

Badrawi, N. (1992) "The Reading Dilemma: Meeting Individual Needs." English Teaching Forum. 30:3.

Carin, Artbur. (1997) Teaching Modern Science. (7th ed.) Newjercey: Prentice Hall Inc.

Carrell, P., Devine, J. and Eskey, D. (eds). (1988) Interactive Approaches to Second Language Reading. Cambridge: Cambridge University Press.

Carrell, P. and Eisterhold, J.C. (1988) "Schema Theory and ESL Reading Peadagoy." In Carrell, P., Devine, J. and Eskey, D. (eds.) Cambridge: Cambridge University Press. 73-92.

Carrell, P. (1984) "Schema Theory and ESL Reading Calssroom Implications and Applications." The Modern Language Journal. 68:4, 332-341.

Celce-Murcua, M. (eds.) (1991) Teaching English as a Second or Foreign Language (2nd ed.). Bosten: Hinle and Hine Publisher Ltd.

Cross, David. (1995) A Practical Hand Book of Language Teaching. London: McHall Macmillan.

Cushenbery, Donald C. (1985) Improving Reading Skills in the Content Area. Omaha: Charles C. Thomas.

Eskery, D.E. (1988) "Holding in the Bottom: An Introduction Approach to the Language Problems of Second Language Readers." in Carrell, P., Devine, J. and Eskey, D.E. (eds.) 93-100.

Eskey, D.E. and Grabe, N. (1988) "Interactive Models for Second Language Reading: Perspective on Instruction." In Carrell, P., Devine, J. and Eskey, D. (eds.) 223-238.

Goodman, K. (1967) "Reading: Apsycholinguistic Guessing Game." In Singer, H. and Rudell, R. (eds.) Theoretical Models and Processes of Reading. (2nd ed.) Newyork, DE: International Reading Association. 497-508.

Grant, N. (1987) Making Most out of your textbook: Newyork: Longman.

Greenwood, J. (1988) Class Reader. Oxford: Oxford University Press.

_____ (1981) "Comprehension and Reading." In Abbott, G. and Wingard, P. (eds.) Teaching of English as an International Language: A Practical Guide. Oxford: Oxford University Press.

Grellet, F. (1981) Developing Reading Skills: A Practical Guide to Reading Comprehensive Exercises. Cambridge: Cambridge University Press.

Harmer, Jermy. (1991) The Practice of English Language Teaching. London: Longman.

Harrison, C. and Gardner, K. (1977) "The Place of Reading." in Marland, M. (ed.) Language Across the Curriculum. London: Heinemann Educational book Ltd. 80-103.

Jarolimek, J. and Foster, C. (1997) Teaching and Learning in Elementay School. Newsjersey: Prentice Hall. Inc.

Johnson, P. (1982) "Effects on Reading Comprehension of Building Background Knowledge." TESOL Quarterly. 16:4, 503-516.

Johnsten, B. (1988) "Active Reading." Modern English Teacher Journal. 16:1.

Marland, M. (1977) Language Across the Curriculum. London: Heinemann Educational books Ltd.

Meu-yun, yue. (1997) "Teaching Efficient EFL" in Karal, T. (ed.) Teacher Development: Making the Right Moves. Washington, D.C: United States Information Agency.

Nunan, David. (1989) Designing tasks for the Communicative Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Nuttal, C. (1982) Teaching Reading Skills in a Foreign Language. London: Heineman Educational Books Ltd.

Papalia, Anthony. (1987) "Interaction of reader and text." in Rivers, W.M. (ed.) Interactive Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Rivers, Wilga M. (1986) Teaching Foreign Language Skills. Chicago: University of Chicago Press.

_____ (ed.) (1987) Interactive Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Silberstein, S. (1994) Techniques and Resources in Teaching Reading. Oxford: Oxford University Press.

Smith, F. (1982) Reading. (2nd ed.) Cambridge: Cambridge University Press.

Ur, Penny. (1996) A Course in Language Teaching: Practice and Theory. Cambridge: Cambridge University Press.

Vale, D. and Ann, F. (1995) Teaching Children English. Cambride: Cambridge University Press.

Wallace, C. (1992) Reading. Oxford: Oxford University Press.

Williams, Ray, (1986) "Top Ten Principles for Teaching Reading." ELT Journal. 40:1 42-45.

Williams, Eddie. (1984) Reading in the Language Classroom. London: Macmillan.

ሰለሞን ሀለፎም። (1990) "በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት የንባብ ክሂልን እንዴት ማዳበር ይቻላል?" መጽሔተ-ትምህርት። በትምህርት ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ። 4÷6።

ሰናይት ከበደ። (1974) "ከ66 ወዲህ የአንደኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዞታ።" በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።

ነገሠ ገ/ዓድቅ። (1989) "በ1987 ለክልል 14 የተዘጋጀው የ5ኛ ክፍል የሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ የቋንቋ አጠቃቀም በደረጃው ካለው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አንፃር።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ÷ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።

የሻነው ታደሰ። (1980) "የአንደኛ ደረጃ አማርኛ ከ1ኛ - 6ኛ ባሉት ክፍሎች ለሚቀርቡ ለሂሣብ÷ ለሳይንስ÷ ለህብረተሰብ ማስተማሪያ ቋንቋ ያለው ድጋፍ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ÷ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።

አሮሚያ ትምህርት ቢሮ። (1991) የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አራተኛ ክፍል። ፌንፊኔ። በአሮሚያ ትምህርት ቢሮ የሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/መምሪያ የተዘጋጀ።

_____። (1991) የአከባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ አራተኛ ክፍል። ፌንፊኔ። በአሮሚያ ትምህርት ቢሮ የሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/መምሪያ የተዘጋጀ።

ክብረት

አባሪ አንድ - ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሑፍ ክፍል
የድህረ-ምረቃ መርህ-ግብር

በአራተኛ ክፍል መምህራን የሚሞላ መጠይቅ

ውድ መምህር - የዚህ መጠይቅ ዓላማ፥ አማርኛ መመሪያ ቋንቋቸው ለሆኑ የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው ሳይክል የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰጥ የአማርኛ ንባብ ትምህርት አቀራረብ፥ በደረጃው የሚሰጠው የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቀውን የንባብ ክሂል ለማዳበር ያለውን ተገቢነት በመገምገም፥ አማራጭ የትምህርት አቀራረብ ለማዘጋጀት የሚያግዝ መረጃዎች ለማሰባሰብ ነው። አላማው ከግብ እንዲደርስ የሙያው ባለቤቶችን ድጋፍ የሚጠይቅ በመሆኑ፥ እርስዎም ይህን መጠይቅ በመሙላት የበኩልዎን ሙያዊ ድጋፍ እንዲያደርጉ አጥኚው በትህትና ይጠይቃል።

መምህር ሆይ - እጅግ ውድ የሆነውን ጊዜዎን ሰውተው መጠይቅ በመሙላት ለሚያደርጉት ትብብር ምስጋናዬ በቅድሚያ ይድረስዎ።

ማሳሰቢያ - መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም
- በጽሑፍ እንዲመልሱ ከተጠየቁት ጥያቄዎች በስተቀር በምርጫ ለቀረቡት ጥያቄዎች የሚሰጡትን መልስ በተዘጋጀው ቦታ x ምልክት በማድረግ ይመልሱ

ክፍል አንድ

ከዚህ በታች ለተጠየቁት መረጃዎች ትክክለኛውን መረጃ በተተውት ባዶ ቦታዎች ሙሉ::

1. ፆታ _____
2. ዕድሜ _____
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ _____
4. የትምህርት ደረጃ _____
5. የአገልግሎት ዘመን _____

ከተራ ቁጥር 6 - ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መረጃዎችን ከተሰጡት አማራጮች x ምልክት በማድረግ ያመልክቱ::

6. መደበኛ የመምህርነት ስልጠና ወስደዋል?
   ሀ. ወስጃለሁ ለ. አልወሰድኩም

7. ከመደበኛ ስልጠናዎ በኋላ በተጨማሪ የሙያ ማሻሻያ ኮርስ ወስደዋል?
   ሀ. ወስጃለሁ ለ. አልወሰድኩም

8. አማርኛን ከ1ኛ - 4ኛ ባሉት ክፍሎች አስተምረዋል?
   ሀ. አስተምሪያለሁ ለ. አላስተማርኩም

9. ከአማርኛ ሌላ በተጨማሪ የሚያስተምሩት የትምህርት አይነት አለ
   ሀ. አለ ለ. የለም

10. ለ 9ኛው ጥያቄ መልስዎ "አለ" ከሆነ የትምህርቱን ወይም የትምህርቶቹን አይነት ይጠቀሱ _____
    _____
    _____

ክፍል ሁለት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ያልዎትን አመለካከት በመምረጥ ይግለፁ

1. በመምህራን ማሰልጠኛ የወሰዱት ስልጠና የንባብ ክሂልን ለማስተማር አግዞታል?

   ሀ. አግዞኛል ለ. አላገዘኝም

2. አብዛኛዎቹ ተማሪዎችዎ ለደረጃቸው የቀረቡላቸውን የትምህርት አይነቶች አንብበው የመግንዘብ ችሎታ አላቸው ብለው ያምናሉ

   ሀ. አላቸው ለ. የላቸውም

3. ለጥያቄ 2 የሰጡት መልስ "ለ" ከሆነ ምክንያቱ ምንድነው ይላሉ?

   _____

   _____

   _____

4. አብዛኞቹ ተማሪዎች ያላቸውን የንባብ ክሂል ችሎታ ደረጃ፥ ከቀረቡት አማራጮች መካከል በመምረጥ፥ ሰንጠረዥ ውስጥ x በማድረግ ይግለፁ

ተራ ቁጥር	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቀተኛ	በጣ ዝቅተ
ሀ	ያነበቡትን ምንባብ የማስታወስ ችሎታቸው ምን ያህል ነው?					
ለ	ከምንባብ የወጡ የግንዛቤ ጥያቄዎችን የመስራት ችሎታቸው ምን ያህል ነው?					
ሐ	መመሪያዎችን ወይም ትዕዛዞችን አንብበው በተግባር የመተርጎም ችሎታቸው ምን ያህል ነው?					
መ	ግራፎችን፥ ሰንጠረገሮችን፥ ስዕላዊ መግለጫዎችን የማንበብና የመተርጎም ችሎታቸው ምን ያህል ነው?					
ሠ	አጠቃላይ ሃሳብን ከዝርዝር ሃሳብ የመለየት ችሎታቸውስ እንዴት ነው?					
ረ	የአንድን ጽሑፍ ቀጣይ ሃሳብ የመገመት ችሎታቸው ምን ያህል ነው?					

5. ለአራተኛ ክፍል በተዘጋጁ የአማርኛና የአካባቢ ሳይንስ ማስተማሪያ መጻህፍት መካከል ግንኙነት አለ ይላሉ?

ሀ. አለ ለ. የለም

6. ግንኙነት አላቸው የሚሉ ከሆነ ግንኙነታቸው በይበልጥ ከሚታይበት በመጀመር በደረጃ 1፣ 2፣ 3፣ በማለት በተሰጠው ክፍት ቦታ በመግፍ ያመልክቱ

ሀ. በቃላት አጠቃቀም _____

ለ. በዐ.ነገር አወቃቀር _____

ሐ. በይዘት _____

መ. በሀሳብ አደረጃጀት _____

ሠ. ሌላ _____

7. በአራተኛ ክፍል አማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የንባብ ክሂልን ለማዳበር ታስበው የቀረቡ መልመጃዎች የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚጠይቀውን የንባብ ክሂል ለማዳበር ያግዛል?

ሀ. አዎ ያግዛል ለ. አያግዝም

8. ለ7ኛው ጥያቄ የሰጡት መልስ ለ ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው ይላሉ? ይግለፁ

_____

_____

_____

9. በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎችን የሚያለማምዱዋቸው የንባብ መልመጃዎች በአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሚቀርብላቸውን መልመጃ እንዲሰሩ ያግዛሉ?

ሀ. ያግዛሉ ለ. አያግዙም

10. ለጥያቄ 15 የሰጡት መልስ "ያግዛሉ" ከሆነ ምን ያህል ያግዛሉ ይላሉ?

ሀ. በጣም በከፍተኛ ደረጃ መ. በዝቅተኛ ደረጃ

ለ. በከፍተኛ ደረጃ ሠ. በጣም ዝቅተኛ ደረጃ

ሐ. በመካከለኛ ደረጃ

11. ቀጥለው ስለ ንባብና ስለማስተማር በቀረቡት ሃሳቦች የሚስማሙበትን ደረጃ በመምረጥ በሰንጠረዥ ውስጥ x በማድረግ ያመልክ

ተራ ቁጥር	ጥያቄ	በጣም እስማማለሁ	እስማማለሁ	ለመወሰን ያስቸግረኛል	እቃወማለሁ	በጣም እቃወማለሁ
ሀ	ንባብ ማስተማር የአማርኛ /የቋንቋ/ መምህር ተግባሩና ሃላፊነት ብቻ ነው።					
ለ	ማንበብ አንድን ጽሑፍ ከዳር እስከ ዳር መውጣት ማለት ነው።					
ሐ	የትምህርት ይዘቶችን አንብቦ የመገንዘብ ችሎታን ለማዳበር የተለያዩ የንባብ ስልቶችን ማስተማር ያስፈልጋል።					
መ	በአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡ ምንባቦች የወጡ ጥያቄዎችን ብቻ በማሰራት የንባብ ክሂልን ማዳበር ይቻላል።					
ሠ	ተማሪዎች የቀረበላቸውን ጽሑፍ አንብበው ለመረዳት በጽሑፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት በሙሉ የግድ ማወቅ አለባቸው					
ረ	ለንባብ የቀረበውን ጽሑፍ ቃላት፥ ሐረግ፥ ዐ.ነገር ደረጃ በደረጃ እያሳወቁ አጠቃላይ የፅሑፉን ሃሳብ እንዲገነዘቡ ማድረግ የንባብ ክሂልን ለማሳደግ የሚመረጥ መንገድ ነው።					

ክፍል ሦስት

የማስተማር ልምድና የትምህርት አቀራረብ

ከዚህ በታች በማስተማር ልምድዎ ያካበቱትን የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብዎን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፤ ጥያቄዎቹን ለመመለስ የተሰጡትን መመሪያዎች እየተከተሉ ይመልሱ።

1. ለንባብ ማስተማሪያ የሚጠቀሙባቸውን ጽሑፎች /ምንባቦች/ ከየት እንደሚወስዷቸው፥ አዘውትረው ከሚጠቀሙት በመጀመር በደረጃ 1፥2፥3... በማለት ይገለፁ

   ሀ. በአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦችን

   ለ. ሌሎች ትምህርቶች ይዘታቸውን ለማስተላለፍ ያቀረቧቸውን ምንባቦች

   ሐ. ጋዜጣዎችና መጽሔቶችን

   መ. ራስዎ ያዘጋጅዋቸውን ጽሑፎች

   ሠ. ሌላ ካለ ይጠቀሱ

   _____

   _____

   _____

2. በአራተኛ ክፍል አማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦችና መልመጃዎች፡ የንባብ ክሂልን ለማዳበር ለትምህርት ሲያቀርቡ እንዴት ይጠቀማሉ?

ሀ. በማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በቀረቡበት መልክ

ለ. መጠነኛ ማሻሻያና ለውጥ በማድረግ

ሐ. ሙሉ በሙሉ በመለወጥ

መ. ሌላ _____

_____

3. ለጥያቄ ሁለት የሰጡት መልስ "ለ" ወይም "ሐ" ከሆነ የሚያደርጉለትን ለውጥና ማሻሻያ ይግለፁ

_____

_____

_____

4. ምንባቦችን ለንባብ ክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ፡ የአቀራረብ ልምድዎን ከሚጠቀሙበት ጊዜ አንፃር ከቀረቡት ምርጫዎች ውስጥ በመምረጥ በ x ምልክት ያመልክቱ

ተራ ቁጥር	አቀራረብ	አዘውትሬ እጠቀማለሁ	አብዛኛውን ጊዜ	አልፎ አልፎ	አንዳንድ ጊዜ	ፈፅሞ አልጠቀምም
1	መጀመሪያ ራስዎ ካነበቡላቸው በሁዋላ ተማሪዎችን					
2	ተማሪዎችን ተራ በተራ እያነሱ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ማድረግ፡					
3	ተማሪዎቹ በየግላቸው ድምፃቸውን ሳያሰሙ እንዲያነሱ ማድረግ፡					
4	በጥንድና በቡድን ሆነው እንዲያነቡ ማድረግ፡					
5	ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ለመነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎች በማቅረብ ማወያየት፡					
6	የተማሪዎቹን የንባብ ሂደት ሊያደናቅፉ የሚችሉ አዳዲስ ቃለአትን ከንባብ በፊት ለትምህርት ማቅረብ፡					
7	ምንባቡ ከተነበበ በሁዋላ ከምንባቡ የወጡ የቃላትና የግንዛቤ መልመጃዎች ማሰራት፡					
8	ተማሪዎቹ የሰሯቸውን መልመጃዎች በቡድንና በጥንድ ሆነው እንዲያስተያዩ ማድረግ					
9	ከምንባቡ በመነሳት ከእካባቢያቸው ወይም ከሌላ ትምህርት ጋር የተያያዙ መልመጃዎች ማቅረብ					
10	የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን ለንባብ ማቅረብና ማስነበብ፡					

5. ቀጥለው በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ያለዎትን አስተያየት ይግለፁ?

ሀ. አጠቃላይ የተማሪዎች የንባብ ችግር ምክንያት ምንድን ነው ይላሉ?

_____

_____

ለ. ችግሩን ለማቃለልና የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሳደግ ምን መደረግ አለበት?

_____

_____

ለትብብርዎ አመሰግናለሁ

አባሪ ሁለት - ለክትትልና ሙከራ ቡድን ተማሪዎች የተሰጡ ቅድመና ድህረ ልምምድ የንባብ ፈተናዎች

ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የቅድመ-ልምምድ የአማርኛ ንባብ ፈተና

ስም _____ ክፍል _____ ኮድ _____

አጠቃላይ መመሪያ

- ይህ ፈተና አንብቦ መገንዘብን የሚጠይቁ 20 ጥያቄዎችን ይዟል
- ጥያቄዎቹ፥ እውነት ሀሰት፥ ክፍት ቦታዎችን መሙላትና የምርጫ ጥያቄዎች ናቸው::
- ጥያቄዎቹ የሚመለሱት ለመልስ መስጫ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ነው::
- ጥያቄዎቹን ለመስራት የተፈቀደው ጊዜ 40 ደቂቃ ነው::

ምንባብ
የኢትዮጵያ ምልክአ ምድር

መልክአምድር በአጭሩ የምድር መልክ ማለት ነው:: የምድራችን መልክ ወጣ ገባ የበዛበት፥ አቀበትና ቁልቁለት የሚታይበት ነው:: አለፎ አለፎ ሜዳማ አካባቢዎችንም እናገኛለን::

ከፍተኛ ሥፍራዎች የሚባሉት ተራሮችና አምባ ምድሮች (ፕላቶዎች) ሲሆኑ፥ ዝቅተኛ ሥፍራ የሚባሉት ደግሞ ሜዳዎች፥ ረባዳ ቦታዎችና ሸለቆዎች ናቸው::

ኢትዮጵያ ተራራማ ከሚባሉት አገሮች አንድዋ ናት:: አብዛኛው መሀል ኢትዮጵያ በተራሮችና በአምባ ምድሮች የተያዘ ነው፤ ይህ ከ 1500 ሜትር በላይ ያለውን ወይና ደጋማ፥ ደጋማና ውርጫማ ቦታዎችንም ሁሉ ይሸፍናል::

በኢትዮጵያ ከ 4000 ሜትር በላይ ከፍታ ያላቸው ብዙ ተራራዎች ይገኛሉ፤ ተራራዎቹንና መገኛቸውን ከሚከተለው ሠንጠረዥ ተመልከቱ

ተራ ቁጥር	የተራራው ስም	ከፍታ በሜትር	የሚገኝበት ክልል	የሚገኝበት ዞን
1	ራስ ዳሽን	4620	አማራ	ሰሜን ጎንደር
2	አቡነ ዮሴፍ	4191	አማራ	ወሎ
3	ባቱ	4370	ኦሮሚያ	ባሌ
4	ካካ	4190	ኦሮሚያ	አርሲ
5	ጉጌ	4200	ደቡብ	ሰሜን ኦሞ
6	ሜጫላሎ	4139	ኦሮሚያ	አርሲ
7	ጉና	4231	አማራ	ደቡብ ጎንደር
8	ፎጫቄ	4100	አማራ	ጎጃም

የኢትዮጵያ ዝቀተኛ ሥፍራዎች፥ በአጠቃላይ ከ 1500 ሜትር በታች የሚገኙትን ቆላማና በረሀማ ቦታዎች ያጠቃልላሉ። እነዚህ ስፍራዎች በአብዛኛው በጠረፍ አካባቢ የሚገኙ ናቸው። ከሁሉም ዝቅተኛ ቦታ ዳሉል ወይም ከባር ስምጥ የሚባለው ነው። ቦታውም በአፋር ክልል ውስጥ ይገኛል።

ሸለቆአማ ስፍራዎች ሁለት አይነት ሲሆኑ፥ ሁለቱም አይነቶች በኢትዮጵያ ይገኛሉ። አንደኛው በወንዞች አማካይነት ከመሸርሸሩ የተነሳ የሚፈጠር ነው። ለምሳሌ ያህል የአባይ፥ የአዋሽ፥ የተከዜ፥ የኦሞ የገናሌና የዋቢ ሸበሌ ወንዞች የሚፈጠሩት ሸለቆአማ ስፍራዎች መጥቀስ እንችላለን። ሁለተኛው ስምጥ ሸለቆ የሚባለው ነው። ይህ ሥፍራ በመሬት ውስጣዊ ሃይል የተነሳ በውጥረት ብዛት የላይኛው የመሬት ክፍል ተሰንጥቆ ሲሰምጥ ወይም ሲያብጥ የሚፈጠር ነው። አገራችንን ከሰሜን ምስራቅ እስከ ደቡብ ምዕራብ <u>የሚዘልቀው</u> ስምጥ ሸለቆ አንዱና ዋነኛው ነው።

መመሪያ አንድ - ቀጥለው የቀረቡት ሃሣቦች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ እውነት፥ ስህተት ከሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት በተሰጠው ክፍት ቦታ በመፃፍ ግለፁ

_____ 1. የኢትዮጵያ ከፍተኛ ሥፍራ ራስዳሽን ይባላል።

_____ 2. መልክአ-ምድር ከፍተኛና ዝቅተኛ ቦታዎችን ያጠቃልላል።

_____ 3. በጠረፍ አካባቢ የሚገኙ ቦታዎች በሙሉ ዝቅተኛ ቦታዎች ናቸው።

_____ 4. የመሀል ኢትዮጵያ አካባቢዎች ተራራና አምባ ምድሮች ይበዙበታል።

መመሪያ ሁለት - ከዚህ ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ የሆነውን በመምረጥ ፊደሉን በተሰጠው ቦታ ፃፉ::

_____ 5. በኢትዮጵያ በጣም ዝቅተኛው ስፍራ የሚገኘው_____ ነው?

ሀ. በአማራ ክልል ለ. በአፋር ክልል ሐ. በዳሎል መ. ፎጫቄ

_____ 6. አብዛኛው የመሀል ኢትዮጵያ አካባቢዎች

ሀ. ወይና ደጋማና ውርጫማ ናቸው ለ. በተራሮችና በእምባ ምድሮች የተያዘ ነው::

ሐ. ከ 1500 ሜትር በላይ ከፍታ አላቸው መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

_____ 7. በሦስተኛው አንቀፅ ውስጥ ይህ የሚለው ቃል የሚያመለክተው___ ነው

ሀ. ከ 1500 ሜትር በላይ የሆኑ አካባቢዎችን

ለ. በተራሮችና በእምባ ምድሮች የተያዙ የመሀል ኢትዮጵያ አካባቢዎች

ሐ. ረባዳ ቦታዎችን

መ. የኢትዮጵያ ተራራማ አካባቢዎችን

_____ 8. ለስምጥ ሸለቆ መፈጠር ምክንያት የሚሆነው ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ. መሬት በወንዞች መሸርሸር

ለ. በመሬት ውስጣዊ ሃይል የመሬት የላይኛው ክፍል መሰንጠቅና መስመጥ

ሐ. በመሬት ማበጥ

መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

_____ 9. ከሰሜን ምስራቅ እስከ ደቡብ ምዕራብ የሚዘልቅ ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. የሚደርስ ለ. የሚያቋርጥ ሐ. የሚሰነጥቅ መ. የሚያልፍ

_____10. ከ1500 ሜትር በታች_____

ሀ. የኢትዮጵያ ዝቅተኛ ቦታዎችን ከፍታ አጠቃላይ መግለጫ ነው::

ለ. ቆላማና በረሀማ የኢትዮጵያ ሥፍራዎችን ከፍታ መግለጫ ነው::

ሐ. በጠረፍ አካባቢ የሚገኙ የአብዛኛዎቹን አካባቢዎች ከፍታ መግለጫ ነው::

መ. የሁሉም መግለጫ ሊሆን ይችላል::

_____11. ዝቅተኛው የኢትዮጵያ ስፍራ_____ ይባላል::

ሀ. አፋር ለ. ዳሎል ሐ. ከባር መ. ለ ና ሐ

_____12. በምንባቡ ውስጥ በኢትዮጵያ ከ4000 ሜትር በላይ ከፍታ ያላቸው ስንት ተራራዎች ቀርበዋል::

ሀ. አራት ለ. ሦስት ሐ. ስምንት መ. አይታወቅም

_____13. አቀበት ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍች የሚሆነው_____ ነው::

ሀ. ዳገት ለ. ተራራማ ሐ. ገደል መ. ረባዳ

_____14. ምንባቡ የኢትዮጵያን መልክአምድራዊ ሁኔታ ያቀረበው_____

ሀ. ከፍተኛ፥ ዝቅተኛና ሸለቆአማ በማለት ነው::

ለ. ከፍተኛና ዝቅተኛ ቦታዎች በማለት ነው።

ሐ. ተራራዎች፥ አምባ ምድሮችና ሜዳማዎች በማለት ነው።

መ. ሁሉም ነው።

_____15. የምንባቡ አጠቃላይ ሃሣብ ምንድን ነው?

ሀ. መልክአምድር ማለት ምን ማለት እንደሆነ መግለፅ

ለ. የኢትዮጵያን የመሬት አቀማመጥ ሁኔታና ሥፍራዎች መግለፅ

ሐ. የኢትዮጵያ ተራራዎች የሚገኙበትን አካባቢና ከፍታ መግለፅ

መ. የኢትዮጵያን ከፍተኛና ዝቅተኛ አካባቢዎችን ከፍታ መግለፅ

መመሪያ ሦስት - ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች በምንባቡ ውስጥ የቀረበውን ሠንጠረዥ መሠረት በማድረግ አሟሉ።

16. ትልቁ ተራራ _____ ሲባል ከፍታውም _____ ነው፤ ትንሹ ደግሞ _____ ሲሆን _____ ከፍታ አለው።

17. በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ተራራዎች _____፥ _____ ና _____ ናቸው።

18. ብዙ ተራራዎች የሚገኙበት ክልል _____ ነው

19. በደቡብ ክልል የሚገኘው _____ ተራራ ከፍታው _____ ሜትር ነው።

20. በከፍታው ሶስተኛ የሆነው ተራራ ከፍታው _____ ሲሆን የሚገኘውም _____ ነው።

ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ንባብ ፈተና

ስም _____ ክፍል _____ ኮድ _____

<u>አጠቃላይ መመሪያ</u>

- ይህ ፈተና አንብቦ መገንዘብን የሚጠይቁ 20 ጥያቄዎችን ይዟል።
- ጥያቄዎቹ፥ በሠንጠረዥ ውስጥ የተተው ክፍት ቦታዎችን መሙላት፥ እውነት ሀሰትና የምርጫ ጥያቄዎች ናቸው።
- ጥያቄዎቹ የሚመለሱት በጥያቄ ወረቀቱ ለመልስ መስጫ በተዘጋጀው ቦታ ነው።
- ጥያቄዎቹን ለመስራት የተፈቀደው ጊዜ 40 ደቂቃ ነው።

መመሪያ አንድ - ከዚህ በታች የተሟላ መረጃዎችን ያልያዘ ሠንጠረዥ ቀርቧል፡ ምንባቡን ካነበባችሁ በኋላ በምታገኙት መረጃ መሠረት በክፍት ቦታዎች ያሉትን ቁጥሮች በመተካት ሠንጠረዡን አሟሉ

የማዕድናት ስም	የሚገኝበት የምግብ አይነት	ጠቀሜታው
ካልሲየም	አይብና ወተት	1
አዮዲን	2	የእንቅርት በሽታን መከላከል
ብረት	3	4
ፎስፈረስ	5	አጥንትና ጥርስ ተስተካክለው እንዲያድጉ
ክሎሪን	አሳ፥ የምግብ ጨው	6

1. _____
2. _____
3. _____
4. _____
5. _____
6. _____

ምንባብ አራት

ማዕድናት

ሰውነታችን ተግባሩን በሚገባ ማከናወን እንዲችልና ጤንነታችን የተሟላ እንዲሆን የተመጣጠነ ምግብ ማግኘት አለብን። የተመጣጠነ ምግብ የሚባሉት የወተት፥ የሥጋ፥ የቅጠላ ቅጠልና የፍራ ፍሬ፥ የዳቦና የጥራጥሬ የምግብ ክፍሎች ናቸው። <u>ከነዚህ</u> የሚገኙ ንጥረምግቦች ከሚሰጡት ጠቀሜታ አኳያ በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍለዋል። ከንጥረ ምግቦቹ መካከል የማዕድናት ክፍል አንዱ ነው።

ማዕድናት ለሰውነታችን አስፈላጊ ከሆኑ ንጠረ ነገሮች መካከል ዋንኞቹ ናቸው። እነርሱም ብረት ኢስቴኔያዊ ወይም ኢ-ብረት ኢስቴኔያዊ ንጥረ ነገሮች የሚገኙባቸው ንጥረ ምግቦች ናቸው። እነዚህ ምግቦች አካላችን በሽታን እንዲቋቋም የሚረዱ ናቸው።

የሰውነታችን ሶስት ከመቶ የሚሆነው ክፍል የተሰራው ከማዕድናት ነው። በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ማዕድናት መካከል፥ ካልሲየም፥ ፎስፎረስ፥ ፖታሲየም፥ ድኝ፥ ሶዲየም፥ ክሎሪን፥ ብረት፥ አዮዲን፥ መዳብና ማግኒዚየም ዋንኞቹ ናቸው። እነዚህም በሰውነታችን ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ።

ለአብነት ያህል የምንተነፍሰው ንፁህ አየር በደም ውስጥ እንዲዘዋወር፥ ኦክስጅንና ካርቦን ዳይኦክሳይድን አመላላሽ የሆነው ቀይ የደም ህዋስ እንዲበዛ የሚረዳ የብረት ማዕድን ነው። አጥንትና ጥርስ ተስተካክለው እንዲያድጉና እንዲገነቡ የሚያደርጉት ካልሲየምና ፎስፎረስ ናቸው፤ ካልሲየም በተጨማሪ ነርቭና ጡንቻ በሚገባ እንዲሠራ፥ የልብ አመታት እንዲስተካከል፥ ደም እንዳይረጋ የሚያደርግ ህዋስ በመፍጠር ያገለግላል።

ማዕድናት የእንስሳትና የዕፅዋት ውጤት ካልሆኑ ምግቦች ይገኛሉ። የወተት ክፍል ምግቦች በተለይም፥ አይብና ወተት በካልሲየም የበለፀጉ ናቸው። ካልሲየም በአነስተኛ መጠን በእንቁላል በብርቱካንና በጎመን ውስጥ ይገኛል። ፎስፎረስ በብዛት የሚገኘው ከሥጋ፥ ከአትክልት፥ ከወተትና ከአሳ ነው። ከጥራጥሬና ከለውዝ አነስተኛ መጠን ፎስፎረስ ይገኛል። ክሎሪንና አዮዲን በአሳና በምግብ ጨው ውስጥ ሲገኙ፥ በባህር ውስጥ የሚበቅሉ ቅጠላ ቅጠሎች ለአዮዲን ምንጭ ናቸው። የብረት ማዕድን ከእንጀራ፥ ከጉበት፥ ከእንቁላል አስኳልና ከቅጠላ ቅጠል ይገኛል። እነኝህን በተመጣጠነ መልኩ መመገብ ጤንነትን ለመጠበቅ ያስችላል።

መመሪያ ሁለት - በምንባቡ መሠረት፥ ቀጥለው የቀረቡት ዐ.ነገሮች ሃሣብ ትክክል ከሆኑ እውነት፥ ትክክል ካልሆኑ ሀሰት በማለት በተሰጠው ክፍት ቦታ ፃፉ።

_____ 7. ደም እንዳይረጋ የሚያደርገው ማዕድን ካልሲየም ነው።

_____ 8. ከቅጠላ ቅጠልና ከእንቁላል አስኳል አነስተኛ መጠን ያለው የብረት ማዕድን ስናገኝ፥ ከእንጀራ ግን በብዛት እናገኛለን።

_____ 9. ከጥራጥሬና ከለውዝ ከሚገኝ ፎስፎረስ ይልቅ፥ ከአትክልትና ከስጋ የሚገኘው ይበልጣል።

_____ 10. ብረት አስቴኔያዊና ኢ-ብረት አስተኔያዊ ንጥረ ነገሮች የሚገኙባቸው ምግቦች በሽታን ለመከላከል ይጠቅማሉ።

መመሪያ ሦስት - ቀጥለው ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት መልሶች መካከል በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በተሰጠው ቦታ ፃፉ

_____ 11. በመጀመሪያው አንቀፅ ውስጥ ከነዚህ ቃል የሚያመለክተው ምንን ነው?

ሀ. ማዕድናትን ነው ሐ. የንጥረ ምግቦችን ጥቅም ነው

ለ. የተመጣጠነ ምግብን ነው መ. ሰውነታችንን ነው

_____ 12. ለአብነት የሚለውን ቃል በየትኛው ቃል ተክተን ማንበብ እንችላለን?

ሀ. ለሙከራ ለ. ለመነሻ ሐ. ለምሳሌ መ. ለነገሩ

_____ 13. የሰውነታችን ሦስት ከመቶ የሚሆነው ክፍል የተሠራው ከ_____ ነው?

ሀ. ከካልሲየም÷ ፎስፎረስና ፖታሲየም

ለ. ከሶዲየም÷ ክሎሪንና ብረት

ሐ. ከአዮዲን÷ መደብና ማግኒዚየም

መ. ከሁሉም

_____ 14. ንጥረ ምግቦች በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈሉት በምንድን ነው?

ሀ. ብረት አስተኔና ኢ-ብረት አስተኔ የሆኑትን በመለየት ነው

ለ. ከሚገኙበት የማዕድን ክፍል አኳያ ነው

ሐ. ከሚሰጡት ጥቅም አኳያ ነው

መ. ከሚገኙበት የምግብ አይነት አኳያ ነው

_____ 15. ብረት አስተኔ የሚለው ቃል የሚገልፀው

ሀ. ከብረት የሚገኝ የምግብ ክፍል ነው

ለ. የብረትነት ባህሪ ያላቸው ማዕድናትን ነው

ሐ. ከብረት ማዕድናት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ማዕድናትን ነው

መ. የብረትነት ባህሪ የሌላቸውን ማዕድናትን ነው

_____ 16. አክስጅንና ካርቦን ዳይአክሳይድን አመላላሽ የሆነው_____ ነው?

ሀ. የብረት ማዕድን ሐ. ቀይ የደም ህዋስ

ለ. ካልሲየምና ፎስፎረስ ለ. ንጥረ ምግቦች

_____ 17. ነርቮችና ጡንቻዎች በሚገባ ሥራቸውን መስራት የማይችሉት_____

ሀ. የካልሲየም እጥረት ሲገጥም ነው::

ለ. የብረት ማዕድን እጥረት ሲገጥም ነው::

ሐ. የካልሲየምና የፎስፎረስ እጥረት ሲገጥም ነው::

መ. የብረትና የአዮዲን እጥረት ሲገጥም ነው::

18. የወተት ክፍል ምግቦች በተለይም አይብና ወተት በካልሲየም የበለፀጉ ናቸው። ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. አይብና ወተት ብቻ በካልሲየም የበለፀጉ ናቸው ማለቱ ነው።

ለ. የወተት ክፍሎች በሙሉ በካልሲየም የበለፀጉ ናቸው ማለቱ ነው።

ሐ. ከሌሎች የወተት ክፍሎች በበለጠ ካልሲየም የሚገኘው ከአይብና ከወተት ነው ማለቱ ነው።

መ. ካልሲየም ከወተትና ከአይብ በስተቀር በሌሎች ክፍሎች አይገኝም ማለቱ ነው።

19. በሁለተኛው አንቀፅ መጨረሻ ላይ የተሠመረበት እነዚህ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማንን ነው?

ሀ. በሽታን ለመቋቋም የሚረዱ ምግቦችን ነው።

ለ. ማዕድናትን ነው።

ሐ. ብረት አስተኔያዊ ወይም ኢ-ብረት አስተኔያዊ ንጥረ ነገሮች ያላቸው ምግቦችን ነው።

መ. ንጥረ ምግቦችን በአጠቃላይ ነው።

20. የምንባቡ አጠቃላይ ሃሣብ ምንድን ነው?

ሀ. የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ለጤንነት አስፈላጊ መሆኑን መግለፅ

ለ. ለሰውነት አስፈላጊ የሆኑ የማዕድናትን አይነትና የሚገኙበትን የምግብ ክፍል ማስተዋወቅ

ሐ. የተለያዩ ማዕድናት የያዙ ምግቦች መመገብ በሽታን ለመከላከል የሚያግዙ መሆናቸውን መግለፅ

መ. ሁሉንም ሃሣቦች መግለፅ ነው።

አባሪ ሦስት - በአማራጭነት የቀረበ የትምህርት ዝግጅት ናሙናዎች፣

ክፍለ-ትምህርት ሦስት

ርዕስ - የመንግሥት አካላት

ቅድመ-ንባብ እንዋኔዎች

መልመጃ አንድ - ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት በቡድንና በጥንድ በመሆን በሚከተሉት የመነሻ ሃሣቦች ላይ ተወያዩ፣

ሀ - መንግሥት ማለት ምን ማለት ነው?
ለ - መንግሥት ህዝብ ነው፣ ህዝብ መንግሥት ነው ሲባል ትሰማላችሁ ምን ማለት ይመሰላችኋል::


መልመጃ ሁለት - ቀጥለው የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት ፍች ታውቃላችሁ? እስኪ የምታውቁዋቸውንና የማታውቁዋቸውን ለይታችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ

ሀ - ምክር ቤት	መ - ፌደሬሽን
ለ - ጉባኤ	ሠ - የህግ አስፈፃሚ
ሐ - የመንግሥት መዋቅር	ረ - ክልል

- በማታውቁዋቸው ቃላትና ሀረጋት ላይ ተወያይታችሁ ፍቻቸውን ግለፁ፣

የንባብ ወቅት እንዋኔዎች

መልመጃ ሦስት - ከዚህ በታች የመንግሥት አወቃቀርን የሚያሳይ መዋቅር ቀርቧል፣ ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት መዋቅሩን ተመልከቱ፣ በመዋቅሩ ወስጥ የጎደሉበታዎችን ምንባቡን አንብቡና አሟሉ::



መልመጃ አራት - በ ሀ ወገን ያሉትን ከ ለ ወገን ጋር አዛምዱ

ሀ	ለ
1. የፌደሬሽን ምክር ቤት	ሀ - የመስተዳድር አካል
2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት	ለ - ሕግ ያወጣል ያፀድቃል
3. የተወካዮች ምክር ቤት	ሐ - ብሔረሰቦችን ይወክላል
	መ - የፍትህ አገልግሎት

መልመጃ አምስት - ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ምንባቡን በገመታ አንብቡና አሟሉ፡

1 - መንግሥት ዋና ዋና አካላት አሉት::
2 - ህግ አውጪው ተግባሩ _____ ነው::
3 - የፍትህ አካላት ዋና ተግባራቸው _____ ነው::
4 - በክልሎች መካከል ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከተው _____ ነው::

ድህረ - ንባብ እንዋኔዎች

መልመጃ ስድስት -

1. የኢትዮጵያ መንግሥት ምክር ቤቶች ተግባርን የአካባቢ ሳይንስ መምህራችሁን በመጠየቅ ግለፁ
2. የመንግሥት ተግባርና ኃላፊነት ምንድን ነው?
3. በፓርላማና በመንግሥት ምክር ቤት መካከል ልዩነት እንዳለ መምህራኖቻችሁን ጠይቁና አንድ አንቀፅ ፃፉ::
4. የምትኖሩበትን ቀበሌ መስተዳድር አወቃቀር የሚያሳይ አንድ መዋቅር ሠርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::


ክፍለ ትምህርት - አራት
ርዕስ - የሳንባ ነቀርሳ ገፅ - 28

የትምህርቱ ዓላማ
- ለጉዳዩ ማንበብን ተግባራዊ ያደርጋሉ
- የተወሰኑ መረጃዎችን ለማግኘት የአሰሳ ንባብ ያካሂዳሉ
- ስዕላዊ መረጃዎችን ያነባሉ፣ ይተረጉማሉ
- ዝርዝር ጃዎቸን ለማግኘት ያነባሉ

አቀራረብ -

ቅድመ- ንባብ እንዋኔዎች

ሀ. በመሣሪያ መጽሐፋችሁ ገፅ 28 ላይ ያለውን ስዕል ተመልከቱና ስዕሉ ምን እንደሚያመለክት ተወያዩ፣ ከውይይታችሁ የምተታገኙትን መነሻ በማድረግ በስዕሉ ምትክ በሚከተለው ሣጥን ውስጥ ሙሉ



ለ. በአካባቢያችሁ ያሉ የታወቁ ተላላፊ በሽታዎች ዓይነቶችን ዘርዝሩ

የንባብ ወቅት እንዋኔዎች

መልመጃ - አንድ - ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብቡ፣ ጥያቄዎቹን ካነበባችሁ በኋላ ለጥያቄዎቹ መልስ ለመስጠት ብቻ ምንባቡን አንድ ጊዜ በፍጥነት አንብቡና ጥያቄዎቹን መልሱ::

1. የሳንባ ነቀርሳ በሽታ_____በሽታ ነው::
2. የሳንባ ነቀርሳ በሽታ መንስኤ የሆኑ ጀርሞች የሚለዩት በ_____ነው::
3. በሳንባ ነቀርሳ በሽታ የተያዘ ሰው መዳን የሚችለው በ_____ብቻ ነው::
4. በሽታው የሚጠቃው_____ሳይለይ ነው::

መልመጃ - ሁለት

1 - ምንባቡን እንደገና በዝግታ አንብቡና ትክክለኛውን መልስ በምንባቡ መሠረት በመምረጥ መልሱ

ሀ. የሳንባ ነቀርሳ በሽታ የሚተላለፍባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?
ሀ. በሳል ለ. በመማስነጠስ ሐ. በትንፈፋሽ
መ. ሁሉም

ለ. በሳንባ ነቀርሳ የተያዘ በሽተኛ ምን ምልክት ይታይበታል?
ሀ. የደረት ህመም ሐ. የቆየ ሳል
ለ. ትኩሳት መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ::

ሐ. አንድ ሰው በሳምባ በሽታ እንዳይያዝ ሊያደርግ የሚገባው ጥንቃቄ ምንድን ነው?
ሀ. ወተት አፍልቶ መጠጣት ሐ. አለማስነጠስ
ለ. ውኃ መፍላት መ. መልስ የለም

2. በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩና አጭር መልስ ስጡ

ሀ. አንድ ሰው በሳንባ ነቀርሳ በሽታ ላለመያዝ ማድረግ የሚገባውን ተጨማሪ ጥንቃቄ ግለፁ::
ለ. አንድ ሰው በሳንባ በሽታ የመያዝ ምልክት ከታየበት ምን ማድረግ አለበት?
ሐ. በበሽታው የተያዘ ሰው ወደ ሌላ ሰው እንዳያስተላልፍ ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ አለበት?

ምጋቤ - ምላሽ - ለጥያቄዎቹ የሰጣችኋቸውን መልሶች ከጓደኞቻችሁ ጋር ደብተራችሁ በመለዋወጥ አስተያዩ
- መልሶቻችሁ ልዩነት ካላቸው እንደገና ምንባቡን በጋራ አንብቡና መልሳችሁን አስተካክሉና ለመምህራችሁ አሳዩ
- መምህራችሁ የሚሰጡትን አጠቃላይ እርማት ተቀብላችሁ ዓፉ

ድህረ - ንባብ እንዋኔ

1. በአካባቢያችሁ የሚታወቅ አንድ በሽታ በመውሰድ
   ሀ. መንስኤውን ለ. ምልክቱን ሐ. መከላመያውን
   መ. የሚያስከትለውን ጉዳት የሚገልፅ አንድ ጽሑፍ አዘጋጅ ጽሑፉን ስታዘጋጅ የሚከተሉትን ቀላት ተጠቀሙ፡ ተያዘ፣ መንስኤ፣ ተሰራጨ፡ ማመርቀዝ፣ መፈወስ፡ ተላላፊ፡ ቫይረስ

ክፍለ - ትምህርት አምስት
ርዕስ - ሠንጠረዥ

ቅድመ - ንባብ እንዋኔ

ሀ. ከዚህ በታች የቀረበውን ሠንጠረዥ ተመልከታችሁ ስለምን ለመግለፅ እንደቀረበ ተወያዩ

ዓይነት	መጠን በኪሎ	የገበያ ዋጋ
ጤፍ	100	250.00
ስንዴ	50	100.00
ገብስ	25	30.00
በቆሎ	20	20.00
ምስር	10	40.00
ስኳር	5	20.00

የንባብ ወቅት እንዋኔ

ሀ. ከዚህ በታች የተጠየቁትን ጥያቄዎች ሠንጠረዡን መሠረት በማድረግ መልሱ

1. በገበያ ዋጋ ከሁሉም ርካሽ የሆነው የቱ ነው?
2. በገበያ ዋጋ ከሁሉም ውድ የሆነው የቱ ነው?
3. አንድ ሰው ለወር ቀለቡ 50ኪሎ ጤፍ፣ 20ኪሎ ስንዴ፣ 5ኪሎ ምስርና 2 ኪሎ ስኳር ቢገዛ የዕለት ወጭው ስንት ይመስላችኋል?
4. በእኩል ዋጋ የሚሸጡት_____ና_____ናቸው::

ድህረ - ንባብ እንዋኔ

ሀ. ከላይ የቀረበውን ሠንጠረዥ ምሳሌ አድርጋችሁ በትምህርት ቤታችሁ የሚገኙ ክበባትንና የአባላትን ብዛት የሚያሳይ ሠንጠረዥ ሥሩ

ክፍለ - ትምህርት ስድስት
ርዕሰ - ማኅኔታዊ መስክን የሚያሳይ ሙከራ

ቅድመ - ንባብ እንዋኔ

ሀ. ቀጥለው በቀረቡት መነሻ ሃሣቦች ለላይ ተወያዩና ለመምህራችሁ የደረሳችሁበትን ሀሳብ በተወካያችሁ ግለፁ

1. ማግኔት ሊሰባቸው የሚችላቸው ነገሮች ምን ዓይነት ናቸው?

2. የማግኔትን ኃይል ወደሌላ ብረት ነክ ቁሶች ዳስተላለፍ እንዴት እንደሚቻል በአካባቢ ሳይንስ ትምህርታችሁ የተማራችሁትን በማስታወስ አሠራሩን ተወያይታችሁ ግለፁ::

የንባብ - ወቅት ክንዋኔ

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ማግኔታዊ ስክን የሚያሳዩ መስመሮችን ለመሥራት መከተል የሚገባችሁን ተግባራት የሚገልፅ ፅሑፍ ቀርቧል ፅሑፉን አንብቡና ተግባሩን ፈፅሙ

ማግኔታዊ መስክን የሚያሳዩ መስመሮችን ለመሥራት ካርክ ወረቀት፣ የብረት ዱቄት፣ ትልቅ ማግኔት፣ ጨውማ ውኃ፣ የመርጨያ መሣሪያ ያስፈልጋል::

አሰራሩም ማግኔቱን ከካርድ ወረቀት ስር ማስቀመጥና ካርዱ ላይ የብረት ዱቄቱን ማፍሰስ፣ ከዚያ በጣታችሁ መስመሮቹ እህኪለዩ ድረስ ካርዱን በጣታችሁ መታ መታ ማድረግና ጨውማ ውኃውን መርጨት:: ከብዙ ሰዓታት በኋላ ደግሞ መርጨት::

ድህረ - ንባብ ክንዋኔ

1. ማግኔታዊ መስክን የሚያሳይ መስመር ለመሥራት በቅድሚያ ምን ማድረግ ይገባል?
2. ከላይ የቀረበውን የሙከራ አንቀፅ መሠረት በማድረግ የአካባቢ ሳይንስ መጽሐፋችሁን አንብባችሁ ቆሻሻ ውኃን ለማጣራት የሚደረግ ሙከራን ለማከናወን የሚያስቸል አንድ አንቀጽ ፃፉ::

ሀ. የክትትልና የመከራ ቡድን ተማሪዎች የቅድመና ድህረ-ልምምድ የንባብ ፈተና ውጤት መግለጫ

ተራ ቁጥር	የክትትል ቡድን ተማሪዎች ውጤት		የመከራ ቡድን ተማሪዎች ውጤት	
	ቅድመ-ልምምድ	ድህረ-ልምምድ	ቅድመ-ልምምድ	ድህረ-ልምምድ
1	30	45	50	70
2	60	55	35	45
3	45	40	55	75
4	60	55	60	80
5	45	40	45	65
6	45	60	65	80
7	40	45	35	45
8	60	55	50	70
9	35	35	50	65
10	65	55	30	40
11	50	55	45	60
12	60	45	45	50
13	50	45	50	60
14	55	65	30	45
15	35	50	55	75
16	55	50	45	50
17	40	50	45	60
18	55	45	55	50
19	55	60	50	65
20	50	45	45	40
21	65	55	45	65
22	45	40	40	55
23	45	55	55	70
24	50	55	50	70
25	40	65	40	55
26	60	55	35	40
27	60	55	55	75
28	35	40	50	60
29	45	50	35	40
30	60	55	40	60
31	35	30	50	70
32	45	50	45	70
33	50	45	50	65
34	45	40	50	55
35	45	40	55	70
36	50	55	35	55
37	35	45	60	65
38	55	45	50	55
39	40	45	45	65
40	50	60	65	80
አማካይ Mean	48.63	49.5	47.25	60.75
ካሬ ልይይት Variance	83.72	65.93	73.62	135.72

አባሪ አራት - ለ

የመከራና የክትትል በድን የቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት የቲ-ስሌት ዝርዝር አሠራር

$$t - cal = \frac{\overline{x1} - \overline{x2}}{\sqrt{\frac{s_1^{\,2}(n-1) + s_2^{\,2}(n_2-1)}{n_1 + n_2 - 2}}} \qquad \left[\left(\frac{1}{n_1} + \frac{1}{n_2}\right)\right]$$

$$= \frac{48.63 - 47.25}{\sqrt{\frac{83.72\,(40-1) + 73.62\,(40-1)}{40+40-2}}} \qquad \left[\left(\frac{1}{40} + \frac{1}{40}\right)\right]$$

$$= \frac{1.38}{\sqrt{\frac{3265.08 + 2871.18}{78}}} \quad (0.05)$$

$$= \frac{1.38}{\sqrt{78.67}} \quad (0.05)$$

$$= \frac{1.38}{\sqrt{3.934}}$$

$$= \frac{1.38}{1.9833}$$

$$= 0.696$$

አባሪ አራት - ሐ

የክትትል ቡድን ተማሪዎች የድህረና ቅድመ ልምምድ ፈተናዎች ውጤት የቲ-ስሉት ዝርዝር አሠራር

$$t - cal = \frac{\overline{x_1} - \overline{x_2}}{\sqrt{\frac{s_1^2 (n_1 - 1) s_2^2 (n_2 - 1)}{n_1 + n_2 - 2}}} \quad \left[\left(\frac{1}{n_1} + \frac{1}{n_2}\right)\right]$$

$$= \frac{49.5 - 48.63}{\sqrt{\frac{65.93(40-1) + 83.72(40-1)}{40+40-2}}} \quad \left[\left(\frac{1}{40} + \frac{1}{40}\right)\right]$$

$$= \frac{0.87}{\sqrt{\frac{2571.27 + 3265.08}{78}}} \quad (0.05)$$

$$= \frac{0.87}{\sqrt{\frac{5836.35}{78}}} \quad (0.05)$$

$$= \frac{0.87}{\sqrt{74825}} \quad (0.05)$$

$$= \frac{0.87}{\sqrt{374125}}$$

$$= \frac{0.87}{1.934}$$

$$= 0.4498$$

አባሪ አራት - መ

የመከራ ቡድን ተማሪዎች የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተናዎች ውጤት የተ-
ስሉት ዝርዝር አሠራር

$$t - cal = \frac{x_1 - x_2}{\sqrt{\frac{s_1^2 (n-1) + s_2^2 (n-2)}{n_1 + n_2 - 2}} \quad \left[\left(\frac{1}{n_1} + \frac{1}{n_2}\right)\right]}$$

$$= \frac{60.75 - 47.25}{\sqrt{\frac{135.72 (40-1) + 73.62 (40-1)}{40 + 40 - 2}} \quad \left[\left(\frac{1}{40} + \frac{1}{40}\right)\right]}$$

$$= \frac{13.5}{\sqrt{\frac{5293.08 + 2871.18}{78}} \quad (0.05)}$$

$$= \frac{13.5}{\sqrt{104.67} \quad (0.05)}$$

$$= \frac{13.5}{\sqrt{5.234}}$$

$$= \frac{13.5}{2.288}$$

$$= 5.90$$


አባሪ - አምስት

ምዕራፍ ስድስት

የሳምባ ነቀርሳ በሽታ

የነቀርሳ በሽታ እድሜን፣ ፆታንና ቀለምን ሳይለዩ የሰውን ልጅ ከሚያጠቁና ተላላፊ ከሆኑ በሽታዎች አንዱ ነው። ዋና ዋና መተላለፊያ መንገዶቹም፦

ሀ. በሽተኛው በሚስልበት፣ በሚያስነጥስበትና በሚተነፍስበት ጊዜ ለበሽታው ምክንያት የሆኑ ጀርሞች በአየር ተሰራጭተው ወደ ጤነኛው ሰው መተላለፋቸው።



ለ. በነቀርሳ በሽታ የተያዙ ላሞችን ወተት ሳያፈሉ ጥሬውን በመጠጣት ወዘተ... ናቸው።

በበሽታው የተያዘ ሰው የተለያዩ ምልክቶች ይታዩበታል። እነርሱም፦ የቆየ ሳል፣ ደም የቀላቀለ አክታ፣ የደረት ህመም፣ ትኩሳት፣ የሰውነት ክብደት መቀነስ ወይም በየጊዜው መክሳት፣ የእጢ ማበጥና ማመርቀዝ ናቸው።

ስለዚህ በዚህ በሽታ ላለመጠቃት ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። ሊደረጉ የሚገባቸው ጥንቃቄዎችም

ሀ. ህፃናትን ማስከተብ

ለ. በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር በተፋፈገ ቤት ውስጥ በአንድነት አለመኖር

ሐ. የላም ወተትን አፍልቶ መጠጣት

መ. በቤተሰብም ሆነ በአካባቢው ሳል የቆየባቸው ሰዎች ወደ ጤና ጣቢያ ሄደው እንዲመረመሩ ማድረግ

ሠ. የበሽተኛው ቤተሰቦችና የቅርብ ወዳጆች አስፈላጊውን ምርመራ ማድረግ

ረ. የሳምባ ነቀርሳ ያለባቸው ሰዎች በሚያስላቸውና በሚያስነጥሳቸው ጊዜ አፋቸውን በመሀረብ መያዝ

ሰ. የነቀርሳ በሽተኞች የታዘዘላቸውን መድኃኒት ሳይሰለቹ እስከመጨረሻው መውሰድ

ሸ. ስለ ሳምባ ነቀርሳ በየደረጃው በሚገኙ የጤና ድርጅቶች ትምህርት እንዲሰጥ ማድረግ ናቸው።

አንድ ሰው በዚህ በሽታ የተያዘ መሆኑን ከተጠራጠርን ወደ ሐኪም ቤት በመውሰድ በምርመራ ማረጋገጥ ይቻላል። ህመምተኛው በሳምባ ነቀርሳ የተያዘ መሆኑንም ከዚህ በታች በቀረቡት ዘዴዎች ማረጋገጥ ይቻላል። መንገዶቹም፦

ሀ. ከበሽተኛው አክታ ወስዶ በላቦራቶሪ ምርመራ በማድረግ የበሽታው መንስኤ የሆኑትን ጀርሞች በመለየት

ለ. እድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆኑና ከአሁን በፊት ክትባት ላልወሰዱ ህፃናት በክትባት መልክ የሚደረግ ምርመራ ናቸው።

ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች ምርመራ ተካሂዶ በሽታው ከታወቀ በኋላ በሐኪም የሚታዘዝ መድኃኒት በመውሰድ መዳን ይቻላል።

መልመጃ አንድ

ሀ. በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. የሳምባ ነቀርሳ በሽታ የሚያጠቃው _____ ሳይለይ ነው፡፡

ሀ. ዕታን ለ. እድሜን ሐ. ቀለምን መ. ሁሉም

2. ሳምባ ነቀርሳ _____ በሽታ ነው፡፡

ሀ. ተላላፊ ሐ. ሀ እና ለ

ለ. የማይተላለፍ መ. መልሱ አልተሰጠም

3. የሳምባ ነቀርሳ የሚተላለፍባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. በሳል ለ. በማስነጠስ ሐ. በትንፋሽ መ. ሁሉም

4. በሳምባ ነቀርሳ የተያዘ በሽተኛ ምን ምልክት ይታይበታል?

ሀ. የደረት ህመም ሐ. የቆየ ሳል

ለ. ትኩሳት መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

5. አንድ ሰው በሳምባ ነቀርሳ እንዳይያዝ ሊደረግ የሚገባው ጥንቃቄ ምንድ ነው?

ሀ. ውሃን አፍልቶ መጠጣት ሐ. ሻይ አፍልቶ መጠጣት

ለ. የላም ወተት አፍልቶ መጠጣት መ. መልሱ አልተሰጠም

ለ. ትክክለኛውን ፍች በምንባቡ መሠረት ምረጡ፡፡

1. <u>ተሰራጭተው</u>

ሀ. ተንሰራፍተው ለ. ተበትነው ሐ. ተሰርተው መ. ተጉዘው

2. <u>የተያዙ</u>

ሀ. የተጨበጡ ለ. የተነከሱ ሐ. የተለከፉ መ. የታቀፉ

3. <u>የቀላቀለ</u>

ሀ. የተጨመረበት ለ. የተቀቀለ ሐ. የተበከለ መ. የተመረዘ

4. <u>ማመርቀዝ</u>

ሀ. ማበጥ ለ. መቋጠር ሐ. ማገርጥ መ. ማቁሙ

5. <u>ላለመጠቃት</u>

ሀ. ላለመያዝ ለ. ላለመነካት ሐ. ላለመሞት መ. ላለመጎዳት

6. <u>በተፋፈገ</u>

ሀ. በተፋፈነ ለ. በተጣበበ ሐ. በተጨናነቀ መ. ሁሉም

7. ሳይሰለቹ

ሀ. ሳያቋርጡ ለ. ሳይታክቱ ሐ. ሳይደክሙ መ. ሁሉም

8. ከተጠራጠርን

ሀ. ከፈራን ለ. ካመንን ሐ. ካገመትን መ. ሁሉም

9. ላልወሰዱ

ሀ. ላልወረሱ ለ. ላልመረጡ ሐ. ላላጋዙ መ. ላልተከተቡ

10. መዳን

ሀ. መፈወስ ለ. መጠንከር ሐ. መበርታት መ. ሁሉም

መልመጃ ሁለት

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡ ጥያቄዎችን በምሳሌው መሠረት ስሯቸው

	ከቤት	ወደቤት	የቤት
1. ቤት			
2. ሜዳ	____	____	____
3. ት/ቤት	____	____	____
4. መኪና ተራ	____	____	____
5. እርሻ	____	____	____
6. መሬት	____	____	____
7. ሐኪም ቤት	____	____	____
8. ሱቅ	____	____	____
9. ቢሮ	____	____	____
10. ጓዳ	____	____	____

ለ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት በምሳሌው መሠረት አራቧቸው

	መጥቷል	ይመጣል	ሳይመጣ	ይመጣና
1. መጣ				
2. በላ	_____	_____	_____	_____
3. ሰራ	_____	_____	_____	_____
4. ሮጠ	_____	_____	_____	_____
5. ወጋ	_____	_____	_____	_____
6. ፃፈ	_____	_____	_____	_____
7. ሰጠ	_____	_____	_____	_____
8. ገዛ	_____	_____	_____	_____
9. ዋጠ	_____	_____	_____	_____
10. በራ	_____	_____	_____	_____

ሐ. በቀረቡላችሁ ባዶ ቦታዎች ትክክለኛውን ቃል በመምረጥ ሙሉ።

ይሁን እንጂ	ስለዚህ	አለበለዚያ

1. ቤቱ በጣም ሩቅ ነው፤ _____ ቶሎ ቶሎ መሄድ አለብህ።
2. ጠንክረህ ማጥናት አለብህ፤ _____ በፈተና ትወድቃለህ።
3. አበበ የመጣው ዘመዶቹን ሊጠይቅ ነው፤ _____ ባሰበው ቦታና ወቅት ሊያገኛቸው አልቻለም።
4. ወደ ት/ቤት መሄድ አስቦ ነበር፤ _____ መኪና ሊያገኝ አልቻለም።
5. አካባቢያችንን ማፅዳት ይጠበቅብናል፤ _____ ቆሻሻው የጤና ጠንቅ ይሆናል።
6. የመኖሪያ ቤት ለመሥራት አቅዶ ነበር፤ _____ ለቤትመስሪያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ማግኘት አልቻለም።
7. የለበስከው ልብስ በጣም አድፏል፤ _____ በነገው እለት ልታጥበው ይገባል።
8. ወደ ኪስ ሜዳ መሄድ ፈልጎ ነበር፤ _____ በዛሬው እለት ውድድር እንደሌለ ስለተገለፀለት ቀረ።
9. የጓሮ አትክልትህ አፍርቷል፤ _____ ለምግብነት ልትጠቀምበት ትችላለህ።
10. ዛሬ እኛ ቤት እንግዳ ይመጣል፤ _____ ቤቱን በሚገባ አፅድተን ልንጠብቅ ይገባል።

መ. ከዚህ በታች የቀረቡትን አዎንታዊ ዐነገሮች ወደ አፍራሽ ዐነገሮች ለውጧቸው።

ምሳሌ ልጁ ምሳውን በላ።

ልጁ ምሳውን አልበላም።

1. ተማሪው ደብተር ገዛ። _____
2. ልጁ ልብሱን አጠበ። _____
3. ወደ ት/ቤት ሄደ። _____
4. የውብሸት ፈረስ ጥቁር ነው። _____
5. በምድር ባቡር ተሳፈረ። _____
6. ከቤታቸው ደጃፍ የነበረውን እንጨት ቆረጠው።

_____

7. ከትምህርት ይልቅ ጨዋታን ይወዳል። _____
8. ፀጉሩን ተስተካክሏል። _____
9. የከበደ ልብስ ተቀደደ። _____
10. ከበደና ገ/ማነህ መጡ። _____

መልመጃ ሃ'ስት

ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ።

1. በአካባቢያችሁ የሚኖረውን ሕዝብ የሚያሰቃዩ የበሽታ ዓይነቶችን ዘርዝሩ።

2. የአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ በነዚህ በሽታዎች እንዳይታወክ ምን ማደረግ አለበት? ተወያዩበት።

3. በአካባቢያችሁ ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል አለ? የአካባቢው ነዋሪ በነኚህ ድርጅቶች የሚጠቀመው በምን መልክ ነው? ተነጋገሩበት።

4. "ሐኪም ብሆን" በሚል ርዕስ አንድ ጽሑፍ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ድንች የሚፈለገውን ውጤት እንዲያስገኝ ከላይ የተጠቀሱትን የአሠራር ስልቶች መከተል ይጠትማል።

መልመጃ አንድ

ሀ. በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ምርጡ።

1. ስኳር ድንች ቅርፁ _____ ነው።
   ሀ. ክብ ለ. ጠፍጣፋ ሐ. ሞላላ መ. ዝርግ
2. ስኳር ድንች ዝርያው ስንት ዓይነት ነው?
   ሀ. አንድ ለ. ሁለት ሐ. ሶስት መ. አራት
3. የስኳር ድንች መልኮች _____ ና _____ ናቸው።
   ሀ. አረንጓዴና ቢጫ ሐ. አርንጓዴና ቀይ
   ለ. ቢጫና ቀይ መ. ቢጫና ነጭ
4. ገበሬዎች በብዛት የሚያበቅሉት የስኳር ድንች ዓይነት የትኛው ነው?
   ሀ. ጥሩ ምርት የሚያስገኘውን ሐ. ቢጫ ሥር ያለውን
   ለ. ነጭ ሥር ያለውን መ. ነጭና ቢጫ ሥር ያለውን
5. የስኳር ድንች የትኛው አካሉ ነው የሚተከለው?
   ሀ. ኮረቱ ለ. አገዳው ሐ. ሀ እና ለ መ. ሥሩ
6. የስኳር ድንች ሲተከል አገዳው የሚመረጥበት ምክንያት ምንድ ነው?
   ሀ. ጥሩ ውጤት ስለሚያስገኝ
   ለ. ኮረቱ ለሌላም አገልግሎት ስለሚውል
   ሐ. አገዳውን መትከል ስለሚቀል
   መ. ለመኮትኮት ስለማያስቸግር
7. ስኳር ድንች በሚተከልበት ጊዜ መሬት ውስጥ የሚቀበረው የአገዳው ስንቱ እጅ ነው?
   ሀ. አንድ እጅ ሐ. ሶስት እጅ
   ለ. ሁለት እጅ መ. አራት እጅ
8. ስኳር ድንች በመስመር በሚተከልበት ወቅት በየመስመሮቹ መሀከል ያለው ርቀት _____ ክንድ መሆን አለበት
   ሀ. አንድ ሐ. ሶስት
   ለ. ሁለት መ. አራት

9. የስኳር ድንች በደንብ እስኪያቆጠቁጥ ድረስ _____ መኩተኮት አለበት፡፡

ሀ. በጥልቀት ሐ. እንደተገኘ

ለ. ጥልቀት በሌላው መ. መልሱ አልተሰጠም

10. ኩትኳቶ ለስኳር ድንች ተክል ምን ጥቅም ይሰጣል?

ሀ. ስኳር ድንቹ አፈር እንዲታቀፍ ያደርጋል፡፡

ለ. አረም ያጠፋል፡፡

ሐ. ጥሩ ውጤት ያስገኛል፡፡

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

ለ. በምንባቡ መሠረት በፍች የሚመሳሰሉትን ቃላት አዛምዱ

ሀ.	ለ.
1. ይጣፍጣል	ሀ. ብዙውን ጊዜ
2. የሚያበቅሉት	ለ. የበሰለ
3. መመገብ	ሐ. ¾
4. በአብዛኛው	መ. የሚተክሉት
5. ተመሳሳይ	ሠ. ዘዴዎች
6. የደረሰ	ረ. ይጥማል
7. ሶስት እጅ	ሰ. ማስወገድ
8. እጥረት	ሸ. እኩል
9. ማጥፋት	ቀ. ማነስ
10. ስልቶች	በ. መብላት

መልመጃ ሁለት

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በምሳሌው መሠረትሥሩ

1. ሀገር	ሀገሬ	ሀገሩ	ሀገርህ	ሀገራችን	ሀገራቸው
2. ሀብት	_____	_____	_____	_____	_____
3. ልብ	_____	_____	_____	_____	_____
4. ልብስ	_____	_____	_____	_____	_____
5. ልደት	_____	_____	_____	_____	_____
6. ሐረግ	_____	_____	_____	_____	_____

7. ሕልም _____ _____ _____ _____ _____
8. ሕንፃ _____ _____ _____ _____ _____
9. ስኳር _____ _____ _____ _____ _____
10. አካል _____ _____ _____ _____ _____

ለ. ጥያቄዎቹን በምሳሌው መሠረት ሥሩ።

1. ወደቀ	ስለወደቀ	ወዳደቀ	ወደቀች
2. አበሰ	_____	_____	_____
3. ለወጠ	_____	_____	_____
4. ሰረቀ	_____	_____	_____
5. መረገ	_____	_____	_____
6. መከተ	_____	_____	_____
7. ነከሰ	_____	_____	_____
8. ለበሰ	_____	_____	_____
9. ሰቀለ	_____	_____	_____
10. መረቀ	_____	_____	_____

ሐ. በ " ሀ " ረድፍ ሥር ለቀረቡት ቃላት በፍች ታቃራኒ የሆኑትን ከ" ለ " ረድፍ ሥር ከቀረቡት ቃላት በመምረጥ አዛምዱ

ሀ.	ለ.
1. ቀልድ	ሀ. ጥቁር
2. ጠብ	ለ. ሥራፈት
3. ቀይ	ሐ. ልበቢስ
4. ቅርብ	መ. ርካሽ
5. ሠራተኛ	ሠ. ቁም ነገር
6. ጠባብ	ረ. በድን
7. አስተዋይ	ሰ. ሰፊ
8. ውድ	ሸ. ከዳተኛ
9. ታማኝ	ቀ. ሰላም
10. ሀያው	በ. ሩቅ

መ. ከታች በቀረቡ ቃላት ዐ.ነገር መሥርቱ

1. ነደደ
2. ሰባ
6. ጎረምሳ
7. አሮጌ

3. ተለያየ
4. ደከመ
5. ቅርብ
8. በጠሰ
9. ተቀመጠ
10. ቀማ

መልመጃ ሦስት

ትክክለኛውን መልስ ስጡ

1. በስኳር ድንችና በተራው ድንች መሀከል ያለው ልዩነት ምንድነው? ተወያዩበት፡፡

2. ሥራቸው፣ ቅጠላቸውና ፍሬአቸው የሚበላ የተክል ዓይነቶችን ዘርዝሩ፡፡

3. አፈር ለአትክልት መትከያነት እንዲውል በምን መልክ መዘጋጀት አለበት? ተነጋገሩበት፡፡

4. በአካባቢያችሁ የሚገኘውን የግብርና መስሪያቤት ባለሙያ በማነጋገር በአካባቢው የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ ስለሚችል ተክል አተካከል፣ ሊደረግለት ስለሚገባ እንክብካቤ፣ ስለምርቱ አሰባሰብና የሚሰጠውን አገልግሎት በሚመለከት መረጃ በመሰብሰብ ሀሳቡን በጽሑፍ አደራጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት፣ ይህ ጥናት የራሴ ሥራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ምንጮች በሙሉ የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ::

ስም
ወንድአጥር ደነቀ

ፊርማ

አድራሻ:- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል

የማስረከቢያ ቀን:- ሰኔ 30/1993 ዓ.ም.